# ወጣት ሥራ ፈጣሪዎችን የአካታች ፋይናንስ ተጠቃሚ ማድረግ፡- ያለዋስትና በሚሰጥ ዲጂታል ብድር ዙሪያ የታዩ አነቃቂ የፖሊሲ እና የተግባር ለውጦች

## በኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ ላይ የተሰራ ንጥል ጥናት


መዚድ ናስር[1]

ፈጠነ ቦጋለ[2]

አቡሌ መሃሪ[3]


**Policy Working Paper 28/2025**


የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን

ሐምሌ 2025



***DISCLAIMER***

The views and opinions expressed in this publication are those of the authors and do not necessarily reflect the official policy or position of the Ethiopian Economics Association. Readers are encouraged to verify the information independently and seek professional advice where necessary. The authors will not be hold liable for any loss, damage, or inconvenience caused because of the use or reliance on the content of this publication.



[1] Senior Researcher, Team Leader, Trade & Industrial Development, Ethiopian Economics Association
[2] Assistant Professor, School of Humanities & Social Science, Adama Science and Technology University
[3] Director, Partnership and Communication Division, Ethiopian Economics Association

# ምስጋና

ይህ ጥናት የተዘጋጀው በኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን (ኢ.ኢ.አ.) ተመራማሪዎችና መረጃ ሰብሳቢዎች ነዉ። ለጥናቱ እውን መሆን ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ዋናውን ድጋፍ ያበረከተ ሲሆን ይህ ጥናት፣ ወጣት አፍሪካውያን ስራ ፈጣሪዎች የፋይናንስ አቅርቦት እድሎችን ተጠቅመው ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል ፋውንዴሽኑ ከሚያደርጋቸው ጥረቶች ውስጥ አንዱ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ የጥናት ቡድኑ፣ ለዚህ ጥናት መነሻ የሆኑትን መረጃዎች ለሰጡና ዕውቀት ላስጨበጡ ባለድርሻ አካላትና የጥናቱ ተሳታፊዎች ልባዊ ምስጋናውን ያቀርባል፤ በተጨማሪም የኢ.ኢ.አ. አስተዳደር በጥናቱ ወቅት በቅርበት ላደረገው ክትትልና ያልተቋረጠ ድጋፍ አድናቆቱን ይገልጻል፡፡ በተለይ ለክፍያ የፋይናንስ ቴክኖሎጂና ለኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ (ኦ.ህ.ስ.ባ.) ልባዊ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡ እነዚህ ተቋማት በኢትዮጵያ እየተሰፋፉ ስላለው የፋይናንስ መልክዓ-ምድር እና ያለ መያዣ ስለሚሰጥ ዲጂታል የብድር አቅርቦት ያላቸው ግንዛቤ የጥናት ቡድኑን በእጅጉ ጠቅሞታል፡፡ በመጨረሻም፣ ፊውቸር አፍሪካ ኮንሰልቲንግ የዚህን ጥናት ጽሁፍ አርትዖት በመስራት እንዲሁም ለንባብ አመቺ ቅርጽ በማላበስ ላደረገው አስተዋጽዖ ቡድኑ ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል፡፡

# ማውጫ


ምህጻረ ቃላት ....................iv

ጭምቅ ሀሳብ .................... v

1. መግቢያ .................... 1

1.1. ዳራ እና አውድ .................... 1

1.2. የንጥል ጥናቱ ዓላማዎች .................... 2

1.3. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ .................... 2

1.4. የንጥል ጥናቱ መዋቅር .................... 2

2. የኢትዮጵያ የፋይናንስ ሴክተር አውድ .................... 3

2.1. የማክሮ ኢኮኖሚያዊ አጠቃላይ እይታ .................... 3

2.2. የፋይናንስ ዘርፍ ስነ-ምህዳር ተዋናዮች .................... 3

3. የጥ.አ.መ.ኢ. ተግዳሮቶች እና እድሎች አጠቃላይ እይታ .................... 5

3.1. ጥ.አ.መ.ኢ. ለኢኮኖሚ ዕድገት ያላቸው አስተዋፅዖ .................... 5

3.2. ጥ.አ.መ.ኢ. ያጋጠሟቸው ተግዳሮቶች .................... 5

3.3. የዘ.ፋ.ተ.ስ.ፈ. ፕሮግራም አጠቃላይ እይታ .................... 7

4. መንግስት አመራር ለመስጠት እና በተግባር የሚገለጽ ሥራ ለመስራት ያለው ቁርጠኝነት፡ አስቻይ የፖሊሲ ከባቢ .................... 9

5. የዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. ያለዋስትና የሚሰጥ የብድር ሞዴል .................... 14

5.1. የፕሮግራሙ አጠቃላይ እይታ .................... 14

5.2. ለስኬት የሚያበቁ ቁልፍ ምክንያቶች .................... 19

5.3. ያጋጠሙ ተግዳሮቶች/ ፈተናዎች .................... 20

6. የሞዴሉ የስነ-ምህዳር ተፅእኖ .................... 23

7. ስነ-ምሕዳራዊ አንድምታዎች .................... 27

7.1. በፋይናንስ ዘርፍ ውስጥ ያሉ አወንታዊ፣ ውጫዊ ሁኔታዎች .................... 27

7.2. ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎች እና የገበያ መዛባት .................... 28

8. የወጣት ሥራ ፈጣሪዎች የአካታች ፋይናንስ ተጠቃሚነትን ለማስቀጠል የሚረዱ ተሞክሮዎች 31

8.1. የፋይናንስ ተቋማት - የብድር ሞዴሎችን ማዘመን .................... 31

8.2. የልማት አጋሮች - አካታች የብድር ሞዴሎችን መደገፍ .................... 34

8.3. ፖሊሲ አውጪዎችና ተሟጋቾች - የአስቻይ ከባቢ አላባውያን .................... 34

9. ማጠቃለያ .................... 36

10. ማጣቀሻ ጽሑፎች .................... 37

# የምስሎች ዝርዝር


ምስል 1: የፋይናንስ ዘርፍ ስነ-ምህዳር ተዋናዮች ........ 3

ምስል 2: የጥ.አ.መ.ኢ. ተግዳሮቶች ........ 7

ምስል 3: ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. የሚያተኩርባቸዉ ተግዳሮቶች ........ 9

ምስል 4: ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. የንግድ ሞዴል ገጽታ ........ 16

ምስል 5: የዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. እንቅስቃሴ አጠቃላይ ዕይታ ........ 17

ምስል 6: የተበዳሪው ጉዞ ........ 20

ምስል 7: 'በወጣት አፍሪካዊያን ይሰራሉ' የፋይናንስ ተደራሽነት ፕሮግራም መፍትሔ የተሰጣቸው ተግዳሮቶች ........ 70

# ምህጻረ ቃላት

| | |
|---|---|
| **ፋ.ተ.** | የፋይናንስ ተደራሽነት |
| **ኦ.ህ.ስ.ባ.** | የኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ |
| **ኮ.መ.ማ.ፕ** | የኮቪድ-19 መቋቋሚያ እና ማገገሚያ ፕሮግራም |
| **ማ.ስ.ኤ** | ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ |
| **ን.ሥ.ማ.ማ.አ.** | የንግድ ሥራ ማቅለያ ማሻሻያ አጀንዳ |
| **ፋ.ዘ.ስ.ስ** | የፋይናንስ ዘርፍ ስርፀት ስትራቴጂ |
| **ፋ.ዘ.ማ.አ** | የፋይናንስ ዘርፍ ማሻሻያ አጀንዳ |
| **ኢ.መ.** | የኢትዮጵያ መንግስት |
| **ሀ.ኢ.ማ.አ** | ሀገር-በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ |
| **ዓ.አ.ፋ.ኮ** | ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን |
| **ዓ.ሥ.ድ** | የዓለም ሥራ ድርጅት |
| **ጥ.አ.መ.ኢ.ተ** | የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ተቋቋሚነት |
| **ግ.ሚ.** | የግብርና ሚኒስቴር |
| **ሰ.ማ.ጉ.ሚ.** | የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር |
| **ጥ.አ.መ.ኢ** | ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች |
| **ኢ.ብ.ባ** | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ |
| **ብ.ዲ.ክ.ስ** | ብሔራዊ የዲጂታል ክፍያዎች ስትራቴጂ |
| **ብ.ዲ.ት.ስ.** | ብሔራዊ የዲጂታል ሽግግር ስትራቴጂ |
| **ብ.ፋ.ት.ስ.** | ብሔራዊ የፋይናንስ ትምህርት ስትራቴጂ |
| **ብ.አ.ፋ.ስ.** | የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ |
| **ብ.ሥ.ስ** | ብሔራዊ የሥርዓተ-ፆታ ስትራቴጂ |
| **ሥ.ፈ.ድ.መ.** | የስራ ፈጠራ የድርጊት መርሃ ግብር |
| **ግ.ኢ.ፕ.ኢ.** | የግል ኢንተርፕራይዝ ፕሮግራም በኢትዮጵያ |
| **ገ.ፋ.አ.ፕ** | የገጠር ፋይናንስ አመቻች ፕሮግራም |
| **ቁ.ብ.ህ.ሥ.ማ.** | የቁጠባ እና ብድር የህብረት ሥራ ማህበራት |
| **ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ** | ዘላቂ የፋይናንስ ተደራሽነት፣ ለሥራ ፈጠራ |
| **አ.መ.ኢ.ፋ.ፕ.** | የአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ የፋይናንስ ፕሮግራም |
| **ሴ.ሥ.ፈ.ል.ፕ.** | የሴቶች ሥራ ፈጠራ ልማት ፕሮግራም |

## ጭምቅ ሀሳብ

በኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው የክፍያ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ፣ ቁልፍ የፖሊሲ እና የተግባር ለውጦችን እና አዳዲስ የብድር ሞዴሎችን አስተዋውቋል። ይህ ንጥል ጥናት የሚያተኩረው በዚህ ቁልፍ ጉዳይ ላይ ይሆናል። ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች (ጥ.አ.መ.ኢ.) የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ናቸው። ሁሉን አቀፍ እድገትን በቀዳሚነት ይመራሉ፣ ድህነትን ይቀንሳሉ፣ 70% የአገሪቱን የስራ እድልም ይፈጥራሉ። ሆኖም፣ የ6.1 ቢሊዮን ዶላር ወሳኝ የገንዘብ ድጋፍ ክፍተት አቅማቸውን በእጅጉ ገድቦታል። ብድር በዋነኛነት የሚሰጠው ዋስትና ሊያቀርቡ ለሚችሉ ትልልቅ ኮርፖሬሽኖች ነው። ጥ.አ.መ.ኢ፣ በተለይም በወጣት ሴት ሥራ ፈጣሪዎች የሚመሩት፣ የብድር አገልግሎቱን የሚያገኙት በዝቅተኛ ደረጃ ነው። ይህ ልዩነት የሚመነጨው በፍላጎት እና በአቅርቦት በኩል ካሉ ውስብስብ ጉዳዮች የተነሳ ነው። ከፍላጎት አንጻር ካየነው፣ የወጣት ተበዳሪዎች ዋስትና ማስያዝ አለመቻል እና የብድር ታሪክ አለመኖር ተጠቃሽ ሲሆኑ በአቅርቦት በኩል ደሞ፣ ከፍተኛ የብድር ወጪዎች፣ ከአጠቃቀም አንጻር ለወጣቶች ተስማሚ የሆኑ የፋይናንስ አማራጮች አለመኖር ይገኙበታል። ባህላዊ የብድር አማራጮች ለወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ተደራሽ እና ዘላቂነት የሌላቸው መሆናቸው ታይቷል። በመሆኑም በፋይናንስ ዘርፉ ውስጥ አዳዲስ አቀራረቦችን ማስተዋወቅ አስፈላጊ ሆኗል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ በ2019 የተጀመረው የማስተርካርድ ፋውንዴሽን፣ 'ያንግ አፍሪካ ዎርክስ' (ወጣት አፍሪካውያን ይሰራሉ) ስትራቴጂ፣ በ2030 በኢትዮጵያ ለ10 ሚሊዮን ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር አቅዷል። ስትራቴጂው፣ ዲጂታል ቴክኖሎጂን በማጎልበት ስራ ፈጠራን ለማሳደግ ትኩረት ያደርጋል። በዚህ ስትራቴጂ ስር ያለው ቁልፍ ጅማሮ፣ እ.ኤ.አ. በ 2023 የተጀመረው ዘላቂ የፋይናንስ ተደራሽነት ለሥራ ፈጣሪነት (ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ.) የተሰኘው ፕሮግራም ነው። ይህ ፕሮግራም ከክፍያ ፋይናንሺያል ቴክኖሎጂ ጋር በመተባበር ከ2 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ወጣቶች ያለዋስትና የዲጂታል ብድር በመስጠትና የፋይናንስ ዕውቀት በማስጨበጥ የብድር ተደራሽነት መሰናክሎችን ለመፍታት ይጥራል።

ይህ ንጥል ጥናት፣ አዳዲስ የብድር ሞዴሎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ቁልፍ የፖሊሲ እና የተግባር ለውጦችን ይዳስሳል፣ በዘርፉ ውስጥ ባሉ ባለድርሻ አካላት ሊተገበሩ የሚችሉ የዘርፍ ግንዛቤዎችን አጉልቶ በማሳየት ወጣቶች በተለይም በሥራ ፈጣሪነት ወይም በንግድ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ ወይም ቀደም ብለው የተሰማሩ ወጣቶችን አካታች የፋይናንስ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ የሚቻልበትን መንገድ ለማሳየት ይሞክራል። ጥናቱ፣ ስኬትን የሚወስኑ ቁልፍ ሁኔታዎችን እና ሊተገበሩ የሚችሉ ትምህርቶችን በመመርመር አካታች የፋይናንስ አገልግሎቶችን መስጠት የሚያስችሉ መሣሪያዎችን እና የችግር አፈታት ዘዴዎችን ለማሳየት ይሞክራል።

ለዚህ ጥናት ቅይጥ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ስራ ላይ ውሏል። አንደኛ ደረጃ መረጃ የተሰበሰበው በቁልፍ መረጃ ሰጭ ቃለመጠይቆች እና የትኩረት ቡድን ውይይቶች ሲሆን ሁለቱም ዘዴዎች ስለ አመለካከቶች፣ የፖሊሲ ለውጦች እና ስነ-ምህዳራዊ ተለዋዋጭነት ግንዛቤ ለመጨበጥ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አስችለዋል። የፋይናንስ ዘርፉን የአሰራር ዝንባሌዎች እና ከዚህ የሚመነጩ ውጤቶችን በተጨባጭ ትንታኔ ለማሳየት ከተቋማዊ መዛግብት እና ተዛማጅ ጽሁፎች የተገኙ ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ጥቅም ላይ ውለዋል።

**የዚህ ንጥል ጥናት ዋና ግኝት የሚሽፍነው፣ በቅርቡ በኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ ውስጥ የታዩ የብድር ፖሊሲዎችና ተግባራት ለዉጦች አውድ፣ ስፋት እና አንድምታን ያጠቃልላል።**

**የኢትዮጵያ መንግስት አስቻይ የፖሊሲ ካባቢን በመፍጠር አካታች የሆነ ዘመናዊ ፋይናንስን በማስተዋወቅ ረገድ ቀዳሚውን ስፍራ ይዟል፡፡** ሀገራዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ፣ የፋይናንሺያል ሴክተር ማሻሻያ አጀንዳ እና ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025ን የመሳሰሉ አገራዊ የለውጥ ፖሊሲዎች ዘርፍ-ተኮር ለውጦችን ለማስተዋወቅ ጠንካራ መነሻ ይሆናሉ:: እነዚህ፣ ለውጥ ለማስተዋወቅ ከሚረዱ ስራዎች መካከል የብሔራዊ ዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ፣ የብሔራዊ የፋይናንስ ትምህርት ስትራቴጂ እንዲሁም የብሔራዊ አካታች የፋይናንስ ስትራቴጂዎች ይጠቀሳሉ:: የፋይናንሺያል ተቋማት ተገቢ መሳሪያዎችን እና አሠራሮችን ሲያስተዋውቁ ማበረታቻ፣ ድጋፍ እና ክትትል ተደርጓል። እንዲሁም መንግስት ተደራሽነትን ያሰፋሉ፣ ወጪን ይቀንሳሉ፣ ቀጣይነት ላለው አላማ-ተኮር ብድር እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮችን ይቀንሳሉ በሚል ያወጣቸውን መመሪያዎች የሚያከብሩ ተቋማትን ያበረታታል።

**የልማት አጋሮች እና ደጋፊ ተዋናዮች፣ ዘርፉን ማዘመንንና አቃፊ የብድር ሞዴሎችን መጠቀምን የማይቀር ጉዳይ ወደ መሆን እየወሰዱት ነው።** ማስተርካርድ ፋውንዴሽን የቴክኒክ ድጋፍና በህዝብና በግለሰቦች መካከል ውይይት በማዘጋጀት እገዛ ከሚያደርጉ አካላት አንዱ ነው፡፡ ሌላው ፋውንዴሽኑ ከሚያደርጋቸው ድጋፎች ውስጥ የሚጠቀሰው ተቋማቱ ለአደጋ ተጋላጭነትን በማስወገድ ወደ አዳዲስ ሞዴሎች አጠቃቀም እንዲሸጋግሩ ዘዴዎች ማሳየት አንዱ ነው:: የልማት አጋሮች እገዛ - የ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. ፕሮግራምን ጨምሮ ማለት ነው፡፡ ከቀድሞው የመንግስት እርምጃዎች ጋር የተጣጣሙ እና በዛ ላይ የሚያክሉ ናቸው፡፡

**የ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. ፕሮግራም ሞዴል፣ ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች በፋይናንስ ዘርፉ ተዋናዮች እና ፖሊሲ አውጪዎች ዘንድ ይበልጥ በበጎ እንዲታዩ አስተዋጽኦ አድርጓል።** እነዚህ ወጣቶች በአሁኑ ጊዜ ብድር የሚገባቸው ደንበኞች እና የስራ እድል ፈጠራ ቁልፍ ተዋናዮች ተደርገው ይወሰዳሉ። በተመሳሳይ፣ ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ስለባንኮች ያላቸውን ግንዛቤ በማሻሻል ተጨማሪ የፋይናንስ ዕድሎችን ለመፈተሽ ጉጉ እንዲሆኑ አድርጓል።

**የ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. አጋር ባንኮች ያስተዋወቋቸው የፖሊሲና የተግባር ለውጦች፣ ለወጣት ስራ ፈጣሪዎች ብድር መስጠትን በሚመለከት የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ አስተዋፅዖ አድርገዋል፤ አጋር ያልሆኑ ባንኮችም በአሰራራቸው ላይ ተመሳሳይ ለውጦችን እንዳደረጉ ይገልጻሉ።** አጋር ባንኮችም የግብይት ታሪክ፣ የባህሪ ታሪክ እና ባህላዊ የብድር ውጤት የመሳሰሉ መረጃዎችን በመጠቀም የውስጥ ብድር ግምገማ ሂደታቸውን አስተካክለዋል። እነዚህ ባንኮች በዋስትና ላይ ብቻ ከተመሰረተ ብድር፣ በመረጃ ወደ ተደገፈ የብድር አሰጣጥ እየተሸጋገሩ ነው፤ በዚህም የተነሳ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም የብድር ግምገማ ለማካሄድ ሰው ሰራሽ አስተውሎት እና ሌሎች ዲጂታል አውታሮችን መጠቀም ግድ ሆኗል[4]።

አጋር ባንኮችም ወቅታዊ የመረጃ ትንተና ማካሄድ እንዲችሉ የብድር ስጋት አስተዳደር ስርአቶችን በማሳደግ ላይ ይገኛሉ፤ ይህንንም የሚያደርጉት ለዚህ ብቻ የታሰቡ ዲጂታል የብድር

[4] ይህ ፕሮገራመ የሚሰጠው የብድር ዋስትና የተበዳሪዎችን የብድር ዋስትና የማቅረብ ሸክም ያቀልላቸዋል፡፡ በተጨማሪም አበዳሪዎች፣ ዘመናዊ የብድር ግምገማ መሳሪያዎችን እንዲፈትሹ ዥድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ባንኮች በተግባር የተደገፈ ልምድ በማዳበራቸውና በሰው ሰራሽ አስተውሎት የተደገፈ ግምገማ የማካሄድ ብቃታቸው እየጨመረ ስለመጣ፣ ወጣት ተበዳሪዎችና ጠ.አ.መ.ኢ. እምነት የሚጣልባቸው መሆናችውን እየተቀበሉ ነው፤ በዚህም የተነሳ፣ ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን የሚሰጠውን ድጋፍ ቀስ በቀስ እየቀነሰ መጥቷል፡፡

መምሪያዎችን በማቋቋም እና የምርት አቅርቦት አማራጮችን በማስፋት ነው። በነዚህ ዘርፎች፣ የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ ፈጠራውን በመምራት ላይ ይገኛል። ለዚህ ስኬትም የበቃው፣ ሚቹ፣ ዲጂታል የብድር ምርቶቹን በማስተዋወቁ፣ እንዲሁም በገጠር ላሉ ወጣት ሴቶች የመሳሪያ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ በማመቻቸቱ፣ በ2025 (እኤአ) መገባደጃ ላይ የሚጀመረውን በሒሳብ መጠየቂያ የሚከናወን የፋይናንስ አሰራር አስመልክቶ ከ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ ጋር ትብብሩን በማሳደጉ ነው። በተጨማሪም ብዙ ባንኮች፣ የጥ.አ.መ.ኢ. የብድር መረጃ ክምችታቸውን እያሳደጉ ይገኛሉ፤ በዚህ ረገድ፣ ኦ.ሕ.ሥ.ባ. ክፍያን በሚመለከት ጉልህ የሆነ ጭማሪ ያደረገ ባንክ ሆኗል።

**አጋር ባልሆኑ ተቋማት ዘንድ የፖሊሲ እና የተግባር ለውጦች ለመኖራቸው ማሳያዎች አሉ።** ኦ.ሕ.ሥ.ባ.፣ ‘ሚቹ’ የተባለውን አገልግሎቱን መጀመሩን ተከትሎ ኢትዮ ቴሌኮም ከዳሽን ባንክ እና ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በመተባበር ጥቃቅን የዲጂታል ብድር አገልግሎቶችን አስተዋውቋል። ይህን ተከትሎ፣ እንደ ዳሽን ባንክ፣ (ዱቤ ፔይ)፣ አቢሲኒያ ባንክ (አፖሎ) እና አንበሳ ባንክ (አለኝታ) ያሉ ተቋማት የራሳቸው የሆነ አሰራር በማስተዋወቃቸው የገበያ ውድድሩ እንዲቀጣጠል ሆኗል። በተጨማሪም SNV፣ KMD ለንደን ጋር በመተባበር ዲጂታል የብድር መተግበሪያ በአዋሽ ባንክ፣ ንግድ ባንክ እና አሃዱ ባንክ በኩል ለመክፈት እየሰራ ይገኛል።

**የፋይናንስ ተቋማት በመረጃ ላይ የተመሰረተ፣ የዲጂታል ብድር አሰጣጥን ሊተገብሩ ይችላሉ። ይህ አሰራር ጠንካራና አካታች ትብብር ለመፍጠር መሰረት ይሆናል፤ የቁጥጥር ማሻሻያ እንዲደረግም ማንቂያ ሊሆን ይችላል።** አካታች የፋይናንስ ፕሮግራሞችን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ፣ ፖሊሲ አውጪዎች ለተለያዩ የፋይናንስ አቅራቢዎች ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እና የፋይናንስ እውቀት ማጎልበት ላይ ቅድሚያ ሰጥተው መስራት ይጠበቅባቸዋል። የፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢዎች በበኩላቸው፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራ እና የንግድ አሰራር ለውጦችን በማካተት እነዚህን ማሻሻያዎች በሰፊው ጥቅም ላይ ማዋል ይገባቸዋል። የልማት አጋሮች ደግሞ የአሰራር ሽግግር እንዲመጣ ማስቻል እና አዳዲስ ሞዴሎች በስፋት ስራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። እነዚህ ግኝቶች አካታች የሆኑ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለማስፋፋትና በተለያዩ አውዶች ውስጥ ያሉ ጥ.አ.መ.ኢ.ን ለማጠናከር እንደ ፍኖተ-ካርታ ሊያገለግሉ ይችላሉ። ከዚህ በታች የቀረበው ማጠቃለያ፣ በጥናቱ የተገኙ ግንዛቤዎችና ተግባራዊነታቸው ከባለድርሻ አካላት አንጻር ምን እንደሚመስል ያሳያል።

| ግንዛቤዎች | ትግበራ |
|---|---|
| | **ፖሊሲ አውጪዎች** |
| የማበደር ፈቃድን ለባንኮች ብቻ መስጠት ሰፊ የሆነ፣ ሁሉን አቀፍ የብድር አሰጣጥ እድገትን ይገድባል:: | **አካታች የቁጥጥር ማዕቀፎችን ማዘጋጀት**፡- ከባንክ ዉጪ ያሉ የፋይናንስ ተቋማት፣ (NBFIs) አካታች የሆነ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ ማስቻል:: |
| በተለይ በገጠር አካባቢዎች የሚስተዋሉ የፋይናንስ እውቀት ክፍተቶች፣ አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች ውጤታማ የሆነ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ እንቅፋት ይሆኑዋቸዋል:: | **አጠቃላይ የመሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራሞችን መተግበር**: ግለሰቦች እና የንግድ ተቋማት የዲጂታል ፋይናንስ መሳሪያዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲረዱ እና እንዲጠቀሙ ማበረታታት:: ይህ የህዝብ ግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን፣ የትምህርት ግብዓት ማሟላትን እና ወጣቶች ላይ ያተኮረ መሰረታዊ የፋይናንስ ግንዛቤ ስልጠና መስጠትን ያጠቃልላል:: |
| በጋራ መስራት እና እውቀት መጋራት፣ ወጣት ሠራተኞችን ተጠቃሚ ማድረግ ላይ የሚያተኩሩ ፈጠራዎችን ያሳድጋል:: | **የትብብር መድረኮችን ማሳደግ**: በፖሊሲ አውጪዎች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ ፊንቴክስ እና ሌሎች በዘርፉ ዉስጥ ያሉ ተዋናዮች መካከል ያለውን አጋርነት ማሳለጥ፤ በዲጂታል ብድር ዙርያ ዕዉቀትንና ፈጠራን ማፋጠን ይቻል ዘንድ ነጻ የልምድ ልውውጥን ማበረታታት። |
| | **የልማት አጋሮች** |
| ፈጠራ፣ ዘላቂና ለሁሉም ሊዳረስ የሚችል ለውጥ ያመጣል:: | **በቴክኖሎጂ የታገዘ ፈጠራን መደገፍ**:<br>ተደራሽነትን የሚያሰፉ እና ወጣቶች፣ በተለይም ወጣት ሴቶች ያሉባቸውን ማነቆዎች በወሳኝ ደረጃ የሚፈቱ ዲጂታል መፍትሄዎች ላይ መዋእለ ንዋይ ማፍሰስ:: |
| ለብዙሓኑ ሊዳረሱ የሚችሉና ዘላቂነት ያላቸው ሞዴሎች ሰፊ ለውጥ ያመጣሉ:: | **ሥር-ነቀል መፍትሄዎችን በገንዘብ መደገፍ**: የፋይናንስ አካታችነት እንቅፋቶችን የሚያስወግዱ፣ ዘርፎችንና ሥነ-ምህዳሮችን በወሳኝነት የሚቀይሩ፣ ከአንድ መርሃ-ግብር የሕይወት ዑደት በላይ የሚዘልቁ ጅምሮችን መደገፍ። |
| ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረግ ትብብር የጋራ ጥቅሞችን ይፈጥራል። | **ጠንካራ አጋርነት መፍጠር**: ከፋይናንስ ተቋማት፣ ፖሊሲ አውጪዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት እና ትብብርን ማመቻቸት:: |
| ድጋፍ መስጠት ላይ የሚያተኩሩ ቁጥጥሮች፣ በዝቅተኛ ደረጃ አገልግሎት ገኙ የነበሩ ቡድኖች ተጠቃሚነታቸው እንዲሰፋ ያደርጋሉ:: | **ቁጥጥር ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ መሟገት**፡- አካታች ፋይናንስን ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንድ ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ከፖሊሲ አውጪዎች ጋር መመካከር:: |
| | **የፋይናንስ ተቋማት** |
| ጥ.አ.መ.ኢ. ትርፋማ እና አዋጭ ገበያ ናቸው:: | **ጠንካራ የዲጂታል መሰረት መገንባት**: በተጠቃሚ ምርቶች፣ በአስፈላጊ መሠረተ ልማት፣ በመረጃ ሳይንስ እና በጠንካራ የሳይበር ደህንነት ላይ መዋእለ ነዋይ ማፍሰስ። |
| ደንበኛን ያማከለ ፈጠራ የእድገት ቁልፍ መሪ ነው:: | **ደንበኛን ያማከሉ መፍትሄዎችን ማዘጋጀት**: በልክ የተዘጋጁ የፋይናንስ አገልግሎቶችን መፍጠር እና የፋይናንስ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራሞችን ማቅረብ:: |
| ዲጂታል አውታሮች፣ የአሰራር ቅልጥፍናን እና የገበያ ተደራሽነትን በእጅጉ ያሳድጋሉ:: | **ፈጠራን እና የአሰራር ቅልጥፍናን መምራት**: የምርምርና ልማት ቡድኖችን ማቋቋም፤ ብድርን እና የተበዳሪዎች መረጃ አሰባሰብን ዲጂታል ማድረግ፣ ብድር አሰጣጥና አመላለስን ከፍ ወዳለ ደረጃ ማድረስ |

# 1. መግቢያ

## 1.1. ዳራ እና አውድ

የወጣቶች ስራ አጥነት በመላው አፍሪካ ትልቅ ፈተና ነው። በ2025 ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት የወጣቶች ስራ አጥነት 8.9 በመቶ እንደሚደርስ ዓ.ሥ.ድ. ተንብዮዋል[5]። ይሁን እንጂ ውጤታማ እና የሚያኖር ሥራ አለመኖሩ ከሰሃራ በታች ላሉ የአፍሪካ ሀገራት ዋነኛው ፈተና እንደሆነ ቀጥሏል። በ 2023 ብቻ ሥራ፣ ትምህርት እና ስልጠና የሌላቸው ወጣቶች ቁጥር 21.9% ነበር[6]። በዓመት ከሁለት ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያን ወደ ሥራ የሚገቡ ቢሆንም ኢኮኖሚው ይሄን ለማስተናገድ ይቸገራል።

ሥራ አጥነትን ለመቅረፍ፣ ድህነትን ለመቀነስ እና የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማፋጠን የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች (ጥ.አ.መ.ኢ.) ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በአፍሪካ ውስጥ፣ ጥ.አ.መ.ኢ. 90% የንግድ ሥራዎችን ያቀፉ ሲሆን ከ60% በላይ የሥራ ዕድልን ይፈጥራሉ[7]። በኢትዮጵያ፣ ወደ 1.5 ሚሊዮን የሚጠጉ ጥ.አ.መ.ኢ. 4.5 ሚሊዮን የሥራ ዕድል የፈጠሩ ሲሆን፣ ወርሃዊ ገቢያቸው 40.7 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ይገመታል[8]።

ሆኖም ግን፣ የእነዚህ ኢንተርፕራይዞችን እምቅ ችሎታ የሚገድቡ ከፍተኛ የገንዘብ ችግሮች አሉባቸው። ከእነዚህ ቁልፍ እንቅፋቶች መካከል፣ የፋይናንስ አቅርቦት ውስንነት፣ በቂ ያልሆነ የፖሊሲ ድጋፍ፣ በመደበኛ የፋይናንስ አገልግሎት ሰጪዎች ዘንድ ለኢንተርፕራይዞቹ ያለው ዝቅተኛ እምነት እና የፋይናንስ እውቀት ውስንነት ናቸው። በተለምዶ 'የጠፋው መካከለኛ' ተብለው የሚጠሩት አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በተለይ ተጎጂዎች ናቸው። ትናንሽ፣ ጀማሪ ድርጅቶች ከትላልቅ ኢንተርፕራይዞች ይልቅ የብድር ጥያቄያቸው ውድቅ የመሆን እድሉ ሰፊ ሲሆን የትላልቆቹ የካፒታል ፍላጎት በመደበኛ ማይክሮ ፋይናንስ በኩል ከሚመደበው የበለጠ ነው።

የኢትዮጵያ ሥራ ፈጠራ ኮሚሽን ሪፖርት (2020) እንደሚያመለክተው 1.9 በመቶ የሚሆኑት ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ብቻ የፋይናንስ አቅርቦት ያገኛሉ፤ ይህ ቁጥር ከኢንተርፕራይዞቹ 6% በታች ነው። ይህም በገንዘብ በኩል የሚያጋጥማቸውን ችግር ክብደት ያሳያል።

በአፍሪካ የወጣቶች የስራ እድል ፈጠራ ላይ ያለውን ጉልህ ፈተና በመገንዘብ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን በ2018 'ወጣት አፍሪካውን ይሰራሉ' (Young Africa

> **ያለዋስትና የሚሰጥ ዲጂታል ብድር:** ማለት ከተበዳሪው መያዣ ሳያስፈልግ ብድር የሚሰጥበት የአሰራር አይነት ነው።
>
> በዘህ የብድር አሰጣጥ አይነት፣ ተበዳሪው ለብድር ብቁ መሆን አለመሆኑ የሚከተሉትን አማራጮች መሰረት በማድረግ ይገመገማል፡- የተበዳሪው የብድር ውጤት፣ የግብይት ታሪክ እና ሌሎች ዲጂታል አሻራዎች ግምት ውስጥ ይገባሉ።
>
> ከባህላዊ የብድር አሰጣጥ ዘዴዎች ጋር ሲነጻጸር፣ ይህ ዘዴ የብድር ሂደቱን ለማሳለጥ እና ፈጣን ውሳኔ ለመስጠት ቴክኖሎጂንና ኢንተርኔትን በማጣመር ይጠቀማል (Zhang, 2021) ።
>
> ኪፌያ ቴክኖሎጂ፣ በአስርት አመታት ጉዞው፣ ጥ.አ.መ.ኢ. ፋይናንስ እና ብድር ለማግኘት ለሚገጥሟቸው የፍላጎት፣ የአቅርቦት እና አካባቢያዊ ተግዳሮቶች ወቅታዊ መፍትሄዎችን ሲሰጥ ቆይቷል።

[5] Sub-Saharan Africa GET Youth 2024_0.pdf
[6] CSA 2018
[7] ITC 2018
[8] Ababiya, 2018; Kassa, 2021

Works) በሚል መርህ ስትራተጂ ነድፎ ስራ ጀምሯል። ይህ ጅማሮ፣ በአህጉሪቱ ያሉ 30 ሚሊዮን ወጣቶች (70 በመቶው ወጣት ሴቶች ናቸው) በ2030 የሚያኖር ስራ እንዲኖራቸው ለማስቻል አልሟል። በኢትዮጵያ፣ ያንግ አፍሪካ ዎርክስ በ2019 ለ10 ሚሊዮን ወጣቶች የስራ እድሎችን በመፍጠር እንቅስቃሴ ጀመረ። ይህ ስትራቴጂ የፋይናንስ፣ የትምህርት እና የክህሎት ተደራሽነትን በማሳደግ ሁሉን አቀፍ እድገት ለማምጣት ያለመ ሲሆን ዲጂታል ቴክኖሎጂን በስፋት በመጠቀም፣ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን በመደገፍ፣ ሥራ ፈጣሪነትን በማሳደግ እና ስትራቴጂያዊ አጋርነቶችን በመገንባት አላማውን ከግብ ለማድረስ ይጥራል።

## 1.2. የንጥል ጥናቱ ዓላማዎች

ይህ ንጥል ጥናት ሶስት ዋና ዋና አላማዎች አሉት። የመጀመሪያው ዓላማ፣ አዳዲስ የብድር አሰጣጥ ዘዴዎች፣ (በተለይም የወጣቶችን ፍላጎት ያማከሉ፤ ያለዋስትና የሚሰጡ የዲጂታል የብድር አገልግሎቶች) እውን እንዲሆኑ ያስቻሉ፣ የፖሊሲና እና የአሠራር ለውጦችን መለየት ነው። ሁለተኛው ዓላማ፣ ያለዋስትና የሚሰጥ የብድር ሞዴል ውጤታማነትን ይመረምራል፤ ይህን ለማሳካትም ለሞዴሉ ውጤታማነት አስተዋጽኦ ያበረከቱትን ወሳኝ የስኬት ሁኔታዎች ይዳስሳል። በመጨረሻም፣ ለሌሎች መሰል ተነሳሽነቶች አስተማሪ ሊሆኑ የሚችሉ ተስፋ ሰጭ ተግባራዊ ትምህርቶችን ለይቶ ለማውጣት ይሞክራል።

## 1.3. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ይህ ንጥል ጥናት ቅይጥ (ዓይነታዊና ቁጥራዊ) የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ይጠቀማል። የፖሊሲ ለውጦችን፣ የብድር አሰጣጥን እና የሥነ-ምህዳር ተለዋዋጭነትን ለመለየት አይነታዊ መረጃን ሲጠቀም፣ ሊለኩ የሚችሉ ውጤቶችን እና አዝማሚያዎችን ለማሳየት ቁጥራዊ መረጃዎችን ይጠቀማል። የመረጃ ምንጮቹም ቁልፍ የመረጃ ሰጭ ቃለመጠይቆች፣ የትኩረት ቡድን ውይይቶች፣ ተቋማዊ መረጃዎች፣ የፕሮግራም ሰነዶች እና ተዛማጅ ሥነ-ጽሑፎች ናቸው።

## 1.4. የንጥል ጥናቱ መዋቅር

ይህ ጥናት በሰባት ክፍሎች የተከፈለ ነው። ክፍል አንድ የጥናቱን ዳራ፣ ዓላማዎች እና ዘዴ ያስተዋውቃል። ክፍል ሁለት የኢትዮጵያን የፋይናንስ ዘርፍ አጠቃላይ እይታ ያቀርባል። ክፍል ሶስት የጥ.አ.መ.ኢ.ን ተግዳሮቶች እና ዕነዚህን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ የተከናወኑ ጅማሮዎችን ይመረምራል። ክፍል አራት ያለዋስትና የሚሰጥ የዲጂታል ብድር ሞዴል የኪሬያ አሰራርን በጥልቀት ያብራራል። ክፍል አምስት እና ስድስት የፖሊሲ እና የተግባር ለውጦችን፣ አስቻይ ሁኔታዎችን እና የእነዚህን አንድምታዎች ይተነትናል። በመጨረሻም ክፍል ሰባት ወደፊት ስራ ላይ የሚውሉ መተግበሪዎች በማቅረብ ያለዋስትና የሚሰጥ የዲጂታል ብድር ሞዴሎችን ለማላመድ እና ለመቀበል የሚያስችሉ ተሞክሮዎችን ያቀርባል። ክፍል ሰባት ከዋስትና ነፃ የሆኑ የዲጂታል ብድር ሞዴሎችን ለወደፊቱ እንዳመቺነታቸው እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ትምህርት ይሰጣል።

# 2. የኢትዮጵያ የፋይናንስ ሴክተር አውድ

## 2.1. የማክሮ ኢኮኖሚያዊ አጠቃላይ እይታ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በ2022/2023 7.2 በመቶ እድገት በማስመዝገብ ከሰሃራ በታች ካሉት የአፍሪካ ሀገራት አማካይ ብልጫ አሳይቷል[9]። ግብርናው ቁልፍ ሴክተር ሆኖ ከፍተኛ የህብረተሰብ ክፍልን በመቅጠር እና ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያበረከተ የቆየ ቢሆንም መንግስት ለአምራች እና አገልግሎት ዘርፉ ቅድሚያ ሰጥቶ በማስፋፋት ኢኮኖሚውን በማሳደግ ላይ ይገኛል። እ.ኤ.አ. በ 2023 እነዚህ ዘርፎች ጠንካራ እድገት አሳይተዋል፣ ግብርና በ 6.3%፣ ኢንዱስትሪ በ 6.9%፣ እና አገልግሎቶች በ 7.9% እድገት ያሳዩ ሲሆን ለአገሪቷ ኢኮኖሚ ደግሞ እንደቅደም ተከተላቸው፣ የ32.1%፣ 28.8% እና 40.3% አስተዋፅኦ አድርገዋል። ይህ እድገት እንዳለ ሆኖ፣ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የማክሮ ኢኮኖሚ ተግዳሮቶች አጋጥመዋታል፤ የዋጋ ግሽበት (26.11%)፣ የወጣቶች ስራ አጥነት (23.1%)፣ የበጀት ጉድለት (ከጠቅላላ ሀገራዊ ምርት አንጻር 2.9%) ደርሷል። በአንጻሩ፣ የመንግስት ብድር ከፍተኛ ደረጃ (USD 63.2 ቢሊዮን፣ 38.7 በመቶ የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት) የደረሰ ሲሆን የንግድ ጉድለቱም (USD 13.5 ቢሊዮን) ከፍተኛ የሚባል ነው[10]።

## 2.2. የፋይናንስ ዘርፍ ስነ-ምህዳር ተዋናዮች

**ምስል 1፡ የፋይናንስ ዘርፍ ስነ-ምህዳር ተዋናዮች**




[9] NBE 2022/23

[10] https://nbe.gov.et/files/annual-report-2022-2023-2/

የኢትዮጵያ የፋይናንስ ስነ-ምህዳር እርስ በርስ የተሳሰሩ ተዋናዮችን ያቀፈ ሲሆን በኢትዮጵያ አካታች የፋይናንስ አሰራርን እና መረጋጋትን ለማጎልበት እነዚህ አስተዋጽያዋቸው ከፍተኛ ነውው፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ (ኢ.ብ.ባ.)፣ እንደ ማዕከላዊ ባንክነቱ፣ የፖሊሲ አቅጣጫ በማስቀመጥ፣ የፋይናንስ ተቋማትን በመቆጣጠርና የዘርፉን አጠቃላይ ጤናማነት በማረጋገጥ ወሳኙን የቁጥጥር ሚና ይጫወታል፡፡ ብሔራዊ ባንክ ፋይናንሺያል ቴክኖሎጂ (ፊንቴክ) ስራ ላይ እንዲውል በማድረግ፣ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶችን በማስፋፋት እና ተደራሽነትንና የአሰራር ቅልጥፍናን በማሳደግ ተግቶ ይሰራል፡፡ ይህን ለማሳካትም እንደ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር (ኢ.ቴ.ሚ.) ካሉ የመንግስት አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡ የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን በበኩሉ የካፒታል ገበያ ልማትን በበላይነት የሚቆጣጠር ሲሆን የብድር ማጣቀሻ ቢሮ ደግሞ የብድር መረጃ ተደራሽ የማድረግ ስራ በመስራት በመረጃ የተደገፈ የብድር ውሳኔ አሰጣጥ እንዲኖር አጋዥ ሚና ይጫወታል፡፡

ባንኮች፣ በዘርፉ የካፒታል እና የብድር መረጃ ክምችት/ፖርትፎሊዮ አሰባሰብ ቀዳሚ ተዋናዮች ናቸው፣ ባህላዊ የባንክ አገልግሎት እየሰጡ ቢሆንም የዲጂታል አሰራር ለውጥ/ትራንስፎርሜሽን እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ከፊንቴክ ኩባንያዎች ጋር በመተባበርና አዳዲስ መፍትሄዎችን በማስተዋወቅ ደንበኞቻቸውን ለማበራከት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ የጥቃቅን ፋይናንስ ተቋማት፣ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በበቂ ሁኔታ ለማያገኙ፣ በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ግለሰቦች እንዲሁም ጥ.አ.መ.ኢ.ን በማገልገል ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የፊንቴክ/የፋይናንስ ቴክኖሎጂ ኩባንያዎች፣ ተደራሽ እና ቀልጣፋ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ከሁለቱም ባንኮች እና ከማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ጋር ይተባበራሉ፡፡ ይህን ሲያደርጉ እነዚህ ኩባንያዎች በባህላዊ እና ዲጂታል ፋይናንስ መካከል ያለውን ልዩነት ያስተካክላሉ፡፡

እንደ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ያሉ የልማት አጋሮች ለመንግስት ተቋማት እና የፋይናንስ ተቋማት የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡ ይህን በማድረግም ለአካታች ፋይናንስ ቅድሚያ የሚሰጡ የአቅም ግንባታ እና የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞችን ያበረታታሉ፡፡

> ባንኮች፣ MFIs፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ የቁጠባ ድርጅቶች እና የብድር አገልግሎት ሰጪዎች የፋይናንስ ሴክተሩን በበላይነት ይቆጣጠራሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ 32 ባንኮች ከበርካታ የጥቃቅን ፋይናንስ እና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ጎን ለጎን በዚህ ረገድ ጉልህ ሚና የሚጫወቱ ሲሆን ባንኮች ከጠቅላላው የፋይናንስ ዘረፍ ሀብት 96 በመቶውን ተቆጣጥረዋል፤ እስከ ሰኔ 2024 ድረስ ይህ መጠን 3.4 ትሪሊዮን (29.5% የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት) ብር ደርሷል
>
> የፊንቴክ ኩባንያዎች የመረጃና የቴክኖሎጂ መፍትሄዎችን እንጂ የብድር አገልግሎት አይሰጡም፣ በፋይናንስ ዘርፍ ደንብ መሰረት እነዚህ አገልግሎቶች ለባንኮች እና ለሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ብቻ የተፈቀዱ ናቸው፡፡

የእነዚህ የትብብር ጥረቶች የመጨረሻ ተጠቃሚዎች ጥ.አ.መ.ኢ. ናቸው፡፡ ምክንያቱም የፋይናንስ ተደራሽነት ከተሻሻለ እነዚህ ኢንተርፕራይዞች የስራ እድል እንዲፈጥሩ ብሎም የኢኮኖሚ እድገት እንዲያስመዘግቡ አቅም ይፈጥርላቸዋል፡፡ ተቆጣጣሪዎች፣ የመንግስት ተቋማት፣ የፋይናንስ ተቋማት እና የልማት አጋሮች በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ጥ.አ.መ.ኢ. ያላቸውን ወሳኝ ሚና በመገንዘብ እድገታቸውን የሚያፋጥንና የፋይናንስ አካታችነትን የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በጋራ ይሰራሉ፡፡

# 3. የጥ.አ.መ.ኢ. ተግዳሮቶች እና እድሎች አጠቃላይ እይታ

## 3.1. ጥ.አ.መ.ኢ. ለኢኮኖሚ ዕድገት ያላቸው አስተዋፅያ

በዓለም ዙሪያ ጥ.አ.መ.ኢ የምንመድብበት ዘዴ የተለያየ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ምደባዎች የሰራተኛ ብዛትን እና አመታዊ ካፒታልን መሰረት ያደርጋሉ። በኢትዮጵያ የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ብያኔ መሰረት እስከ 100 የሚደርሱ ሰራተኞችን የሚቀጥሩ እና አመታዊ ካፒታላቸው እስከ 7.5 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር የሆኑ ኢንተርፕራይዞች ጥ.አ.መ.ኢ. ተብለው ይመደባሉ። ጥ.አ.መ.ኢ. የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት በመሆናቸው የነሱ ስኬት እጅግ ወሳኝ ነው፤ የስራ እድል በመፍጠር እና የኢኮኖሚ እድገትን በማነቃቃት ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ።

**ሠንጠረዥ 1: የጥ.አ.መ.ኢ. አመዳደብ**

| *ዘርፍ* | ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች | | አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች | | መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አገልግሎቶች | ኢንዱስትሪ | አገልግሎቶች | ኢንዱስትሪ | አገልግሎቶች | ኢንዱስትሪ |
| *ተቀጣሪዎች* | ≤ 10 | ≤ 10 | 11-50 | 11-50 | 51-100 | 51-100 |
| *ካፒታል (በሺህ ብር)* | <50 | <100 | 501-500 | 101-1,500 | 501-7,500 | 1,501-7,500 |

ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ በኢትዮጵያ ወደ 2 ሚሊዮን የሚጠጉ ጥ.አ.መ.ኢ. አሉ[11]። ይሁን እንጂ፣ በሀገሪቱ ያለው የወጣቶች ስራ አጥነት ከፍተኛ ሲሆን በ 2018 24.95% ደርሷል፤ በተለይ የሴቶች ሥራ አጥነት በ 30.9%[12] ከፍተኛ ሊባል የሚችል ነው። ጥ.አ.መ.ኢ ሥራ በማመንጨት ይህን ሁኔታ ሊቀይሩ ይችላሉ። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ጥ.አ.ኢ. በኢትዮጵያ 70% የሚሆነውን የስራ እድል የሚሸፍኑ ናቸው[13]። ይህም የሀገሪቱን የስራ አጥነት ፈተናዎች በመቅረፍ፣ የድህነት ቅነሳ ጥረቶችን በመደገፍ እና ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ልማትን በማጎልበት የማይተካ ሚና ሊኖራቸው እንደሚችል በግልፅ ያሳያል።

## 3.2. ጥ.አ.መ.ኢ. ያጋጠሟቸው ተግዳሮቶች

ለጥ.አ.መ.ኢ ዋነኛ ተግዳሮት የብድር አቅርቦት ውስንነት ሲሆን ይህም እድገታቸውን እና በኢኮኖሚው ውስጥ ያላቸውን እምቅ አስተዋፅያ የሚገድብ ነው። የባንክ ብድር በዋነኛነት የሚያተኩረው ዋስትና ማስያዝ በሚችሉ ትልልቅ የድርጅት ተበዳሪዎች ላይ ሲሆን ጥ.አ.መ.ኢ. በዋነኝነት የሚገለገሉት በማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት (MFIs) ነው።

በመላው አህጉር፣ መደበኛ የሆኑ ጥ.አ.መ.ኢ. ከ330 ቢሊዮን ዶላር በላይ የሚገመት የፋይናንስ ክፍተት አጋጥሟቸዋል። በኢትዮጵያ ብቻ በ2021 የአ.መ.ኢ. የገንዘብ ድጋፍ ክፍተት 6.1 ቢሊዮን ዶላር ደርሷል[14]።

---

[11] UNDP, 2022
[12] CSA, 2018
[13] Abate, et al., 2023
[14] World Bank, 2024

ይህ የሚያሳየው የችግሩን ክብደት ነው። እ.ኤ.አ. በ 2021 ዩኤንዲፒ *'አካታች እና ዘመናዊ ፋይናንስ ለልማት'* በሚል ርዕስ ያወጣው ሪፖርት እንደሚያሳየው ከኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዞች መካከል እጅግ ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው መደበኛ ፋይናንስ ማግኘት የሚችሉት፤ ይህ ማለት ከአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ውስጥ 1.9 በመቶው ብቻ መደበኛ ብድር ወይም የችግር መፍቻ ፈጣን የብድር አማራጮች ያገኛሉ። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ብድር የማግኘት ዕድል ከንግዱ ግዝፈት ጋር በሆነ መልኩ ይቆራኛል። በመሆኑም፣ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች 6%፣ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች 20.5%፣ ትላልቅ ኢንተርፕራይዞች 35.5% ብድር የማግኘት እድል አላቸው። ትናንሽ ንግዶች በተለየ ሁኔታ ዝቅተኛ የሚባል አገልግሎት ያገኛሉ። ይህ የብድር አቅርቦት ችግር በተለይ መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ ሴቶች እና ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች በጣም አሳሳቢ ነው።

**ምስል 2: የጥ.አ.መ.ኢ. ተግዳሮቶች**

| ከፍላጎት ጋር የሚያያዙ ተግዳሮቶች | ከአቅርቦት ጋር የምያያዙ ተግዳሮቶች |
|---|---|
| በተበዳሪው ስም የተመዘገበ ማስያዣ አለመኖር፤ የቋሚ ንብረት እጥረት | በቂ ያልሆነ የአደጋ ግምገማ መሳሪያዎች - አደጋን ለመቆጣጠር በዋስትና ላይ መተማመን። |
| መደበኛ ንግድ አለማካሄድ፣ ደካማ የብድር ታሪክ እና የፋይናንስ መረጃን መዝግቦ አለመያዝ። | አግባብነት ያላቸው፣ ተስማሚ የፋይናንስ አገልግሎቶች እጥረት |
| በወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ዘንድ መሰረታዊ የፋይናንስ እውቀት እና ግንዛቤ ዝቅተኝነት | አነስተኛ መጠን ያለው፣ ለብድር የሚውል ገንዘብ በቀጣይነት ለማግኘት፣ ለማስተዳደርና፣ ለተጠቃሚ ለማቅረብ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ መሆኑ። |
| የተበዳሪው መረጃ ባለመኖሩ ስለሽያጭ ሁኔታ መረጃ አለማግኘት - በተለይም ወጣት ሴቶችን በሚመለከት። | ለጥ.አ.መ.ኢ. ብድር መስጠት ከፍተኛ ስጋት ላይ ይጥላል ብሎ ማሰብ። |
| የመበደር አቅም ያላቸው በተንዛዛ የማመልከቻ ሂደት መደናቀፋቸው | ገንዘብ ለማግኘት የሚያጋጥሙ ማነቆዎች |
| | የዲጂታል መሠረተ ልማት እጦት፣ በገጠር አካባቢዎች ውስን ቅርንጫፎች መኖር |
| **ከአስቻይ ከባቢ ጋር የሚያያዙ ተግዳሮቶች** | |
| የብድር መረጃ መሠረተ-ልማት እጥረት፣ ውጤታማ የብድር ቢሮዎች እና የመረጃ ማጋሪያ ዘዴዎች አለመኖር። | |
| ፈቃድ አሰጣጥና አዳዲስ የፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢዎች ወደ ሥራ እንዳይገቡ የሚያደርጉ ማነቆዎች መኖር። | |
| የዲጂታል ክፍያ መሠረተ ልማት እና የመታወቂያ ስርዓት ውስንነቶች | |
| በጾታ እና በእድሜ የተከፋፈለ የፋይናንስ ዘርፍ መረጃ እጥረት። | |
| ወጣቶች የአካታች ፋይናንስ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚገድቡ ባህላዊ እና ማህበራዊ ልማዶች | |

የጥ.አ.መ.ኢ. ብድር ተደራሽነት ችግሮች ከፍላጎት እና አቅርቦት በኩል የሚመነጩ ናቸው፤ ከፍላጎት በኩል ካየነው ችግሮቹ ጥ.አ.መ.ኢ. - ተኮር ጉዳዮች ሲሆኑ ፣ ከአቅርቦት በኩል ደግሞ በፋይናንስ ተቋማት ውስጥ ያሉ ማነቆዎች ናቸው። ከአጠቃላይ የፋይናንሱ ስነ-ምህዳር ጋር የተያያዙ ድንበር-ዘለል ተግዳሮቶችም አሉ።

ጥ.አ.መ.ኢ.ች የፋይናንስ አቅርቦት ሲያጡ፣ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴን የማነቃቃት እና ስራ የመፍጠር አቅማቸው ይገደባል (W.B፣ 2015)። በተለይም ጀማሪዎች አስፈላጊ ካፒታል ስለማይኖራቸው ስራዎችን ለማስፋት እና ለማስቀጠል ትልቅ ትግል ውስጥ ይገባሉ። ይህም የውድቀት እድላቸውን ይጨምራል። በተጨማሪም፣ ውስን የገንዘብ ድጋፍ፣ ጥ.አ.መ.ኢ.ች በገበያ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንዳይሳተፉ ይከለክላቸዋል። ይህ ደግሞ እድገታቸውን ከመገደቡም በተጨማሪ ጠንካራ የሀገር ውስጥ ገበያና የአቅርቦት ሰንሰለት አውታር ለመዘርጋት እንቅፋት ይሆናል። በመሆኑም፣ በጥ.አ.መ.ኢ. ውስጥ ያለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እና ሊፈጥሩት የሚችሉት የስራ እድል መቀነስ ተያኘነት ያላችው ውጤቶች ይኖሩታል። ይህ ደግሞ ሰፊ ለሆነ የኢኮኖሚ አለመረጋጋት እና የድህነት አዙሪት አስተዋጽኦ ያደርጋል።

## 3.3. የዘ.ፋ.ተ.ስ.ፈ. ፕሮግራም አጠቃላይ እይታ

የማስተርካርድ ፋውንዴሽን በኢትዮጵያ እየተገበረ ያለው *'ያንግ አፍሪካ ምርክስ* (ወጣት አፍሪካውያን ይሰራሉ) *ስትራቴጂ፣* በወጣቶችና ወጣት ሴት *ሥራ* ፈጣሪዎች የሚመሩ ጥ.አ.መ.ኢ. የሚያጋጥሟቸውን ተከታታይ ፈተናዎች መፍታት ላይ ያተኮረ ነው። በተለይም የፋይናንስ አቅርቦት ችግርን ለመፍታት ትልቅ ትኩረት ያደርጋል። ፋውንዴሽኑ እነዚህ አካላት (ጥ.አ.መ.ኢ.) ኢኮኖሚያዊ እድገትን እና የስራ እድልን በመፍጠር የሚጫወቱትን ወሳኝ ሚና በመገንዘብ ቀጣይነት ያላቸውን የፋይናንስ ተደራሽነት ውጥኖችን ለአመታት ሲደግፍ ቆይቷል። በሰኔ 2023፣ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ከኪፊያ ፋይናንሺያል ቴክኖሎጂ ጋር በመተባበር ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. አስተዋወቀ። ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ.፣ ጥ.አ.መ.ኢ.ን፣ አነስተኛ ገበሬዎችን እና መካከለኛ ገቢ ያላቸውን ሸማቾችን ለመርዳት ያለመ ያለዋስትና ብድር የመስጫ ሞዴል ነው። ሴቶች (80%) የዚህ ሞድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ትኩረት ተሰቷቸዋል። ይህ ቀጣይነት ያለው መርሃ ግብር ዋስትና የማይጠየቅባቸው ዲጂታል አገልግሎቶችን በመስጠት፣ ዲጂታል ክህሎቶችንና የፋይናንስ እውቀትን በማሳደግ፣ እና የብድር ተደራሽነትን በማስፋት የስራ እድል ፈጠራን ያሳልጣል። በUS$75 ሚሊዮን የገንዘብ አቅርቦት እና በ25 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የቴክኒክ ድጋፍ እየተደገፈ፣ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. ሁሉን-አቀፍ የፋይናንስ ተደራሽነት ለማስፋት የተቀየሰ ነው። ከስድስት አጋር ባንኮች ጋር በመተባበር፣ ፕሮግራሙ ጥ.አ.መ.ኢ. ከ US$300 ሚሊዮን በላይ ያለዋስትና የሚሰጥ ዲጂታል ብድር ለማቅረብ ይሰራል።

ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ.፣ ብድር ገንዘብ ላይ ከፍ ያለ *ሥራ* በመስራት፣ በጥ.አ.መ.ኢ. ፋይናንስ ዙሪያ ከአቅርቦት እና ፍላጎት አንጻር የሚያጋጥሙ እንቅፋቶችን ለማስወገድ ይጥራል። ። ኮ.መ.ማ.ፕ እና ጥ.አ.መ.ኢ. ለክፍያ የሚቀል ብድር እና እርዳታ በሚሰጡ ጊዜ ተበዳሪዎች የደመወዝ ወይም የሰው ዋስትና እንዲያቀርቡ ይጠይቃሉ። በአንጻሩ፣ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. አዲስ፣ ዋስትና የማይጠይቅ የብድር ሞዴል አስተዋውቋል። በ ሰው ሰራሽ አስተውሎ የሚመራ የሽግግር ጊዜ ብድር አመላለስ ማዕቀፍን መጠቀም፣ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. ብድር ለመውሰድ የማስያዣ አስፈላጊነትን አስቀርቷል፣ ይህም በጥ.አ.መ.ኢ. የፋይናንስ አሰራር ታሪክ ከፍተኛ ለውጥ ሆኖ ተመዝግቧል።

***ምሥል 1፡ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፊ. የሚያተኩርባቸዉ ተግዳሮቶች***

| ከፍላጎት ጋር የሚያያዙ ተግዳሮቶች | ከአቅርቦት ጋር የሚያያዙ ተግዳሮቶች |
|---|---|
| በተበዳሪው ስም የተመዘገበ ማስያዣ አለመኖር፤ የቋሚ ንብረት እጥረት:: | በቂ ያልሆነ የአደጋ ግምገማ መሳሪያዎች - አደጋን ለመቆጣጠር በዋስትና ላይ መተማመን:: |
| መደበኛነትን ያልከተለ ንግድ፣ ደካማ የብድር ታሪክ እና የፋይናንስ መረጃን መዝግቦ የመያዝ ችግር:: | አግባብነት ያላቸው፣ ተስማሚ የፋይናንስ አገልግሎቶች እጥረት:: |
| በወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ዘንድ መሰረታዊ የፋይናንስ እውቀት እና ግንዛቤ ዝቅተኝነት:: | አነስተኛ መጠን ያለው፣ ለብድር የሚውል ገንዘብ በቀጣይነት ለማግኘት፣ ለማስተዳደርና፣ ለተጠቃሚ ለማቅረብ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ መሆኑ:: |
| በመረጃ ሰጪና ተቀባይ መካከል ያለ የመረጃ አለመመጣጠን፤ ለምሳሌ የመታወቂያ እጥረት፣ ለአበዳሪዎች መረጃ መስጠት አለመቻል:: | ለጥ.አ.መ.ኢ. ብድር መስጠት ከፍተኛ ስጋት ላይ ይጥላል ብሎ ማሰብ:: |
| ረጅም የማመልከቻ ሂደት:: | የዲጂታል መሠረተ ልማት እጦት፣ በገጠር አካባቢዎች ውስን ቅርንጫፎች መኖር:: |

## 4. መንግስት አመራር ለመስጠት እና በተግባር የሚገለጽ ሥራ ለመስራት ያለው ቁርጠኝነት፡ አስቻይ የፖሊሲ ከባቢ

**የኢትዮጵያ መንግስት ምቹ የፖሊሲ ምህዳርን በማዘጋጀት፣ አዳዲስና አካታች የፋይናንስ አሰራሮችን በማስተዋወቅ ረገድ ግንባር ቀደም የመሪነት ሚና ተጫውቷል።**

እንደ ክፍያ ያሉ ቴክኒካዊ መፍትሄዎችን ማዘጋጀት እና ማስተዋወቅ የተቻለው ቀጣይነት ያላቸው የፋይናንስ ዘርፍ ማሻሻያዎች በመደረጋቸው ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የሠራተኛና ክህሎት ሚኒስቴር፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች እንደገለጹት በፋይናንስ ዘርፉ በርካታ የፖሊሲና የቁጥጥር ለውጦች የተደረጉ ሲሆን እነዚህ ለውጦች ከሀገር-በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ (HGER) እና ከአሥር ዓመት ዕቅዱ ጋር የተተጣጣሙ ናቸው[15]። ከኢ.ን.ባ. የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው መንግሥት ነባር አሠራሮችን በመገምገምና መመሪያዎችን በማውጣት ረገድ ንቁ ሥራ ይሰራል። ከሚያካሂድባቸው ስራዎች መካከልም የፋይናንስን ዲጂታል አሰራር ማጎልበት፤ አካታችነት፣ ተደራሽነት፣ ማስፋፋት፣ የሞባይል ባንክ አሰራርና የመሳሰሉትን ማሳደግ ይጠቀሳሉ[16]። መንግስት ቀጣይነት ያላቸው ማሻሻያዎችን በሀገር በቀል የኢኮኖሚ አጀንዳ[17] መሰረት መደረግ እነዳለባቸው ይገነዘባል፤ ምክንያቱም የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ካልተቀረፈ በ2025 ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለመሰለፍ ያላትን ዓላማ አደጋ ላይ ይጥላል።

የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ትኩረት በወጣት ለሚመሩ ጥ.አ.መ.ኢ፣ ለወጣት ሴት ስራ ፈጣሪዎች እና የባንክ አገልግሎት ላልተዳረሰባቸው የገጠር ማህበረሰቦች ሲሆን ፋውንዴሽኑ አሰራሩን ከኢ.ብ.ባ. አሰራር ጋር በማቀናጀት ባንኩን በቀጣይነት እየደገፈ ይገኛል። ለምሳሌ፣ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን የፋይናንስ ስነ-ምህዳር ተዋናዮች የሆኑትን እንደ ኪፌያ እና የ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፌ. አጋር ባንኮችን ሲያግዝ ቆይቷል። የነዚህ ተዋናዮች ጥረት፣ እንደ ዲጂታል ኢትዮጵያ እና አካታች የፋይናንስ ስትራቴጂ II ያሉ፣ ከፋይናንስ ሴክተሩ ጋር የተያያዙና አገራዊ ፖሊሲዎችን ያማከሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን ተግባራዊ ማድረግ ነው።

### *ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025*

በሰኔ 2020፣ የኢትዮጵያ መንግስት "ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025" በመባል የሚታወቀውን አገራዊ የዲጂታል ለውጥ ስትራቴጂ ጀመረ። ዓላማውም በ2025 ኢኮኖሚውን ዲጂታል ማድረግ ነው። ዲጂታል ኢትዮጵያ፣ በሁሉም ዘርፎች ቴክኖሎጂዎችን በመዘርጋትና በመተግበር በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረቱ ስራዎችን እና ካፒታል ለመፍጠር አልሞ ሲሰራ ቆይቷል። የኦ.ህ.ስ.ባ. ቁልፍ መረጃ ሰጭ እንደገለጸው፣ ከሞባይል ገንዘብ፣ የክፍያ ሥርዓቶች እና ዲጂታል ባንኪንግ ጋር የተያያዙ የመንግስት ፖሊሲ ለውጦች፣ ባንኮች እንደ 'ሚቹ' ያሉ አውታሮች ላይ እንዲያተኩሩ

[15] The scope of this case study did include a comparison of the impact of individual policies, nor assess the gendered impact of these policies

[16] www.mofed.gov.et/media/filer_public/38/78/3878265a-1565-4be4-8ac9-dee9ea1f4f1a/a_homegrown_economic_reform_agenda-_a_pathway_to_prosperity_-_public_version_-_march_2020-.pdf

[17] Ibid

እና እንደ *'ክፍያ'* ካሉ ውጫዊ አጋሮች ጋር በመተባበር ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀጥሉ አበረታቷቸዋል:: በተመሳሳይ፣ የMNT ቁልፍ መረጃ ሰጭ አክለው እንደገለጹት የብሔራዊ ዲጂታል ስትራቴጂ፣ የፋይናንስ ሥነ-ምህዳሩን በመሰረታዊነት ለውጦታል፤ ይህም ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025ን እውን በማድረግና የውስጥ ፖሊሲዎችን በማስተካከል ረገድ አስተዋፅኦ አድርጓል::

### *የፋይናንስ ዘርፍ ፖሊሲዎች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች*

የወጣቶች አካታችነት ላይ ውጤት የሚኖራቸው የፋይናንስ ዘርፍ ፖሊሲዎች በሶስት ሰፋፊ ምድቦች ሊከፈሉ ይችላሉ:: በመጀመሪያው ምድብ ውስጥ የፋይናንስ ሴክተሩን እና የፋይናንስ አካታችነትን በቀጥታ የሚመለከቱ ፖሊሲዎች አሉ:: እነዚህ የብሔራዊ አካታችነት ጥረቶች ዋና አካላት ናቸው:: በሁለተኛው ምድብ ውስጥ በፋይናንስ ላይ ብቻ የማያተኩሩ፣ ነገር ግን የፋይናንስ ማካተትን በተዘዋዋሪ የሚደግፉ ሰፋ ያሉ ፖሊሲዎች አሉ:: በመጨረሻም፣ ከታች ባለው ሠንጠረዥ እንደተገለጸው ለእድገት አጋዥ ከባቢ የሚፈጥሩ ፖሊሲዎች አሉ::

**ሰንጠረዥ 2፡ የፋይናንስ ዘርፍ ፖሊሲዎች**

| ቀጥተኛ አካታች የፋይናንስ ፖሊሲ | በተዘዋዋሪ የሚዛመዱ አካታች የፋይናንስ ፖሊሲዎች | ደጋፊ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎች |
|---|---|---|
| • **ብሄራዊ የዲጂታል ክፍያዎች ስትራቴጂ፣ (ብ.ዲ.ክ.ስ)** ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው እና የገጠር ማህበረሰቦችን ተደራሽነት ለማሳደግ ዲጂታል የክፍያ ሥርዓቶችን ያስተዋውቃል<br><br>• **ብሔራዊ የፋይናንስ ትምህርት ስትራቴጂ፣** (ብ.ፋ.ት.ስ.) እ.ኤ.አ. በ2025፣ 75% አዋቂዎች፣ በተለይ የፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶች ላይ ያላቸውን እውቀት ለማሳደግ ያልማል።<br><br>• **ብሔራዊ አካታች የፋይናንስ ስትራቴጂ II (ብ.አ.ፋ.ስ. II)፡** እ.ኤ.አ. ዘርፍ-ዘለል መርሃ ግብሮችን በማብዛት እና ስር እንዲሰዱ በማድረግ በ 2025፣ 70% ጎልማሶችን (በተለይ በቂ አገልግሎት ያላገኙትን) ተጠቃሚ ለማድረግ ከHGER ጋር የተጣጣመ ሥራ ይሰራል::<br><br>• **የገጠር ፋይናንስ አመቻች ፕሮግራም፣ (ገ.ፋ.አ.ፕ)፡** የገጠር የፋይናንስ ተቋማትን በማጠናከር የቁጠባ እና ብድር ፍሰትን ለማሳደግ ይሰራል።<br><br>• **የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ጥበቃ መመሪያ፡** እምነትን ለማጎልበት የሸማቾችን መብቶች እና የገበያ መረጋጋትን በማስፈን መተማመን ለማምጣት ይሰራል። | • ***ሐገራዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ, (ሀ.ኢ.ማ.አ.)፡*** ግብርናን በገንዘብ መደገፍ፣ ዲጂታል አሰራር ማስፈንን ጨምሮ ሌሎች ከፋይናንስ ጋር የተገናኙ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል።<br><br>• **ብሄራዊ የዲጂታል ሽግግር ስትራቴጂ፣ (ብ.ዲ.ት.ስ.)፡** ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ዲጂታል ክፍያ፣ የሞባይል ገንዘብ እና የፋይናንስ ትምህርት ፕሮግራም ማስፋፋት ላይ ያተኩራል።<br><br>• ***የስራ ፈጠራ የድርጊት መርሃ ግብር፣ (ሥ.ፈ.ድ.መ.)፡*** የወጣቶችን ሥራ አጥነት መቀነስ እና በተለይም ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች (ጥ.አ.መ.ኢ) የሥራ ዕድል መፍጠር ላይ ያተኩራል።<br><br>• ***የንግድ ሥራ ማቅለያ ማሻሻያ አጀንዳ (ን.ሥ.ማ.ማ.አ.)*** የኤሌክትሮኒክ የክፍያ ዘዴን ያጠናክራል፣ የተንቀሳቃሽ ንብረቶች ዋስትና እና የብድር መረጃ ስርዓቶችን ያሻሽላል።<br><br>• **የፋይናንስ ዘርፍ የማሻሻያ አጀንዳ፣ (ፋ.ዘ.ማ.አ.)፡** የፋይናንስ ዘረፉን ቅልጥፍና እና አካታችነት በማሻሻል በተለይ በገጠር ላሉ በዝቅተኛ ደረጃ አገልግሎት የሚያገኙ ነዋሪዎችን በተሻለ ለማገልገል ይጥራል። | • **የአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ የፋይናንስ ፕሮግራም** (ብ.ኤ.ማ.ፕ.)<br><br>• **ብሔራዊ ኤሌክትሪክ የማዳረስ ፕሮግራም** |

### *የኢንተርኔት ግብይት*

የኢትዮጵያ የኢንተርኔት ግብይት ስትራቴጂ ዓላማ ከንግድና ወደ ውጭ ከሚላኩ እቃዎች የሚገኙ ገቢዎችን ማሳደግ ሲሆን ይህን ዓላማ ዕውን ለማድረግ ጠንካራ የዲጂታል ገበያን ማጎልበት አስተዋጽኦ እንዳለው ይታመንበታል፡፡ ስትራትጂው፤ ዲጂታል ቴክኖሎጂን በሰፊው በመጠቀም የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት፤ የገበያ ተደራሽነትን ለማስፋት እንዲሁም ለንግድ ሰራተኞችና ሸማቾች አዳዲስ እድሎችን ለመፍጠር ይሰራል፡፡ ስትራቴጂው ሶስት ቁልፍ ተግባራት ላይ ያተኩራል፡፡ አገራዊ የሆነ የኢትዮጵያ የኢንተርኔት የግብይት አውታሮችን ማቋቋም፤ የቁጥጥር ማዕከላትን ጥቅም ላይ ማዋል እና የገጠር የኢንተርኔት ግብይትን ማሳደግ ናቸው፡፡ ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ለአገሪትዋ የኢንተርኔት ግብይት ዕድገት ዋና ሞተር ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

### *አካታች የፋይናንስ ስትራቴጂ II*

የኢትዮጵያ አካታች የፋይናንስ ስትራቴጂ አጠቃላይ ዕቅድ ሲሆን ዓላማውም ሁሉም የአገሪቱ ዜጎች መደበኛ የፋይናንስ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ተደራሽነትንና ተጠቃሚነትን ማስፋፋት ነው፡፡ በተለይ በዚህ ረገድ በዝቅተኛ ደረጃ አገልግሎት ያገኙ የነበሩ ማህበረሰቦች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በስትራቴጂው ቅድሚያ የተሰጣቸው ጉዳዮች፡- ዲጂታል የፋይናንስ አካታችነትን ማስፋፋት፣ የፋይናንስ መሰረተ ልማቶችን በማስፋፋት ዝቅተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ የነበሩ አካላትን ይበልጥ ማገልገል፣ በሴትና በወንድ መካከል የሚታየውን የፋይናንስ ተጠቃሚነት ክፍተት ማጥበብ ብሎም የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ማጎልበት፣ ሸሪያን ያማከሉ የፋይናንስ አገልግሎቶች ገበያ ላይ በብዛት እንዲገኙ ማስቻል ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡
ይህ ስትራቴጂ፣ ባንኮች ከጠቅላላ ብድር 5 በመቶውን ለአነስተኛ ገበሬዎች እና ሌላ 5% ደግሞ ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን በመጠቀም ለአነስተኛ ገበሬዎች እንዲመድቡ የሚያስገድድ ነው፡፡ ይህ አሰራር ተንቀሳቃሽ የዋስትና መዝገብ መመሪያን ለማስተዋወቅ የበኩሉን ሚና ተጫውቷል፡፡ ባንክ ውስጥ የሚሰሩ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ከሆነ እነዚህ የፖሊሲ ለውጦች የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶችን፣ የሞባይል ባንኪንግን እና አገልግሎት ለሌላቸው ማህበረሰቦች ተደራሽነትን በማሳደግ ረገድ አስተዋጽዖዋቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ሆኖም ከ MFI የተገኘ ቁልፍ መረጃ ሰጪ እንደተናገረው "ባንኮች ይህንን 5% ብድር ለ MFIs እንዲለቁ የሚያስገድድበት ምንም አይነት የማስፈጸሚያ ዘዴ የለም፤ በዚህም ምክንያት MFIs የገንዘብ እጥረት ስላጋጠማቸው የብድር መጠኑን ከፍ ማድረግ እና የተቸገሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማስተናገድ አልቻሉም፡፡

### *ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት መጀመር*

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በቅርቡ ኢስላማዊ የፋይናንስ ባንክ አገልግሎት (ኢ.ፋ.ባ)ን በቁጥጥር ማዕቀፉ ውስጥ በማካተት ሸሪዓን ማእከል ያደረገ አሰራር አስተዋውቋል፡፡ ዘምዘም ባንክ እንደገለጸው፣ "ከዚህ ቀደም IFBን ያማከለ አስተዳደራዊ መዋቅር አልነበረም፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እስላማዊ የባንክ አሰራርን በተሟላ ሁኔታ አይተገብርም ነበር፡፡" ዘምዘም ባንክ ጨምሮ እንዳለው፣ ብሔራዊ ባንክ የ‹ሙራባሃ› ሞዴልን ማፅደቁንም ይጠቅሳል፡፡ በዚህ ሞዴል ላይ በመመስረት አንድ ባንክ በደንበኛው ስም ሸቀጦችን ገዝቶ በተወሰነ ትርፍ የሚሸጥበት አሰራር ነው፡፡ ይህ አሰራር ወለድ ላይ ከሚያተኩር ብድር አሰጣጥ የሚለየው የሙራባሃ ዋጋ ኮንትራቱ

እስኪያበቃ ድረስ አይለወጥም። ይህ ሞዴል፣ ጥ.አ.መ.ኢ. ከሚከተሉት አሰራር ይልቅ ሽሪያን ያማከለ አማራጭ ይሰጣል።

### *የጥ.አ.መ.ኢ. ስትራቴጂን ማሻሻል*

ሲ.ማ.ጉ.ሚ፣ በማስተርካርድ ፋውንዴሽን ድጋፍ የጥ.አ.መ.ኢ. ስትራቴጂውን አሻሽሏል። ይህ ማሻሻያ በሚመለከታቸው ባለስልጣናት ጸድቆ ለትግበራ ተላልፏል። እነዚህ ስትራቴጂዎች የጥ.አ.መ.ኢ. ብድርን በማስተዋወቅ፣ አዳዲስ የፋይናንስ ሞዴሎችን በማሳደግ እና ከአለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ጋር ያለውን አጋርነት በማጠናከር ላይ የሚያተኩሩ ናቸው።

### *የገንዘብ ፖሊሲ ማስተካከያዎች*

እ.ኤ.አ. በ 2023፣ ብሔራዊ ባንክ ከዋጋ ንረት-ቅነሳ ጥረቶቹ አንዱ የሆነውን የ14 በመቶ የብድር ጣሪያ አስተዋወቀ። ይህ አሰራር፣ ብድር የመመለስ ሂደትን የጎዳ ሲሆን በተለይ ጥ.አ.መ.ኢ. እና የባንክ ተጠቃሚ ያልሆኑ ቡድኖች ተጠቂ ሆነዋል። ይሁን እንጂ እ.ኤ.አ. የኢ.ን.ባ. በ2024 መጨረሻ አካባቢ የንግድ ባንኮችን አመታዊ የብድር እድገት ጣርያ ከ14% ወደ 18% እንዲያድግ አድርጓል[18]። የዚህ እርምጃ ዓላማ የገንዘብ ቁጥጥርን በማላላትና የፋይናንስ ተቋማትን በማጠናከረ የተበዳሪዎችን ፍላጎት ማሟላትና ኢኮኖሚያዊ መረጋጋትን ማምጣት ነው። በተጨማሪም የካፒታል እና የመጠባበቂ ገንዘብ መስፈርቶች ላይ የወጡ ማሻሻዎች፣ (በተለይ ለባንኮች የተቀመጠ ዝቅተኛ የካፒታል መጠን ላይ የተደረጉ ለውጦች) የካፒታል መዋቅር እና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ላይ ማስተካከያ እንዲደረግ ተጽዕኖ ድርጓል።[19]

በተጨማሪም የብድር መረጃ ክምችት/ፖርትፎልዮ ላይ የሚደረግ ቁጥጥር፣ (ለምሳሌ የዘርፍ ብድርን በሚመለከት፣ የኢ.ብ.ባ. ያወጣውን መመሪያ ጨምሮ) የባንኮች የብድር ስትራቴጂ ላይ ተጽዕኖ አድርጓል። እነዚህ፣ የኢ.ብ.ባ የዘርፍ ብድር ላይ ያወጣቸው መመሪያዎች በቤት ግንባታ ላይ የተጣሉ ገደቦች፣ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው እንደ ግብርናና እና አምራች ዘርፎች የሚደረግ ማበረታቻ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

### *የቁጥጥር መሰናክሎች*

በስራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ የባንክ ሞዴል ከባንክ ውጪ ያሉ የፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢዎች ብድር እንዲሰጡ የሚፈቅድ የቁጥጥር ማዕቀፍ የለውም። ከኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ናይጄሪያ እና ህንድ ካሉ አገራት ገበያ ጋር ሲወዳደር ከፍተኛ የሆነ ልዩነት ይታያል። በእነዚህ አገራት ከባንክ ውጪ ያሉ ተቋማት ለጥ.አ.መ.ኢ. ብድር በመስጠት ረገድ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ናቸው። በእነዚህ ገበያዎች ብድር መስጠት ለባንኮች ብቻ የተገደበ አይደለም። ሌላው፣ በኢትጵያ የዲጂታል ብድር አተገባበርን እና የደንበኛ መረጃ ማጋራትን በሚመለከት ወጥነት የሚጎድላቸው ፖሊሲዎች መኖራቸው አተገባበር ላይ ውስብስብ ሁኔታን ፈጥሯል፤ በፋይናንስ ስርአቱ ላይ ወጥ የሆነ መለኪያ ለማበጀትም ተጨማሪ ሳንካ ሆኗል። ለምሳሌ እናት ባንክ ወጥነት የጎደለው ፖሊሲ መኖር በዲጂታል ብድር እና የመረጃ ማጋራት ላይ የሚፈጥረውን ተግዳሮት ገልጧል።

---

[18] Vision MFI
[19] Nisir MFI

## *የውጪ ተዋናዮች ሚና፡ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን አጋርነት*

*ማስተርካርድ ፋውንዴሽን እና አጋሮቹ በኢትዮጵያ የዲጂታል ፋይናንስ ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን መዋዕለ ንዋያቸውን አፍስዋል፤ ብዙ ስራዎችንም ሰርተዋል። ይህም ባንኮች ውስጣዊ፣ ስትራቴጂካዊ የአሠራር ለውጦችን እንዲያደርጉ አስችሏቸዋል፡፡ ባንኮችም በበኩላቸው፣ እንደ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. ያሉ ፕሮግራሞችን እና ፈጣን የገንዘብ ማስገኛ ዘዴዎቻቸውን እውቅና ይሰጣሉ። እንደነዚህ ያሉ ዘዴዎች ባንኮች ለተጠቃሚዎች፣ በተለይም ለወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ያለዋስትና የሚሰጡ ዲጂታል ብድሮችን በልበ ሙሉነት እንዲያቀርቡ አስችሏቸዋል። እንደዚህ ዓይነት ጥምረቶች አዳዲስ አገልግሎቶች ስራ ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ አፋጥኗል፤ የብድር ውሳኔ አሰጣጥም በሰው ሰራሽ አስተውሎት የጎለበተ የመረጃ ትንተና ላይ እንዲመሰረት የበኩላችውን አስተዋጽዖ አበርክተዋል፡፡ በተጨማሪም፣ ጠቃሚ የቴክኒክ እና የአቅም ግንባታ ድጋፍ የማግኘት አስፈላጊነት ልብ እንዲባል አድርገዋል፡፡ ይህ ከማስተርካርድ ፋውንዴሽን ጋር የተደረገ ትብብር ያለዋስትና የሚሰጡ የብድር አገልጎሎት ዓይነቶች እንዲፈጠሩና ጥቅም ላይ ዕንዲውሉ በማድረግ ረገድ ትልቅ እገዛ አድርጓል። ሌላው አስተዋጽዖዋቸው የዋስትና ጥገኝነትን መቀነስ እና በመረጃ አሰባሰብ አማካኝነት ጤናማ የአደጋ አስተዳደርን ማረጋገጥ ይጠቀሳል።*

*በተለይ፡-*

- *በ ሰው ሰራሽ አስተውሎት የጎለበተ፣ በመረጃ ላይ የተመሰረተ የብድር አሰጣጥ ስርዓት፣ ባንኮች ሰፊ መረጃን በመጠቀም የብድር ብቃትን ከገመገሙ በኂላ የብድር አሰጣጥ ሂደታቸውን እንዲቀይሩ አስችሏቸዋል። ለምሳሌ ወጋገን ባንክ በተበዳሪ ባህሪ፣ በግብይት ታሪክ እና ብድር በመክፈል አቅም ላይ ተመስርተው በላቀ የ*MIS *ዘዴ እና* **የሳይኮሜትሪክ** *መሳሪያዎች ታግዘው ወቅታዊ ግምገማዎች ያካሂዳሉ። ይህ ከባህላዊ የዋስትና መስፈርቶች የላቀ ዘመናዊ አሰራር ነው። ይህ አሰራር፣ ባንኮች ቀደም ሲል የ ባንክ አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ለማያገኙ ጥ.አ.መ.ኢ. እና ግለሰቦች በልበ ሙሉነት ብድር እንዲሰጡ አስችሏቸዋል። በተመሳሳይ፣ ኦ.ህ.ሥ.ባ. እንደዘገበው የሳይኮሜትሪክ ፈተናን፣ የፋይናንስ ግብይት ታሪክ እና የባህሪ ትንታኔዎችን የሚያካትቱ አማራጭ የብድር ውጤት መስጫ ሞዴሎችን መጠቀም በዋስትና ላይ ያለውን የጥገኝነት አሰራር ቀንሷል።*
- *የሽግግር ጊዜ የገንዘብ ማስገኛ ዘዴዎች እና ጊዜያዊ የብድር ዋስትና መርሀ-ግብሮች በመጀመሪቸው ለጥ.አ.መ.ኢ. ብድር መስጠት ጋር ተያይዞ ያለው ስጋት ቀንሷል፤ በዚህም ምክንያት በብድር የሚሰጥ የገንዘብ መጠን ጨምሯል።*
- *ከኪፊያ ጋር በመተባበር ባንኮች አዳዲስ የፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶችን አዘጋጅተዋል። እነዚህ አገልግሎቶች፣ የጥ.አ.መ.ኢ. ልዩ ልዩ ፍላጎቶችን ለማሟላት የተነደፉ ሲሆኑ ዘርፍ-ተኮር እና ሴት-ተኮር ብድሮች ናቸው። ይህ የጥ.አ.መ.ኢ. ተሳትፎን በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፤ አካታች ፋይናንስን አበረታቷል፤ ባንኮች የብድር መረጃ ክምችታቸውን እንዲያሳድጉ ረድቷቸዋል።*
- *ባንኮች፣ የቴክኒካዊ ድጋፍ እና የለውጥ አስተዳደር እገዛዎችን በማግኘት፣ ዋስትና የማይጠየቅበት የዲጂታል ብድር አሰጣጥ አሰራሮችን ለመተግበር እና ለማስተዳደር አስፈላጊ የሆኑ ችሎታዎችን አግኝተዋል፡፡ ይህንን ለውጥ ለማሳለጥ ለከፍተኛ አመራር አካላት የሚሰጥ የአቅም ግንባታ ስልጠና ወሳኝ መሆኑን ከቡና ባንክ የመጡ ዋና መረጃ ሰጪ በአፅንኦት ገልጸዋል።*

# 5. የዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. ያለዋስትና የሚሰጥ የብድር ሞዴል

## 5.1. የፕሮግራሙ አጠቃላይ እይታ

### የዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ ማስተዋወቂያ

እ.ኤ.አ. በ2022 ኪፊያ፣ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን እና የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ 'ሚቹ' የተባለውን ለኢትዮጵያ ፈር ቀዳጅ የሆነ ያለዋስትና የሚሰጥ ዲጂታል የብድር አገልግሎት ለጥ.አ.መ.ኢ. አስተዋውቀዋል፡፡ የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ በ2005 ዓ.ም የተመሰረተ 'ቅድሚያ ለዲጂታል- አሰራር' የሚል መርሕ ያለው ባንክ ነው፡፡ ኪፊያ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ፣ እ.ኤ.አ. በ2010 የተመሰረተ እና መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ የፊንቴክ ኩባንያ ሲሆን በኢትዮጵያ የፋይናንስ እና የገበያ ተደራሽነትን ለማስፋት በመረጃ የተደገፈ ዲጂታል መፍትሄ ይጠቀማል፡፡ ኪፍያ፣ የዲጂታል አጠቃቀም ክፍተትን ለማጥበብ አትኩሮ የሚሰራ ሲሆን የተለያዩ ክፍያዎችን፣ ኢንሹራንስ እና ጥቃቅን ብድሮችን የሚያጠቃልሉ አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡ ዋናው ትኩረቱ በቂ ግልጋሎት የማያገኙ ማህበረሰቦችን ማጎልበት እና የኢኮኖሚ እድገትን ማበረታታት ነው፡፡ ቀደም ብሎ በተወሰነ የብድር አሰጣጥ ጥምርታ ላይ በመመስረት፣ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን በኪፊያ በኩል ለ ኦ.ህ.ሥ.ባ. የገንዘብ ማስገኛ ዘዴዎች ይሰጣል፡፡ ኦ.ህ.ሥ.ባ.፣ የኪፊያ ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማትን እና የቴክኒክ ድጋፍን በመጠቀም የሚቹ ብድሮችን ማቅረብ ችሏል፡፡ ይህ፣ ንግዶች፣ በሚቹ አውታሮች በኩል በዲጂታል መንገድ እንዲያመለክቱ እና በብድር ብቁነታቸው ላይ በመረጃ የተደገፉ ውሳኔዎችን እንዲቀበሉ ያስችላቸዋል፡፡ የብድር አከፋፈል ሂደቱም በዲጂታል መንገድ ይከናወናል፡፡ በሚቹ ስኬት እና የብድር ፍላጎት ቀጣይነትን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ኪፊያ እና ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስራ ፈጣሪነትን ለማጎልበት ያለመ ዘላቂ የፋይናንስ ተደራሽነት (ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ) በመባል የሚታወቅ ፕሮግራም በጋራ ፈጠሩ፡፡ የዚህ ፕሮገራም ዋና አላማ ከዋስትና ነፃ የሆነ የዲጂታል ብድር አገልግሎት አሰጣጥን ማስፋፋት ነው፡፡

ክፍያ ፋይናንሺያል ቴክኖሎጂ ከስድስት ባንኮች እና የስነ-ምህዳር አጋሮች ጋር በመተባበር የሚተገብረው፣ የዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. ፕሮግራም አላማ በገጠር፣ በከተማ እና በከተማ ዙሪያ ላሉ ነዋሪዎች (በዋነኛነት ለሴቶች) ተገቢ የፋይናንስ መፍትሄዎችን መስጠት ላይ ያተኮረ ነው፡፡[20] ይህም፣ ወጣቶች ዋስትና የማይጠየቅባቸውን ዲጂታል አገልግሎቶችን በመጠቀም ሥራ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡

ይህ ምኞት፣ በአሁኑ ጊዜ የጥ.አ.መ.ኢ. የፋይናንስ ተደራሽነታቸውን የሚያደናቅፉ ወሳኝ ተግዳሮቶችን በመፍታት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ፣ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. ከአቅርቦት አንጻር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚጥር ሲሆን በዋናነት በፋይናንስ ተቋማት ውስጥ ያለው የብድር ገንዘብ አቅርቦት ውስንነት ለዚህ ዓላማ መሳካት እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ለብድር የተቀመጠ ገንዘብ እጥረት ወደ ጥ.አ.መ.ኢ. ይገባ የነበረውን የካፒታል መጠን ይገድባል፡፡ በመጨረሻም፣ ፕሮግራሙ ከገበያ ዕውቀት ጋር የተያያዙ የስነምህዳር እንቅፋቶችን እና ዲጂታል ብድርን የሚመራውን የቁጥጥር ማዕቀፍ ይፈታል (አባሪ B፣ የ ጥ.አ.መ.ኢ. ለውጥ ቲዎሪን ይመልከቱ)፡፡

[20] **ማስታወሻ፡** በዋነኝነት ብድር ትኩረት የሚያረገው ሴቶች ላይ ነው፡፡ ነገር ግን ቀደም ብለው የተዘረጉ መሰረተ-ልማቶችና የአሰራር ዘዴዎች፣ ባንኮች፣ እነዚህኑ የፋይናንስ አገልግሎቶች ለሁሉም ህዝብ ማቅረብ ስለሚያስችሏቸው ወንዶችም ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡

*የፕሮግራሙ ዓላማዎች እና ውጤቶች*

*ምስል 4፡ የዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ የንግድ ሞዴል ገጽታ*

| ዓላማ | ተግባራት | ዒላማ (TARGET) |
|---|---|---|
| አካታች የፋይናንስ ተጠቃሚነትን በሚከተሉት መንገዶች ማሰፋፋት፡-ያለዋስትና ብድር በመስጠት፣ የብድር ተደራሽነትን በማብዛት እና የፋይናንስ ትምህርትን በማሻሻል የጥ.አ.መ.ኢ. እድገትን እና አደጋ የመቋቋም አቅምን ማሳደግ:: | 1. የጥ.አ.መ.ኢ. ስልጠና<br>2. በሰዓቱ መረጃን መያዝ<br>3. በሰው ሰራሽ አስተውሎት ላይ የተመሰረተ የብድር ውጤት አሰጣጥና እና የብድር አገልግሎት<br>4. TA እና የባንኮች አቅም ግንባታ<br>5. የሽግግር ጊዜ የገንዘብ ማስገኛ ዘዴዎች እና ጊዜያዊ የብድር ዋስትና እቅድ<br>6. ቁጥጥርን ማጠናከር | 478,000 ጥ.አ.መ.ኢ. ዋስትና የማይጠየቅበት የዲጂታል ብድር አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማስቻል፤ ለ425,000 ወጣት ሴቶች የሞባይል ፋይናንስ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እድል ማመቻቸት፤ እስከ 2.18 ሚሊዮን ለሚደርሱ ወጣቶች በቀጥታ የስራ እድል መፍጠር:: |
| **የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች** | **አጋር የፋይናንስ ተቋማት** | **የስነምህዳር አጋሮች** |
| - 80% በሴቶች ባለቤትነት የተያዙ ኢንተርፕራይዞች<br>- 80% ወጣቶች<br>- 10% አካል ጉዳተኞች<br>- 10% ስደተኞች እና ተፈናቃዮች/IDPs | - የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ<br>- አማራ ባንክ<br>- ቡና ባንክ<br>- እናት ባንክ<br>- ወጋገን ባንክ<br>- ዘምዘም ባንክ | - የትምህርት ተቋማት (አካባቢያዊ እና ዓለም አቀፋዊ)<br>- የኢ.ብ.ባ<br>- የሞባይል ግንኙነት ኦፕሬተሮች<br>- የፋይናንስ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት<br>- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር |

እነዚህን ሁለገብ ተግዳሮቶች በብቃት ለመፍታት እና የእድገት ግቦቹን ለማሳካት፣ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. ስድስት ዋና ዋና ተግባራትን ነድፏል:: እነዚህ ተግባራት በፋይናንሺያል መልክዓ-ምድሩ ላይ ከሚታዩት ሶስት መሰረታዊ ለውጦች ጋር በስትራቴጂያዊ መንገድ የተሳሰሩ ናቸው፡- ዋስትናን መሰረት ካደረገ የብድር አሰጣጥ ወደ ያለ ዋስትና የሚሰጥ ብድር መሸጋገር፣ ለጥ.አ.መ.ኢ. የብድር አቅርቦትን ማስፋፋት እና የፋይናንስ ዕውቀት ክፍተቶችን መቅረፍ ናቸው:: ይህ ሁሉን አቀፍ አካሄድ፣ የበለጠ አካታች እና ጠንካራ የፋይናንስ ሥነ-ምህዳር ለመፍጠር ያለመ ነው:: የዚህ አካሄድ የመጨረሻ ግብ፣ በጥ.አ.መ.ኢ. ዘርፍ ውስጥ ዘላቂ እድገትን እና አደጋ የመቋቋም አቅምን ማጎልበት ነው:: ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ.፣ በሌሎች የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የጥ.አ.መ.ኢ. ፕሮግራሞች ውስጥ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን ተደራሽ የሚያደርግ የጋራ መገልገያ ይሆናል::

*ምስል 5: የ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፌ. እንቅስቃሴ አጠቃላይ እይታ*

| የፋ.ተ. እንቅፋት | የተግዳሮቶች መግለጫ | ዋና ተግባር |
|---|---|---|
| ከፍላጎት በኩል | ዝቅተኛ የሆነ የፋይናንስ እና የዲጂታል ትምህርት፣ ክህሎት እና ተደራሽነት ችግር<br>የማስያዣ እጥረት<br>ሴቶችን፣ ወጣቶችን እና ተጋላጭ ቡድኖችን ከብድር ውጤት አሰጣጥ የሚያርቅ ዝቅተኛ የመረጃ እና መሠረተ ልማት/ሥርዓት | 1. የ ጥ.አ.መ.ኢ. ስልጠና ★<br>2. የሰው ሰራሽ አስተውሎት ነጥብ አያያዝ እና የብድር አገልግሎቶች<br>3. በወቅቱ መረጃ መያዝ ★ |
| ከአቅርቦት በኩል | የብድር ብቁነት መለኪያዎች እጦት፣ ለጥ.አ.መ.ኢ. ማበደር በከፍተኛ ሁኔታ አስጊ ነው ብሎ ማሰብ እና ከፍተኛ የብድር አስተዳደር ወጪዎች ተደማምረው ብድር አሰጣጥ በዋስትና ላይ የተንጠለጠለ እንዲሆን ማድረጋቸው<br>የገንዘብ ማግኛ ማነቆዎች፣ ብድርን ለትላልቅ የድርጅት ተበዳሪዎች በቀዳሚነት መመደብ | 4. ለባንኮች የሚሰጥ የቴክኒክ ድጋፍ እና የአቅም ግንባታ ★<br>5. የሽግግር ጊዜ ገንዘብ የማግኛ መንገዶች እና ጊዜያዊ የብድር ዋስትና እቅድ |
| አስቻይ ከባቢ | ውስን የገበያ እውቀት፣ እና ገና በማደግ ላይ ያለው የቁጥጥር ከባቢ የዲጂታል ብድርን ለማስፋፋት በቂ አለመሆኑ | 6. የቁጥጥር አካባቢን መደገፍ እና ማጠናከር ★ |

★ እነዚህ እንቅስቃሴዎች የ ጥ.አ.መ.ኢ. የገበያ መፍትሔ ተግባራት (MSP) አካል ናቸው፤ ዓላማውም የክፊያን ዋና የቴክኖሎጂ መሠረተ-ልማት በማጎልበት የገበያ ችግርን የሚፈቱ መፍትሄዎችን መንደፍና መተግበር ነው።

**የፕሮግራሙ 6 ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው:-**

1. **የጥ.አ.መ.ኢ ስልጠና፣** ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ ወጣቶች በተለይም ለሴቶች የፋይናንስ ውሳኔ አሰጣጥ፣ የብድር አስተዳደር እና የንግድ ችሎታ ማሻሻያ የዲጂታል፣ የፋይናንስ እና የንግድ ክህሎቶች ስልጠና መስጠት። ለምሳሌ የፋይናንስ ፍላጎቶቻቸውን እንዲገመግሙ፣ ተስማሚ የፋይናንስ ምርቶችን እንዲመርጡ፣ ለተሻለ ጥቅም እንዲደራደሩ ወዘተ ማስቻል፣

2. **ወቅታዊ መረጃ መያዝ:** እንደ ትምህርት፣ ክህሎት እና የስራ ታሪክ ያሉ ተከታታይና ወቅታዊ መረጃዎችን መያዝ። እነዚህ መረጃዎችን፣ የተበዳሪውን መልካም ታሪክ ለማሳየት የሚጠቀሙ ብሎም ከዋስትና ነጻ ብድር ለማግኘት አስተማማኝ መሳሪያዎች አድርጎ መውሰድ

3. **የሰው ሰራሽ አስተውሎት የብድር ውጤት እና የብድር አገልግሎት አሰጣጥ:** ባንኮችን እና ፊንቴክን በሰው ሰራሽ አስተውሎት የጎለበተ ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ በማድረግ ሁሉን ዓቀፍ የብድር ውጤት አሰጣጥ እና ዲጂታል ብድር አሰጣጥን እውን ማድረግ። ባህላዊ የክሬዲት ውጤት አሰጣጥ ሞዴሎች በመደበኛ የክሬዲት ታሪክ ላይ ይመረኮዛሉ። ኪፊያ ግን የብድር

ብቁነትን ለመወሰን የአስተውሎት መረጃ እና ውሳኔ አሰጣጥ (IDD) የሚባል ስርዓት ይጠቀማል። ይህ ስርዓት፣ የግብይት ታሪኮችን እና የባህሪ ሁኔታዎችን ያካተተ ሰፋ ያለ መረጃን የሚሰበስብ በሰው ሰራሽ አስተውሎት የጎለበተ የብድር ውጤት ሞዴል ነው። ይህ በሰው ሰራሽ አስተውሎት ላይ የተመሰረተ ቴክኖሎጂ ጠንካራ የብድር ውጤቶች እና የአደጋ ደረጃዎችን ለማዘጋጀት እና ማጭበርበርን ለመለየት ይረዳል። አዲስ መረጃ ሲገኝ ስርዓቱ ራሱን ያስተካክላል፣ ያጠራል፣ ይህም የብድር ውጤት ትንበያዎች ሁሌም ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ያረጋግጣል።

የክፊያ አካሄድ ፍትሃዊ እና ሁሉን አቀፍ ብድርን ያበረታታል። የሚጠቀመው ቴክኖሎጂ ትክክለኛ እና ፍትሀዊ ግምገማ ለማካሄድ ያስችላል። በባህላዊ አሰራር ምክንያት የብድር ተጠቃሚ ሊሆኑ ያልቻሉ ጥ.አ.መ.ኢ.ን የብድር ተደራሽነት ያሰፋል። ከዚህም በላይ፣ የሚከተለው ሥርዓተ-ፆታ ተኮር የሆነ የብድር ውጤት አሰጣጥ ስትራቴጂ ዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን እና የአካባቢ መረጃዎችን በማቀናጀት ሲሆን ይህም የሥርዓተ-ጾታ ልዩነትን ለማስወገድ መፍትሄ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፤ በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ኢፍትሃዊ ጉዳትም ይከላከላል።

ከብድር አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ፣ የ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፊ. ፕሮግራም የፋይናንስ ተቋማት የተለያዩ ተገቢ እና ተዛማጅ የሆኑ የዲጂታል ብድር አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ በቴክኖሎጂ ይደግፋል። የኪፊያ ዋና የፋይናንስ አገልግሎት ቴክኖሎጂ፣ አስተዋይ የመረጃ አገልግሎት (IFS) ቴክኖሎጂን በመጠቀም፣ ዲጂታል አውታሮች (ለምሳሌ የባንክ አውታር እና አገልግሎት፣ የመሣሪያ ፋይናንስ አውታር፣ የክፍያ መጠየቂያ ፋይናንስ አውታር፣ B2B የኢንተርኔት ግብይት አውታር እና BMPL እና የእቃ ክምችት በማሳየት የሚፈጸም ብድር አሰጣጥ አውታሮች) የጥ.አ.መ.ኢ. ፍላጎቶችን የሚያሟሉ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለመንደፍ እና ለማበጀት ይጠቅማሉ። የኪፊያ አውታሮች፣ ያለዋስትና የሚሰጡ አዳዲስና በፈጠራ የታገዙ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት አማራጮችን ይደግፋሉ - በተለይ በሴቶች እና በወጣቶች ለሚመሩ፤ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ዘርፎች ለተሰማሩ ጥ.አ.መ.ኢ. የተነደፉ አገልግሎቶችን ያበረታታሉ።

- ለመደበኛ እና ኢ-መደበኛ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የሚሰጥ ዝቅተኛ የስራ ካፒታል ብድር
- የዲጂታል ጾታ ክፍተትን ለመፍታት ለሴቶች የሚሰጥ መሣሪያ በመጠቀም የሚሰጥ የፋይናንስ አገልግሎት/ዲቫይስ ፋይናንሲንግ
- ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ ለተባራሪ የሥራ መድረኮች (ለምሳሌ ድረ-ገጾች) እና ተባራሪ ሥራ ለሚሰሩ የሚሰጥ የእቃ ፋይናንስ
- የክፍያ መጠየቂያ በመጠቀም የሚሰጥ ፋይናንስ እና ለመካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ወጪ የሚውል ፋይናንስ
- ከወለድ ነጻ የሆኑ፣ ሸሪዓን ያማከሉ ልዩ ልዩ የባንክ አገልግሎቶች፦ ምሳሌ፣ ለመደበኛ፣ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ (ሳሊሃት) IFB//ኢስላማዊ ፋይናንስ፣ አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ (ThriveMaal) IFB//ኢስላማዊ ፋይናንስ፣ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ (Wasl) IFB/ኢስላማዊ ፋይናንስ።
- የመደበኛ፣ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የእሴት ሰንሰለት።

- ጥቃቅን፣ የእርሻ እና ሆርቲካልቸር (የአትክልት፣ፍራፍሬና አበባ) ኢንተርፕራይዝ ሥራ
- ጥቃቅን፣ የእርሻ እና የዶሮ እርባታ ሥራ
- ጥቃቅን፣ የንብ ማነብ እና በግና ፍየል ማድለብ ሥራ

ለተለያዩ የአገልግሎት ምድቦች፣ የዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ የምርት ማዕቀፍ፣ የብድር መጠን ገደቦችን፣ የቆይታ ጊዜን እና የወለድ መጠን ጣሪያዎችን በዝርዝር ይገልጻል። በሴቶች ለሚመሩ ጥ.አ.መ.ኢ. ቅድሚያ ለመስጠት ሲባል የኪፊያ ባንክ አጋሮች መጀመሪያ ላይ ሴቶችን ያማከሉ የአገልግሎት አማራጮችን አስጀምረዋል።

በ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ ውስጥ ያለው ቴክኖሎጂ፣ ባንኮች ይበልጥ ቀልጣፋ እና ፈጣን የብድር ሂደቶችን (በመነሻ፣ በሂደት፣ በማፅደቅ እና በማስተዳደር) በመጠቀም የስራ ማስኬጃ ወጪዎችን እንዲቀንሱ ያስችላቸዋል። የክሬዲት ነጥብ አሰጣጥ ስርዓቱ የአደጋ ግምገማ ለማካሄድ ይውሉ የነበሩ ወጪዎችን ይቀንሳል፤ ባንኮች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ተበዳሪዎች በተመሳይ ጊዜ እንዲያገለግሉ ያስችላቸዋል።

4. **የቴክኒክ ድጋፍ እና የባንኮች አቅም ግንባታ፡** ፕሮግራሙ በሥርዓት ደረጃ ለውጥ ለማምጣት በተዘጋጀው ባለ ሰባት ደረጃ ማዕቀፍ መሰረት ለባንኮች እና ለፊንቴክ የአቅም ግንባታ እና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል። ይህ በብድር ውጤት አሰጣጥ ላይ አቅም ግንባታን፣ በትብብር ምርት መፍጠርን፣ የንግድ ሞዴል አሰራር እና በለውጥ አስተዳደር ውስጥ ድጋፍ መስጠትን ይጨምራል። የፋይናንስ አገልግሎት ሰጪዎችን የውስጥ ፖሊሲዎች፣ ሂደቶች እና ስርዓቶች በማሻሻል፣ ይህ የቴክኒካል ድጋፍ ያለዋስትና የሚሰጥ ዲጂታል ብድር ውጤታማ እንዲሆንና በስፋት እንዲዳረስ ያደርጋል።

> ዕቅዱ ይተገበራል ተብሎ በታቀደው ጊዜ (2023-2027)፣ በድምሩ $1.2 ቢሊዮን ገንዘብ ለጥ.አ.መ.ኢ. ይለቀቃል ተብሎ ይታሰባል። ይህ ድጋፍ በ$300 ሚሊዮን መነሻ ይጀምራል፤ ፋውንዴሽኑ በሚያዋጣው እያንዳንዱ ዶላር፣ ባንኮች ተጨማሪ ሶስት ዶላር ያዋጣሉ፤ ይህም የ1፡ 3 ጥምርታ ይፈጥራል ማለት ነው። በዚህ አሰራር መሰረት፣ በመጀመሪያው አመት ፋውንዴሽኑ 75 ሚሊዮን ዶላር አስተዋፅዖ ያደርጋል። በምላሹም ተሳታፊ ባንኮች ተጨማሪ 225 ሚሊዮን ዶላር መዋጮ እዛ ላይ ይጨምራሉ። ይህ በመጀመሪያው አመት ለጥ.አ.መ.ኢ. የሚከፈለውን የገንዘብ መጠን ወደ 300 ሚሊዮን ዶላር ያደርሰዋል።

5. **የመሸጋገሪያ ጊዜ የገንዘብ ማግኛ ዘዴዎች እና ጊዜያዊ የብድር ዋስትና መርሀ ግብሮች፡** ፕሮግራሙ፣ ባንኮች፣ አዲስ ካሰባሰቡት ገንዘብ ውስጥ 10% መልሰው እንዲያከፋፍሉ የሚያበረታታ የሽግግር ጊዜ ገንዘብ ማግኛ ዘዴዎችን እና ጊዜያዊ የብድር ዋስትና መርሃ ግብሮችን ተግባራዊ አድርጓል። በ1፡3 ተዛማጅ መርህ እና በ50% የኪሳራ ዋስትና፣ ይህ ዘዴ ለብድር የሚውል 300 ሚሊዮን ዶላር ያስገኛል፤ ከ $1 ቢሊዮን ዶላር በላይ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ገንዘብም፣ ያለዋስትና በዲጂታል ብድር አሰጣጥ መሰረት ለጥ.አ.መ.ኢ ማከፋፈል ያስችላል።

6. **ቁጥጥርን ማጠናከር፡** ፕሮገራሙ፣ ያለዋስትና ማበደርን በሚመለከት ምርጥ ተሞክሮዎችን በማካፈል ከተቆጣጣሪዎች ጋር አብሮ ይሰራል፣ የድጋፍ ማዕቀፎች በስፋት እንዲተዋወቁ የማመቻቸት ስራ ይሰራል፤በአካታች ፋይናንስ አካባቢ እድገትን የሚያደናቅፉ እንቅፋቶችን ያስወግዳል።

**የ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ ተበዳሪ ጉዞ**

በ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ ፕሮግራም ውስጥ ላሉ አዲስ አመልካቾች፣ የብድር ሂደቱ ስድስት ደረጃዎችን ያካትታል:: በመጀመሪያ፣ አመልካቾች የKYC (Know Your Client)/ደንበኛህን እወቅ መረጃቸውን በኢንተርኔት ላይ ይጭናሉ:: አጋር ባንኮች ይህንን ካረጋገጡ በኋላ ያጸድቃሉ:: ይህን ተከትሎ፣ ተበዳሪዎች ስልጠና ይወስዳሉ (ይህ የወደፊት የሚተገበር ነው)፤ ከዚያ በኋላ የብድር ውጤት የሚወሰነው በደንበኛው ዲጂታል መተግበሪያ ውስጥ ባለው መረጃ ላይ ይሆናል:: በዚህ ውጤት ላይ በመመስረት ባንኮች የብድር መጠኑን በማዘጋጀት ገንዘቡን ዲጂታል አማራጮችን በመጠቀም ይሰጣሉ:: በአጋር ባንኮች ውስጥ ያሉ የጥ.አ.መ.ኢ. ተበዳሪዎች ብዙ ጊዜ ክሬዲትን ወዲያውኑ ማግኘት ይችላሉ ማለት ነው:: አዲስ አመልካቾች ግን መለያ ለማዘጋጀት ጥቂት ቀናት ሊያስፈልጋቸው ቢችልም ምንም ክፍያ አይጠየቁም:: የKYC መረጃን ለመጫን የሚያስፈልገው ብቸኛው መሳሪያ ስማርትፎን ብቻ ነው::

***ምስል 6፣ የተበዳሪው ጉዞ***




## 5.2. ለስኬት የሚያበቁ ቁልፍ ምክንያቶች

የክፍያ ቡድን፣ የዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ ፕሮግራም ትግበራ በበርካታ የስኬት ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ መሆኑን ዘግቧል::

**ውጫዊ የስኬት ምክንያቶች**

**1. ሊፈታ የሚችል የገበያ ክፍተት::** የኢትዮጵያ አ.መ.ኢ. ያጋጠማቸው ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ ክፍተት ከፍተኛ የገበያ እድል ፈጥሯል:: ይህ ክፍተት በ2021 ወደ 6.1 ቢሊዮን ዶላር ገደማ ይገመታል (የዓለም ባንክ፣ 2024):: ይህ በመሆኑም የኢትዮጵያ ባንኮች ይህን የፋይናንስ ተደራሽነት ድጋፍ ክፍተትን ለመፍታት ፍላጎት አላቸው:: የኢትዮጵያ ባንኮች የጥ.አ.መ.ኢ የብድር

መዋቅር እና ስትራቴጂ አላቸው። እነዚህ የብድር አወቃቀሮች እና ስትራቴጂዎች፣ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ሲሆን የዚህን ዘርፍ ልዩ ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት የተዘጋጁ የፋይናንስ ሞዴሎች የላቸውም። ጥ.አ.መ.ኢ. ለስራ እድል ፈጠራ ያላቸው ዕምቅ አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ፖሊሲ አውጪዎች ተስማሚ ደንቦችን እና የአስተዳደር ፖሊሲዎችን በማውጣት እንዲያድጉ ይጥራሉ።

**2. ተወዳዳሪ የባንክ መልክዓ ምድር:** ተወዳዳሪ የባንክ መልክዓ ምድር የተሻሻሉ የብድር ሞዴሎች ስራ ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ኪፊያ፣ ከ ኢ.ህ.ስ.ባ ጋር የጀመረው ሽርክና ስኬታማውን የሚቹ መድረክ እውን በማድረጉ በጣም አበረታቻ ነበር። አወንታዊ ውጤቶቹን በማየት ሌሎች ባንኮች ተመሳሳይ ሞዴሎችን ለመተግበር ከኪፊያ ጋር ለመተባበር ጉጉት አድሮባቸዋል። በኢትዮጵያ የዲጂታል ብድር አሰጣጥ ታሪክ፣ የኢ.ህ.ስ.ባ አመራር ቀዳሚ እንደመሆኑ፣ የአዳዲስ ተፎካካሪዎች ወደ መድረኩ መምጣትን ፈታኝም አጠናካሪም አድርጎ ተቀብሎታል። ውድድሩ በቀጣይነት የዲጂታል ብድር አውታሮችን እንዲያሻሽሉ፣ አማራጭ የብድር አሰጣጥን እንዲቀበሉ እና ያለዋስትና የሚሰጡ የብድር ሂደቶችን እንዲያዘምኑ ያደርጋቸዋል። ዳሽን ባንክም ከኢንዱስትሪ አቻዎች ልምድ መቅሰም ጠቀሜታ እንዳለው ይገነዘባል፣ ቀጣይነት ያለው ልማት ለማስፋፋት እንደሚረዳም ያምናል።

**ውስጣዊ የስኬት ምክንያቶች**

1. **የመረጃ ተደራሽነት:** ክፍያ በጊዜ ሂደት የዳበረ ከፍተኛ የሆነ የወጣት ስራ ፈጣሪዎች የመረጃ ቋት አዘጋጅቷል። እና የመረጃውን ጥራት ያለማቋረጥ እያሳደገ ይገኛል። ለምሳሌ፣ የተሻለ የተበዳሪዎች ፕሮፋይል ለማዘጋጀት የሳይኮሜትሪክ መረጃን እየተጠቀመ ይገኛል።
2. **የቡድን አቅም:** ኪፊያ በሶፍትዌር ልማት የተካነ ጠንካራ የቴክኖሎጂ ቡድን አለው። ቴክኖሎጂን ከመረጃ ትንተና ጋር በማጣመር፣ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ አሰጣጥ እንዲኖር ይሰራል።
3. **የገበያ ጥናትና ፍላጎትን ያማከለ የምርት ንድፍ:** ኪፊያ የጥአ.መ.ኢ ክፍሎች ዳሰሳዎችን ጨምሮ ሰፊ የገበያ ጥናት አድርጓል። የእነዚህ ጥናቶች ዓላማ የገበያ ፍላጎቶችን የሚያሟሉ፣ በልክ የተበጁ ምርቶችን መንደፍ እና ከፍተኛ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው።
4. **የግንኙነት አስተዳደር:-** ኪፊያ ለበርካታ አመታት የቆየ ጠንካራ የባንክ ለባንክ ግንኙነቶችን መስርቷል፣ ለምሳሌ፣ ለባንክ ተወካዮች የኬንያ ጉብኝት አመቻችቷል።

## 5.3. ያጋጠሙ ተግዳሮቶች/ ፈተናዎች

የ ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ ፕሮግራም፣ ያለዋስትና የሚሰጡ ዲጂታል የብድር ሞዴሎች ስላጋጠሟቸው ተግዳሮቶች ሰፊ ግንዛቤዎችን ይሰጣል። አካታች ፋይናንስን ለማስፋት እና የጥ.አ.መ.ኢ. እድገትን ለማፋጠን ፕሮገራሙ ብዙ ፈተናዎች ገጥመውታል።

- ለባንኮች የሚሰጥ የገንዘብ እና የብድር ዋስትና፡ አንዳንድ ባንኮች ለጥ.አ.መ.ኢ. ብድር የሚውል ተጨማሪ ገንዘብ በልበ ሙሉነት ለመመደብ በቂ የገንዘብ ማግኛ መፍትሄዎች እና የብድር ዋስትና ዘዴዎች ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ይህ ከተለምዷዊ ዋስትና-ተኮር ብድር ወደ ያለዋስትና የሚሰጡ ዲጂታል ብድሮች ከመሸጋገር ጋር ተያይዞ ያለውን ስጋት

ለመቆጣጠር ወሳኝ ነው:: እነዚህ መፍትሄዎችና ዘዴዎች ውጤታማ የሽግግር ማበረታቻዎች ሊሆኑ ቢችሉም፣ እነሱን አደጋ የመቀነሻ እርምጃ አድርጎ ከመጠን በላይ መታመን የሞዴሉን ቀጣይነትና የለውጥ ሀይልነት ዝቅ አድርጎ መገመት ይሆናል::

- የመረጃ ውስንነት፡- አስተማማኝ የክሬዲት መረጃን እና አማራጭ የመረጃ ምንጮችን በበቂ ሁኔታ አለማግኘት የተበዳሪውን አደጋ በትክክል ለመገምገም አስቸጋሪ ያደርገዋል፣ በተለይ ባንኮች እርስ በርሳቸው መረጃ አለመለዋወጣቸው ችግሩን ለመቅረፍ አስቻጋሪ ያደርገዋል:: ወጋገን ባንክ እንዳስገነዘበው የአስተማማኝ መረጃ እጥረት የብድር ብቁነትን የመወሰን ሂደቱን ያወሳስበዋል:: እንደ ክፍያ ያሉ የፊንቴክ ኩባንያዎች ቴክኖሎጂን በማጎልበት እና በሰው ሰራሽ አስተውሎት የተደገፈ የብድር ውጤት አሰጣጥ ስርዓቶችን በማስተዋወቅ ባህላዊ የብድር ወይም የግብይት ታሪክ በሌለበት ሁኔታ እንኳ ባንኮች የተበዳሪዎችን የብድር ብቃት ለመገምገም እንዲችሉ እየሰሩ ይገኛሉ:: ሆኖም የብሔራዊ መታወቂያ ሥርዓቱ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እስከሚሆን ድረስ አሁንም ክፍተቶች መኖራቸውን ማስተርካርድ ፋውንዴሽንና አዋሽ ባንክ አመልክተዋል:: ለምሳሌ ፋውንዴሽኑ በተለይ የግል መረጃ ሲቀየር ማንነቶችን የማጣራት ተግዳሮቶች እንደሚያጋጥሙ ጠቁሟል::
- **ውስን የዲጂታል እውቀት፡** ብዙ ጥ.አ.መ.ኢ. እና ተበዳሪዎች ዲጂታል አውታሮችን በብቃት ለመጠቀም ዕውቀት የላቸውም፣ ይህም የዲጂታል ብድር መፍትሄዎችን ለመለካት አስቸጋሪ ያደርገዋል:: የዲጂታል አገልግሎቶችን የማያውቁ ደንበኞች ተቃውሞም ሌላው ተጠቃሽ ነው::
- **በቂ ያልሆነ መሠረተ ልማት፣** የተገደበ የኢንተርኔት ግኑኝነት እና የዲጂታል መሠረተ ልማት፣ አገልግሎት በሌላቸው ክልሎች የስማርትፎን ተደራሽነት አለመኖር የመሳሰሉ ጉዳዮች ዲጂታል ክሬዲትን ለማስፋፋት እንቅፋት ይሆናሉ:: በተለይም በገጠር አካባቢዎች ዝቅተኛ የስማርትፎን ተጠቃሚነት የዲጂታል ብድር አቅርቦትን ይገድባል:: ኪፊያ፣ የስማርት ስልኮች መስፋፋት አሁንም ፈታኝ እንደሆነ አፅንዖት ሰጥቶ ያስረዳል:: ከ70% በላይ የሚሆነው ህዝብ የስማርት ስልኮች ተጠቃሚ አይደለም:: በተመሳሳይ ወጋገን ባንክ፣ የኢንተርኔት ግንኙነት ደካማ መሆን እና በገጠርም ሆነ አገልግሎት በማያገኙ አካባቢዎች የዲጂታል መሳሪያዎች አቅርቦት እጥረት፣ የዲጂታል ብድር አገልግሎት ለማዳረስ እንቅፋት እንደሆነ ገልጿል:: እንደ IFC ዘገባ (2020)፣ የኢትዮጵያ ባንኮች እና ማዕከላዊ ባንክ በዲጂታል መሠረተ ልማት ላይ ያለመስራታቸው ምክንያት ከማበረታቻ እጦት፣ የአቅም ውስንነት እና የግንዛቤ ማነስ ጋር የተያያዘ ነው::
- **የዋጋ** ንረት፡ በዋጋ ንረት ምክንያት የፋይናንስ ተቋማት የገንዘብ አቅም አሳሳቢ ሆኗል:: ንስር እንደጠቆመው፣ ለዚህ ምላሽ ይሆን ዘንድ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የብድር ወለድ መጠንን በመጨመሩ፣ ከማይክሮፋይናንስ ተቋማት ዝቅተኛ ወለድ የሚከፈልባቸው ብድሮችን ከባንክ ለማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነባቸው ጠቁሟል፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰ የሚሄደው የዋጋ መጨመርም ሌላው ገንዘብ ማግኘትን አስቸጋሪ ያደረገ ጉዳይ ነው::
- **የክሬዲት ጣሪያ፡-** ባንኮች ወይም ብድር አቅራቢዎች ለተበዳሪዎች ወይም ንግዶች በሚሰጡት የብድር መጠን ላይ በ ኢ.ብ.ባ የሚጣሉ ገደቦች የብድር አቅምን ይገድባሉ (በክፍል 4 የተገለጸውን የገንዘብ ፖሊሲ ማስተካከያ ይመልከቱ):: አቢሲኒያ ባንክ እና አዋሽ ባንክ በዚህ ጉዳይ ስጋታቸውን ገልጸዋል:: እንደ አዋሽ ባንክ፣ እነዚህን የብድር ጣሪያዎች ላላ ማድረግ የገንዘብ አቅማቸውን ባይጨምርም የማበደር አቅማቸውን እንደሚያጎለብትላቸው ገልጿል::

- **የአቅም ግንባታ እና ስልጠና፡-** የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ለዲጂታል ብድር ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የአቅም ግንባታ ስልጠና ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህ ስልጠና ለጥ.አ.መ.ኢ.ዎች የፋይናንስ እውቀታቸውን እና የንግድ ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ አቅም ይጨምራል፡፡ በተጨማሪም ዘ.ፋ.ተ.ሥ.ፈ. የመረጃ ሳይንስን ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ (አ.አ.ሳ.ቴ.ዩ.) እና ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ (አ.ሳ.ቴ.ዩ.) ሥርዓተ ትምህርት ጋር በማቀናጀት የወደፊት የመረጃ ሳይንቲስቶችን ለማፍራት ድጋፍ እያደረገ ነው፡፡ ኃላፊነት የሚሰማው እና ቀጣይነት ያለው የዲጂታል ብድር እድገትን ለማስፋፋት እንደ ተቆጣጣሪዎች እና የፋይናንስ ተቋማት ላሉት ሌሎች የስነ-ምህዳር ተዋናዮች ስልጠና ታቅዷል፡፡

## 6. የሞዴሉ የስነ-ምህዳር ተፅእኖ

‘የወጣት አፍሪካዊያን ይሰራሉ’ (Young Africa Works) ውጥኖች፣ በኢትዮጵያ መጀመር በፕሮግራሙ ትግበራ እና ስብሰባ ላይ በግሉ ሴክተር ፋይናንስ ያልሆኑ ተቋማት (የፋይናንስ ቴክኖሎጂ) እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና በመንግስት ሴክተር መካከል ተጨማሪ እና ጥልቅ ግንኙነቶችን አካቷል። ዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ፕሮግራም (SAFEE) ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የተደረገው የቴክኒክ ድጋፍ እና የለውጥ አስተዳደር ድጋፍ አጋር ባንኮች አሠራራቸውንና ፖሊሲያቸውን እንዲቀይሩ አስችሏቸዋል።

### 6.1. የታዩ የሴክተር ልምምድ ለውጦች

#### የብድር ፖሊሲ ለውጥ

አጋር ባንኮች ከባህላዊ የብድር ውጤት መስጫ በተጨማሪ እንደ ግብይት ታሪክ እና የባህሪ መረጃ ያሉ አማራጭ የመረጃ ምንጮችን ለማካተት የብድር ግምገማ ሂደታቸውን አስተካክለዋል። ለምሳሌ፣ የኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ የአደጋ ቅነሳን፣ የአሰራር ቅልጥፍናን እና የቁጥጥር ተገዢነትን ለማረጋገጥ ለ’ሚቹ’ ዲጂታል ብድር መስጫ አውታር የተለየ የብድር አሰራር አዘጋጅቷል። ወጋገን ባንክም የብድር ፖሊሲውን በማዘመን ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ያለዋስትና ብድር መስጠትን ያካተተ፣ ሲሆን ዘምዘም ባንክ ከወለድ ነፃ የባንክ ፖሊሲ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ጋር በማጣጣም አዘጋጅቷል።

በሌላ በኩል፣ አጋር ያልሆኑ ባንኮች ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ ተደራሽነትን ማሳደግ ላይ ትኩረት ከሚያደረጉት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ጋር ለማጣጣም የብድር ፖሊሲዎቻቸውን በተለያየ ደረጃ አስተካክለዋል። ለምሳሌ፣ የአቢሲኒያ ባንክ የብድር ፖሊሲውን ወደ አፖሎ ያለዋስትና ዲጂታል አውታር አሻሽሎታል። በተመሳሳይ ሁኔታ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ብርሃን ባንክ፣ ኦሮሚያ ባንክ እና ንብ ባንክ የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችን በመከተል የፖሊሲ ማሻሻያ አድርገዋል። በተለይም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ትኩረቱን ከመንግስት ወደ ግሉ ዘርፍ አበዳሪነት በማሸጋገር ላይ ሲሆን፣ በተለይም የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ብድሮች ላይ በማተኮር እና በቂ አገልግሎት የሌላቸውን ህዝቦች ኢላማ በማድረግ ላይ ይገኛል።

#### የዘመነ የብድር ሂደት

የብድር አሰጣጥ ሂደቶች የተለመዱ መስፈርቶችን በመተካት ብድርን ለማጽደቅ የሚረዱ አውቶሜሽን፣ ቴክኖሎጂ እና በመረጃ የተደገፉ ሞዴሎች በማካተት ተሻሽለዋል። አጋር ባንኮች ሰው ሰራሽ አስተውሎት መሳሪያዎችን እና ዲጂታል አውታሮች በመጠቀም በዋስትና ላይ ከተመሰረተ ብድር ወደ በመረጃ የተደገፈ ብድር ተለውጠዋል። ቴክኖሎጂ፣ ባንኮች አማራጭ ብድር ነጥብ መስጫ እና የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በማዋሃድ ግለሰቦችን እና ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን እንዲገመግሙ ያስችላቸዋል። ለምሳሌ፣ እናት ባንክ ከዋስትና

ይልቅ በመረጃ እና በተሞክሮ ላይ የተመሰረተ አማራጭ የብድር ምዘና ሞዴሎችን ተቀብሎ የዲጂታል ብድር ሂደቱን አሻሽሎ ዲጂታል አውታሮችን እና አውቶሜሽን በማዋሃድ ቅልጥፍናን እና ተደራሽነትን ለማሳደግ ችሏል። የብድር ሂደት ውጤታማነትን ለማረጋገጥ፣ የኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ የግብይት ታሪክን፣ የዲጂታል አሻራን እና የደምበኛ ባህሪን ይጠቀማል።

በተመሳሳይ፣ የወጋገን ባንክ የዲጂታል ብድር ፕሮግራሞች ትርፋማነት እና ተስፋፊነት እውቅና፣ ወደ ዲጂታል ብድር ሞዴሎች ያለውን አዝማሚያ ያሳያል። ዳሽን ባንክ ከኤግልላየን (EagleLion) አሰራር ቴክኖሎጂ ጋር በ'ዱቤፔይ' አሁን ይግዙ፣ በኋላ ይክፈሉ የሞባይል መተግበሪያ ጋር ትስስር ፈጥሯል። የአቢሲኒያ ባንክ የማይክሮ ብድር ባህሪያት ያለውንና አፖሎ ዲጂታል የባንክ አውታር ለመተግበር ሙከራ ላይ ነው። 'አሌኝታ' ሌላው በአንበሳ ባንክ የተዘጋጀ የማይክሮ ብድር መተግበሪያ ነው። በተጨማሪም SNV ከKMD ለንደን (የአማካሪ ድርጅት) ጋር በመተባበር በሶስት ባንኮች (አዋሽ ባንክ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አሃዱ ባንክ) በኩል ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ዲጂታል የብድር መተግበሪያን ለመክፈት እየሰራ ነው።

ከአጋሮች ጋር በመተባበር እና የዲጂታል አውታሮችን በመቀበል የሚመራው ይህ ለውጥ ፈጣን ውሳኔዎች እና ሰፋ ያለ ውህደት እንዲኖር አስችሏል፤ በተለይ አገልግሎት ለሌላቸው ቡድኖች። እናም አውቶሜሽን እና የበለጠ ተለዋዋጭ የዋስትና መስፈርቶች ውህደት ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ቅልጥፍናን እና ተደራሽነትን አሳድጓል።

## ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጠው የብድር መጠን እና ፋይዳ መጨመር

የአጋር ባንኮች ተጨማሪ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ለማካተት የብድር መረጃ ስብስቦችን (portfolios) እያሰፋ ነው። የኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጠውን የብድር ክፍያ መጠን በከፍተኛ ደረጃ ያሳደገ ሲሆን፣ ይህም ቀደም ሲል በኮርፖሬት ብድር ላይ ከነበረው ስትራቴጂካዊ ለውጥ መኖሩን ያሳያል። ይህ ለውጥ ባንኩ ለጥቃቅንና አነስተኛ እንተርፕራይዞች ዘርፍ እድገት ያለውን ቁርጠኝነት ያመላክታል። ለምሳሌ፣ የኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ የጥቃቅንና አነስተኛ ብድር አቅርቦት ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። ይህም እኤአ በ2021 ከጠቅላላ ብድራቸው 13% የነበረ ሲሆን፣ በ2024 ወደ 67% አሳድጓል[21]። ይህ ጥምርታ እኤአ በ2021/22 ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ተሰጥቶ ከነበረው 1.52% አገራዊ አማካይ ብድር በእጅጉ የላቀ ነው[22]። በተጨማሪም በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ (ከሀምሌ 1 2024 እስከ ታህሳስ 31 2024) (እኤአ) የኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ 8.7 ቢሊዮን ብር ለ579,494 አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና 5.18 ቢሊዮን ብር ለ220 ኮርፖሬት ኩባንያዎች ሰጥቷል[23]። ይህ መረጃ በባንኩ የብድር ስትራቴጂ ውስጥ ጉልህ ለውጥ መኖሩን እንዲሁም፣ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ የሚሰጠውን ትኩረት ያሳያል።

ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚቀርበውን የብድር አቅርቦት ጥምርታን አስመልክቶ፣ የዘላቂ የፋይናንስ ተደራሽነት ለስራ ፈጠራ ፕሮግራም አጋር ባንክ (የኦሮሚያ

[21] *ቁልፍ መረጃ ሰጪ ከኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ ጋር*

[22] https://www.thereporterethiopia.com/27289/

[23] *ከፍያ መረጃ*

ህብረት ሥራ ባንክ) አጋር ካልሆነው ባንክ (ብርሃን ባንክ) ጋር ያለው ንፅፅር ከፍተኛ ልዩነት ያሳያል። የኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያደርገው የብድር አቅርቦት ከፍተኛ እና እያደገ የመጣ መሆኑን በቋሚነት እያሳየ ሲሆን፣ ይህም ባንኩ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ጠንካራ ድጋፍ ያለው መሆኑን ያመላክታል። በአንፃሩ የብርሃን ባንክ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ብድር አቅርቦት ዝቅተኛ እና እየቀነሰ የመጣ ሲሆን፣ ይህም ባንኩ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ያለው ትኩረት ወይም የተመደበው ግብአት አናሳ መሆኑን ያሳያል። ይህ ክፍተት የሚታወቅ ቢሆንም፣ ሌሎች ነገሮች በውጤቶቹ ላይ ተጽዕኖ እያሳደሩ በመሆናቸው የኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክን የአቅርቦት እድገትን በፋውንዴሽን ፕሮጀክት ላይ ብቻ ማጠቃለል ከባድ ነው።

## የብድር ስጋት አስተዳደር ማሻሻል

ባንኮች ለተሻሻለ የብድር ስጋት ክትትል እና ግምገማ፣ የእውነተኛ ጊዜ መረጃ አሰባሰብ እና ትንታኔን በማቀናጀት፣ የብድር ስጋት አስተዳደር ስርዓቶቻቸውን እያሳደጉ ነው። ለምሳሌ፣ እናት ባንክ ይህ ማሻሻያ የተበዳሪውን አስተማማኝነት እና የመክፈያ አቅሙን በብቃት እንዲገመግሙ እንዳስቻላቸው ገልጸዋል፤ በተለይ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ባህላዊ የብድር ታሪክ ለሌላቸው ሴት ስራ ፈጣሪዎች ጥቅሙ የጎላ ነው።

ወጋገን ባንክም እንዲሁ ለዲጂታል ብድር ሥራቸው የብድር ውጤት መስጫን መሠረት ያደረገ የአደጋ አስተዳደር ሥርዓት መተግበሩን ዘግቧል። ይህም ስርዓት የሚከተሉትን ለማከናወን ያስችላቸዋል፡- ሀ) በመረጃ የተደገፈ ስልተ ቀመሮችን በመጠቀም የብድር ብቃትን ለመገምገም፣ ለ) ከፍተኛ ስጋት የሆኑትን ተበዳሪዎች በመለየት እና የብድር ውሎችን በዚሁ መሠረት በማበጀት ለስጋት ተጋላጭነትን ለመቀነስ፣ እና ሐ) ለፈጣን ውሳኔዎች እና የላቀ የደንበኛ ልምድ የብድር ግምገማን በቴክኖሎጂ ለማዘመን።

## የዲጂታል ብድር ክፍል ወይም ዘርፍ ማቋቋም

አጋር ባንኮች ያለዋስትና የሚፈጸም ዲጂታል ብድርን ለማበረታታት የተለያዩ ድርጅታዊ መልሶ ማዋቀር አከናውነዋል። መጀመሪያ ላይ ለዲጂታል ብድር የሚሆን አነስተኛ ክፍል የነበረው ኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ የቴክኒክ ድጋፍ መጀመሩን ተከትሎ ቡድኑን ወደ 200 ሰዎች አሳድጓል። ይህ የማስፋፊያ ስራ ባንኩ በትራንስፎርሜሽን እና በአዲስ መልክ በማደራጀት የታጀበ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን፣ በአሁን ጊዜ 50% የሚሆነውን የብድር መጠኑን ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ለአነስተኛ አርሶ አደሮች እየሰጠ ነው። በተመሳሳይ ቡና ባንክ 20 ሰራተኞች ያሉት የዲጂታል ብድር አሰጣጥ ክፍል ያቋቋመ ሲሆን፣ እናት ባንክ በምክትል ፕሬዚዳንት ደረጃ የሚቆጣጠረውን የዲጂታል ብድር ክፍል አቋቁሟል።

ከዲጂታል የብድር ክፍሎች ወይም መምሪያዎች ምስረታ በተጨማሪ፣ የሰራተኞች አቅም በስልጠና እና በእውቀት ሽግግር ማሳደግ ተችሏል። ለምሳሌ፣ ከቡና ባንክ የመጣ አንድ ቁልፍ መረጃ ሰጪ እንደገለጸው፣ "የክፊያ ቴክኖሎጂ የተለያዩ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት እና ከ13 በላይ ለሆኑ ግለሰቦች የውጭ ሀገር ጉብኝት በማመቻቸት ለዚህ ክፍል የሰው ሃይል ድጋፍ አድርጓል።"

### የምርት ብዝኃነትን ማሳደግ

በክፊያ ቴክኖሎጂ የተደረገው የቴክኒክ ድጋፍ እንደ ሚቹ ትግበራ ፋይናንስ አሰራር እና መጠየቂያ በመጠቀም የሚሰጥ የፋይናንስ አገልግሎት (invoice financing) ያሉ አገልግሎቶች መጀመር ላይ እስታዋጽኦ አድርጓል። በተመሳሳይ፣ ወጋገን ባንክ ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡ ያለዋስትና ብድሮች እና በሴቶች ላይ ያተኮረ የፋይናንስ አሰራር የመሳሰሉ አግልግሎቶችን በአጋሪነት መፍጠር ላይ ተሳትፏል። እነዚህ ምርቶች የባንኩን አቅርቦቶች በማስፋፋት፣ አገልግሎት ለማያገኙ ክፍሎች የፋይናንስ አቅርቦት ክፍተቶችን ቀርፏል።

## 6.2. በፖሊሲና ተግባር ላይ ለታዩ ለውጦች አስቻይ ምክንያቶች

በፋይናንስ ሴክተሮች ውስጥ በርካታ ምክንያቶች የፖሊሲ፣ የተግባር እና የአሠራር ለውጦች መፈጠር ምክንያት ሆነዋል። ከእነዚህ መካከል በመጀመሪያ ደረጃ የመንግስት የፖሊሲ ማሻሻያዎች እና እርምጃዎች ናቸው። የቅርብ ጊዜ የመንግስት ፖሊሲዎች፣ በተለይም የፋይናንስ አካታችነትን፣ ዲጂታል ፋይናንስን እና የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍን የሚያበረታቱ ፖሊቺዎች፣ ባንኮች የፋይናንስ ተደራሽነታቸውን ለማሳደግ እንዲሰሩ አነሳስቷቸዋል። የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ ስትራቴጂያዊ አቅጣጫውን በመምራት ረገድ እነዚህ ፖሊሲዎች ለሚጫወቱት ወሳኝ ሚና እውቅና ይሰጣል። በተመሳሳይ፣ ወጋገን ባንክ በተለይ በዲጂታል ብድር ውስጥ ስትራቴጂካዊ እና ተግባራዊ ለውጦችን ለማስቀጠል ጠንካራ የቁጥጥር ማዕቀፍ አስፈላጊ መሆኑን አጽንኦት ሰጥቷል። የመንግስት ድጋፍ ከሌለ እንደዚህ አይነት ጥረቶች ህጋዊነትን፣ ተስፋፊነትን ወይም የረጅም ጊዜ አዋጭነትን ለማግኘት ይታገላሉ ሲሉ ይከራከራሉ።

ሌሎች የዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ፕሮግራም እንሼቲቭ አጋር ያልሆኑት ባንኮች፣ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ብርሃን ባንክ፣ ንብ ባንክ እና የኦሮሚያ ባንክ፣ የፋይናንስ ሴክተሩን ከገንዘብ ተኮር ወደ ዲጂታል ሲስተም ለማሸጋገር፣ በብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ እና ብሔራዊ ዲጂታላይዜሽን ስትራተጂ ምሳሌነት የታየውን የመንግስት ድህረ-2018 እንቅስቃሴን አድንቋል። እንደ ክፊያ ፋይናንስ ቴክኖሎጂ እና ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ያሉ የውጪ አጋሮች ሚና የገበያ አሰራር ለውጦችን ለማድረግ ትልቅ አስተዋፅዖ አድርጓል። ይህንንም ድጋፍ ያደረጉት፣ አማራጭ የብድር ምዘና ስልቶችን፣ የቴክኒክ ድጋፍን፣ የአቅም ግንባታን፣ የምርት እድገት ፈጠራን፣ ዲጂታል የብድር አውታሮችን እና የአደጋ መጋራት ዘዴዎችን በማቅረብ ነው። እነዚህ አስታዋጽኦዎች ባንኩ ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያቀርበውን የብድር አሰራር በዋስትና በሚፈጸም የብድር አሰራር ወደ ያለዋስትና የብድር አገልግሎት እንዲሸጋገር በማድረግ፣ የፋይናንስ አካታችነት ክፍተቶችን ለመቅረፍ እና በቂ አገልግሎት ለሌላቸው ማህበረሰብ ለመድረስ አስችሎታል።

## 7. ስነ-ምሕዳራዊ አንድምታዎች

የዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ፕሮግራም አጋር ባንኮች አሰራሮች አጋር ባልሆኑ ባንኮች አጋር ባልሆኑ ባንኮች ውስጥ በማሳያ ተፅዕኖ የፖሊሲ ለውጦችን እና የአሠራር ለውጦችን ለማነሳሳት ምሳሌ ሆነዋል። በተጨማሪም፣ የፋይናንስ ተዋናዮች ስለ ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ያላቸውን የግንዛቤ ለውጥ እንዲያመጡ እና የበለጠ አዎንታዊ አመለካከትን እንዲያጎለብቱ የዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ፕሮግራም ሞዴል አስተዋፅዖ አድርጓል።

### 7.1. በፋይናንስ ዘርፍ ውስጥ ያሉ አወንታዊ፣ ውጫዊ ሁኔታዎች

**የአስተሳሰብ ለውጥ**

**በአቅርቦት በኩል ያሉ ለውጦች**

የዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ፕሮግራም ያለዋስትና የዲጂታል ብድር ሞዴል በፋይናንስ ዘርፍ ተዋናዮች እና ፖሊሲ አውጪዎች መካከል ስለ ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች የበለጠ አዎንታዊ ግንዛቤን ፈጥሯል፡- ይህንንም ለማጉላት ከአዋሽ ባንክ አንድ ቁልፍ መረጃ ሰጪ እንዲህ ብሏል፣

> "ከዚህ በፊት ወጣቶች ብዙውን ጊዜ ከልምድ ማነስ ጋር ይያያዛሉ፣ ነገር ግን በወጣት ስራ ፈጣሪዎች ላይ መዋእለ ነዋይ ማፍሰስ ትርፋማ መሆኑን አይተናል። ለውጡም፣ ሰፊ የብድር ታሪክ ወይም ቁሳዊ ሀብት ባይኖራቸውም ወጣት ስራ ፈጣሪዎችን በብቁ ተበዳሪነት እንዲመለከት ተቋሙን አበረታቶታል።"

አንድ የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ ቁልፍ መረጃ ሰጪ፣ ባንኩ ባለፉት 4 እስከ 6 ዓመታት ውስጥ በጥሩ ሁኔታ የተነደፈውን ዲጂታል ስትራቴጂ አስመልክቶ ከወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ጋር ያስመዘገበው ስኬት እና ባጠቃላይ ሥነ-ምህዳሩን በመሠረታዊነት ያሻሻለውን ሂደት አድንቋል። በተለይም በመረጃ ላይ የተመሰረተ የብድር ግምገማ መወሰዱ ተቋማቱ ወጣት ስራ ፈጣሪዎች ሰፊ የፋይናንስ ታሪክ እና ንብረት ባይኖራቸውም፣ እንደ ውጤታማ የብድር ተጠቃሚዎች እንዲመለከቱዋቸው እያስቻላቸው ነው። ወጋገን ባንክም ሲገልጽ፡ "ከዚህ በፊት ለወጣት ስራ ፈጣሪዎች ብድር መስጠት ከፍተኛ ስጋት ያለው ስራ ተደርጎ ይታይ ነበር። እንደ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ባሉ የውጭ ተዋናዮች የተደገፈው አዲሱ የዘርፉ አሰራር ይህንን ግንዛቤ ቀይሮታል። ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች አሁን ከፍተኛ የእድገት አቅም ያለው ያልተነካ የገበያ ዕድል ተደርገው ተወስዷል።"

የቡና ባንክ ቁልፍ መረጃ ሰጪም እንዲህ ብሏል፡

> "ከፕሮጀክቱ ዋናው ውጤታማ ትምህርት አመራሮቻችንን ግንዛቤ አስጨብጧል። ማስተርካርድ የከፍተኛ መሪዎቻችንን አስተሳሰብ ወደ አዲሱ የፋይናንስ አቀራረብ ይለውጣል።" በመረጃ የተደገፉ የብድር ግምገማዎች ለወጣት ሥራ ፈጣሪዎች፣ ውስን የፋይናንስ ታሪክ ወይም ንብረት ላላቸውም ጭምር፣ የማበደር ስጋትን/አደጋን እየቀነሱ ናቸው። እነዚህ ሥራ ፈጣሪዎች አሁን ከፍተኛ ስጋት ከመሆን ይልቅ፣ ከፍተኛ የማደግ

አቅም ያለው ተስፋ ሰጪ ገበያ ሆነው መገኘታቸው ከፍተኛ ለውጥ መኖሩን ያመላክታል ሲል ወጋገን ባንክ ገልጿል፡፡

አሁን አሁን ለወጣት ስራ ፈጣሪዎች ብድር መስጠት እንደ ትርፋማ ስራ ሆኖ ተስተውሏል፡፡ አዋሽ ባንክ እንደገለጸው፣ የካበተ ልምዳቸው እነዚህ ግለሰቦች ባህላዊ የብድር መያዣ ሳይኖራቸው እንኳ ብቁ ተበዳሪዎች መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡ በተመሳሳይ፣ ወጋገን ባንክ የማይመለስ ብድር መጠን ከ1% በታች ዝቅ ማለቱ የዲጂታል ብድር ሞዴሎችን ስኬት አጉልቶ ያሳያል፣ ይህ ደግሞ በወጣት ስራ ፈጣሪዎች የብድር አጠቃቀም ብቃት ላይ ያላቸውን እምነት ያሳድጋል፡፡ በአጠቃላይ ባንኮች ስለ ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ያላቸው አመለካከት ቢቀየርም፣ የኮርፖሬት ብድር መስጠት የበርካታ ባንኮች ተመራጭ ትኩረት እንደሆነ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገልጿል፡፡

## በፍላጎት በኩል ያሉ ለውጦች

የትኩረት የቡድን ውይይቶች (FGDs) እንደሚያሳዩት ከሆነ፣ ያለዋስትና ዲጂታል ብድር አሰጣጥ ሂደት ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ስለ ባንኮች ያላቸውን አመለካከት በአዎንታዊ መልኩ ለውጦታል፡፡ ተጨማሪ የፋይናንስ ዕድሎችን ለመፈተሽ የበለጠ ግልጽነት መኖሩን ተሳታፊዎች ጠቁመዋል፡፡ በተጨማሪም ሁሉም የትኩረት የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች በፋይናንስ ተቋማት ለወጣት ስራ ፈጣሪዎች ያላቸው አመለካከት ከፍተኛ ለውጥ ማሳየቱን ገልጸዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ባንኮች ቀለል ባለ መስፈርት ስለ አዳዲስ የብድር አማራጮች አስቀድሞ ግንዛቤን በማሳደግ በጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የመክፈያ አቅም ላይ እምነት እንዳላቸው አሳይተዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው በኢትዮጵያ ከፍተኛ የስነ-ምህዳር ለውጥ መኖሩን ሲሆን፣ የፋይናንስ ተቋማቱ የድርጅት ብድርን ለማከናወን ከረጅም የሂደት አማራጭ እየወጡ መሆኑን ያሳያል፡፡

## 7.2. ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎች እና የገበያ መዛባት

የፕሮግራሙ ዘላቂነት፣ መስፋፊት መቻሉ እና መደገም መቻሉ የረጅም ጊዜ ስኬቱን የሚወስኑት ወሳኝ ኩነቶች ናቸው፡፡ እንደ ምላሽ ሰጪዎች ሀሳብ፣ ከሚጠበቁት አደጋዎች መካከል አንዱ የዘላቂነት ስጋት ነው፡፡ ፕሮግራሙ ሊደገም እና ወደ ሌሎች ባንኮች ሊስፋፋ እንደሚችል የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ያምናሉ፣ ነገር ግን አንድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቁልፍ መረጃ ሰጪ በ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራም በኩል በፋይናንስ ሴክተሮች ላይ የተደረጉ ለውጦች ከፕሮግራሙ ማብቂያ በኋላ እንደሚቆዩ ጥርጣሬውን ገልጸዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አንዱ ቁልፍ መረጃ ሰጪ ሲገልጽ፡

"በፋይናንስ ሴክተሮች ላይ ያሉት ለውጦች ያለ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ድጋፍ ዘላቂነት እንደማይኖራቸው መገመት እችላለሁ፣ እናም በ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራም ድጋፍ ምክንያት የፋይናንስ ሴክተሮች ስኬት ምን ያህል እንደሆነ ለማየት ተጨማሪ ምርምር ያስፈልጋል ብዬ አስባለሁ፡፡"

ከባንኮች ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች እንደገለጹት ከሆነ፣ ተበዳሪዎች ከተለያዩ አበዳሪዎች ብዙ እዳዎችን ሲለሚያከማቹ፣ ተመልሶ ያለመከፈል ዕድሉ ይጨምራል፡፡ ይህ በተለይ ለሚሰጠው የብድር መጠን ምንም አይነት የንብረት መያዣ ለማይደረግበት ያለዋስትና ለሚሰጡ ብድሮች ችግር ነው፣ ምክንያቱም ተበዳሪዎቹ ዕዳቸውን መክፈል ካልቻሉ አበዳሪዎቹ ለአደጋ ተጋላጭ ይሆናሉ (Smith, 2020)፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ተበዳሪዎች የቆዩትን ዕዳዎች

ለመክፈል ሲሉ አዲስ ብድር በመውሰድ እራሳቸውን በእዳ አዙሪት ውስጥ ሊያገኟቸው ይችላሉ። ይህም ከገንዘብ ችግር አልፎ ተርፎም ለኪሳራ ይዳርጋቸዋል። ለምሳሌ እናት ባንክ እንዲህ ብሏል "

"ተበዳሪዎች፣ ከመጠን በላይ ወደ ባለዕዳነት የሚመራቸውን ብድር ከበርካታ ባንኮች ሊያገኙ ይችላሉ። እናም እንደ ገንዘብ ማስገኛ አገልግሎቶች ባሉ ውጫዊ ሀብቶች ላይ ሙሉ በሙሉ መታመን የአጭር ጊዜ ትርፍ ያስገኛል፣ ነገር ግን የረጅም ጊዜ ዘላቂነትን ሊጎዳ ይችላል።"

በተመሳሳይ፣ ከባንኮች የተሳተፉት ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ከሆነ፣ ማስፋፋት ሁኔታ እና ተሸጋሪነት ሊሳኩ የሚችሉ ቢሆንም፣ ነገር ግን የፕሮግራሙ ዘላቂነት በገንዘብ መገኘት ላይ የተመሰረተ ነው። ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር አቅርቦት ላይ ለውጥ እንዳለ፣ ባንኮችም የእነዚህን ኢንተርፕራይዞች አቅም እንደሚገነዘቡ አዋሽ ባንክ ገልጿል። ሆኖም፣ ያለ በቂ ገንዘብ ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ አቅርቦት ዘላቂነት አጠያያቂ እንደሆነ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ገልጸዋል። የባንክ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎችም አደጋ መጋራትን ማቆም የብድር መረጃ ስብስቦችን እንደሚቀንስ እና በመጨረሻም ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚደረገውን ድጋፍ እንደሚቀንስ ገልጸዋል። በተመሳሳይ፣ ባንኮችም በፋይናንስ ሥነ-ምህዳር ውስጥ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ አስታዋጽኦን በፍጥነት መቀበል የገበያ መዛባት እና አደጋዎችን ሊያስከትል እንደሚችልም ጠቁመዋል።

**የወለድ ተመን ልዩነቶች፡** የወለድ ተመኖች በአሁኑ ጊዜ በገበያ ውስጥ ካለው አደጋ ጋር አልተጣጣሙም። ቁልፍ መረጃ ሰጭዎች የዲጂታል ብድር ፈጣን እድገት በባህላዊ እና ዲጂታል ብድር አሰራር መካከል የወለድ ተመን ልዩነት እንዲፈጠር ሊያደርግ እንደሚችል ስጋታቸውን ገልጸዋል። ይህ ደግሞ አገልግሎት የማያገኙትን ወገኖች ይበልጥ ተጎጂ ያደርጋቸዋል። ዲጂታል አበዳሪዎች የብድር ብቃትን/አዋጭነትን ለመገምገም አማራጭ ዳታ እና ስልተ-ቀመሮችን/አሰራረሮችን ይጠቀማሉ፣ እናም ብዙ ጊዜ ውስን የብድር ታሪክ ያላቸውን ጨምሮ ለአደጋ ተጋላጭ ተበዳሪዎች (አገልግሎት ለማያገኙ ቡድኖች) ከፍተኛ የወለድ ክፍያ ያስከፍላሉ። ባህላዊ አበዳሪዎች፣ በመደበኛ የብድር ታሪክ ላይ በመመስረት፣ ለተቋቋሙ ተበዳሪዎች (ኮርፖሬት) ዝቅተኛ የወለድ ተመኖችን ሊያቀርቡ ይችላሉ። ይህ ምልከታ ከZhang (2021) እና Smith (2020) ግኝቶች ጋር ይስማማል።

**የማጭበርበር እና የሳይበር ደህንነት ስጋቶች፡** በዲጂታል አውታሮች ላይ ያለው ጥገኝነት እያደገ መምጣቱ፣ በተለይም አሁን ካሉ የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነቶች አንፃር፣ የመረጃ ጥሰት ስጋትን ይጨምራል። ጠንካራ የደህንነት እርምጃዎች ካልተወሰዱ፣ ዲጂታል የብድር ሂደቶች ለማጭበርበር እና ለአላግባብ መጠቀም አጋጣሚዎች በጣም የተጋለጡ ናቸው (McKinsey, 2020)። እናት ባንክ፣ ይህ የዲጂታል ጥገኝነት መጨመር በማጭበርበር እና በሳይበር አደጋዎች ገበያውን ሊያዳክም እንደሚችል ያስጠነቅቃል።

**የመልሶ መክፈል ሂደት ተግዳሮቶች፡** ከበርካታ ባንኮች ብድር የሚያገኙ ተበዳሪዎች ከአቅም በላይ ባለዕዳ በመሆናቸው ምክንያት፣ የመልሶ መክፈል አለመቻል አደጋ ያጋጥማቸዋል። ተበዳሪዎች አዳዲስ ብድሮችን በመጠቀም ነባር ዕዳቸውን ስለሚከፍሉ፣ ወደ ዕዳ አዙሪት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ይህም የገንዘብ ችግር እና ኪሳራ ያስከትልባቸዋል። ይህ አደጋ በተለይ ያለ መያዣ

ለሚፈጸሙ ብድሮች በጣም ከባድ ነው። ምክንያቱም፣ አበዳሪዎች የንብረት መያዣ ስለሌላቸው እና ገንዘባቸውን ያለማግኘት ዕድል ስለሚገጥማቸው (Smith, 2020)። ይህ በበርካታ ብድሮች እና የውጭ ገንዘብ ማስገኛ ስልቶች ላይ ጥገኛ መሆን የአጭር ጊዜ ትርፍ ቢያገኝም የረጅም ጊዜ ዘላቂነትን አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑን የእናት ባንክ ያስጠነቅቃል። ከዚህም በላይ በቂ የሆነ የተበዳሪ ትምህርት አለመኖር፣ የመልሶ መክፈል አደጋን ይጨምራል። ያለበቂ የተጠቃሚ ትምህርት፣ ፈጣን ያለዋስትና የብድር ዕድገት የመልሶ ክፍያ ችግር እንደሚያስከትል እናት ባንክ አመልክተዋል። በተለይም ብዙ የገጠር ተበዳሪዎች ስለ ብድር ውሎች እና የዕዳ አያያዝ ሙሉ ግንዛቤ ስለሌላቸው ለመልሶ መክፈል ችግር ይጋለጣሉ[24]።

**በከተማና በገጠር መካከል ያሉ ክፍተቶች፡** ቁልፍ መረጃ ሰጭዎች በኢትዮጵያ የገጠር ተደራሽነትን የሚገድበው የዲጂታል አገልግሎት ከተማን ማዕከል ያደረገ መሆኑን አጉልተው አሳይተዋል። ይህ ግኝት የገጠር የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ዝቅተኛ በሆነባቸው አንዳንድ ታዳጊ አገሮች ላይ Agwu (2021) ካደረገው የዲጂታል ብድር ጥናት ጋር የሚጣጣም ነው።

ለምሳሌ፣ የወጋገን ባንክ ምንጮች የዲጂታል ብድር ተደራሽነት ለከተሞች ያደላ በመሆኑ፣ የገጠር ህዝብን ያለአገልግሎት አስቀርቷቸዋል፣ የገበያ መዛባትንም ፈጥሯል።

**የቁጥጥር ስርዓት ክፍተቶች፡** ለዲጂታል ብድር ቀጣይነት ያለው የቁጥጥር ስርዓት እድገት ቢኖርም፣ የዲጂታል እድገት ፈጣን እርምጃ የስርዓቶች መሻሻል አደጋን ይፈጥራል። ይህም ውጤታማነትን ይቀንሳል። እንደ WEF (2022) እና IMF (2021) ያሉ ጥናቶች በዚህ አደጋ መፈጠር ይስማማሉ፡

ያልተመጣጠነ ውድድር፡ የማሳያ ውጤቱ ጤናማ ውድድርን እና በብዙ ባንኮች ላይ ያለዋስትና ዲጂታል ብድር ስርዓትን እድገትን ቢያመጣም፣ በትልልቅ ተቋማት የሚወስዱት ከባድ ብድር በትናንሽ ባንኮች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ከባንክ የመጡ ቁልፍ መረጃ ሰጭዎች ስጋታቸውን ገልጸዋል። በተጨማሪም፣ ፈጣን የዲጂታል ብድር እድገት የገበያ ሙሌት፣ የዋጋ ግፊቶችን እና የአበዳሪ ትርፋማነት መቀነስን ሊያስከትል ይችላል (Liu, 2020)።

**በውጫዊ ድጋፍ ላይ ከመጠን በላይ ጥገኛ መሆን፡** ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ብድር የገንዘብ ማስገኛ መፍትሄዎች እና የብድር ዋስትና ዘዴዎች ውጤታማ የሽግግር ማበረታቻዎችን ሊሰጡ ቢችሉም፣ እንደ አደጋ መከላከያ እርምጃ በእነሱ ላይ ከመጠን በላይ መታመን ያለዋስትና ብድር አሰራርን ዘላቂነት እና ተሸጋሪ ባህርውን ሊያዳክመው ይችላል።

[24] ትቡው ከወጣት ስራ ፈጣሪዎች ጋር

# 8. የወጣት ሥራ ፈጣሪዎች የአካታች ፋይናንስ ተጠቃሚነትን ለማስቀጠል የሚረዱ ተሞክሮዎች

የዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ፕሮግራም ሞዴል ጠቀሜታ፣ በአካታች የምጣኔ ሀብት እድገት እና አገልግሎት ያላገኙትን ህዝቦች በማብቃት አኳያ በቀጥተኛ እርመጃ ባበረከተው አስተዋፅኦ ይመዘናል፡፡ ያለመያዣ የዲጂታል ብድር አሰጣጥ ስትራቴጂው የሚነደፈው፣ ለወጣቶች በሚደረገው የብድር አገልግሎት ባህላዊ እንቅፋቶችን ለማስወገድ ሲሆን፣ ይህም በወጣቶች ለሚመሩ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር ክፍተትን ያጠብላቸዋል፡፡ ይህ ሞዴል ለሴቶች እና ለወጣቶች ቅድሚያ በመስጠት፣ የፋይናንስ ፍትሃዊነትን ያሰፍናል፣ የተገለሉ ቡድኖችንም ያበረታታል፡፡ በተጨማሪም፣ ስራን በመፍጠር፣ ኑሮን በማሻሻል እና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን በማነቃቃት የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እድገትን ያፋጥናል፡፡

የሚከተሉት የሞዴሉ ዘርፎች ለሴክተር ተዋናዮች ትምህርት ሰጪ ነው፡፡

## 8.1. የፋይናንስ ተቋማት - የብድር ሞዴሎችን ማዘመን

1. **የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ስጋት እና መልካም አጋጣሚን መልሶ መገምገም፡**
   - **ግንዛቤ፡** ብዙ ጊዜ እንደ ከፍተኛ ስጋት ቢታሰብም፣ ትክክለኛ ስልቶችን እና አቀራረቦችን ተጠቅሞ ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ዘርፍ ብድር መስጠት የሚቻል ጉዳይ እና ትርፋማ ነው፡፡
   - **ትግበራ**፡ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን እንደ ከፍተኛ የእድገት አቅም ያለው አዋጭ ገበያ በመገንዘብ፣ የፋይናንስ ተቋማት አመለካከታቸውን መቀየር አለባቸው፡፡ የሚስተዋሉ ስጋቶችን በብቃት ለማቃለል፣ በመረጃ ላይ የተመሰረቱ የብድር ግምገማዎችን እና አውዳዊ የብድር ምርቶችን መተግበር አለባቸው፡፡

2. **የገንዘብ ዝውውር ፍጥነትን እና ዲጂታል ተደራሽነትን ማሳደግ፡-**
   - **ግንዛቤ፡** የፋይናንስ ተቋማት በተመሳሳይ የካፒታል መጠን ከፍተኛ የብድር እንቅስቃሴን (ገንዘብን መልሶ መላልሶ በማበደርና እንደገና ጥቅም ላይ በማዋል የብድር አቅምን ማሳደግ) ማሳካት ይችላሉ፣ ይህም ገቢን ይጨመራል፣ የብድር አመላለስ አያያዝን ያሻሽላል፡፡ በተጨማሪም ዲጂታል አውታሮችን መጠቀም የተበዳሪዎችን ተደራሽነት ሊያሰፋ ይችላል፡፡
   - **ትግበራ**፡ "የገንዘብ ፍጥነት" (ገንዘብ በኢኮኖሚ ውስጥ በምን ያህል ፍጥነት እንደሚሽከረከር) የሚለውን ጽንሰ-ሀሳብን መቀበል ያስፈልጋል[25]፡፡ ዲጂታል ገንዘብ፣ ወጪን በመቀነስ እና ግብይቶችን በማፋጠን የገንዘብ ዝውውርን ከፍ ሊያደርግ ስለሚችል፣ የደንበኞችን ተደራሽነት ለማስፋት እና የብድር ልውውጥን ለማፋጠን፣ ዲጂታል አውታሮቶችን መጠቀም ትርፋማነትን እና የመልሶ መክፈል አቅምን ይጨምራል፡፡

[25] *በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ፣ ዲጂታል ብድር የብድር አተገባበርን፣ አረጋገጥን እና አሰረጫጨትን እንደገና በማደራጀት፣ የትግበራ ዋጋን ይቀንሳል፡፡ይህ በእነ Francis et al. (2017), Robinson et al. (2022), እና Chappell et al. (2018) ጥናቶች የሚደገፍ ነው፡፡ በተጨባጭ ጥናትና በፅንሰ ሀሳብ በመደገፍ የዲጂታል ብድር የአዋጭነት ፋይዳው በደንብ የተደራጀ ሲሆን፣ በዚህ ጉዳይ እምብዛም የሚያሰስብ አይኖርም፡፡*

3. **ዲጂታል ደንበኛ ማግኘትን ማጠናከር:**

- **ግንዛቤ:-** ዲጂታል አውታሮች እና ግልጽ ስርዓቶች ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በመሳብ እና ወደ ባንክ ደንበኝነት ይቀይራል፣ ለብዙ ባህላዊ ተቋማትም አዲስ አቀራረብ ይሆናል።
- **ትግበራ:** የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ደንበኞችን ለማግኘት ግልጽ የመድረክ ስትራቴጂዎችን መፈተሽ እና መተግበር ያስፈልጋል። ይህ አካሄድ ለባንኮች አዲስ ደንበኛ ማግኛ ዘዴን ይፈጥርላቸዋል።

4. **ጠንካራ፣ በመረጃ የሚመራ ዲጂታል ብድር ስነ-ምህዳርን መገንባት**

- **ግንዛቤ:** የዲጂታል መሠረተ ልማት፣ ዲጂታል የብድር ነጥብ መስጫ፣ ብቃት ያላቸው ሠራተኞች እና የዘመነ የብድር አሰጣጥ ሂደቶች፣ ከባህላዊ ዘዴዎች ጋር ሲነፃፀሩ ልህቀትን እና ጥቅሞችን ይሰጣሉ።
- **ትግበራ:** የፋይናንስ ተቋማት የሚከተሉትን የሚያጠቃልለውን አጠቃላይ የዲጂታል ብድር ስነ-ምህዳር ላይ ስልታዊ በሆነ መንገድ መዋዕለ ነዋይ ማፍሰስ አለባቸው።
  - ዲጂታል መሠረተ ልማት: ሁሉንም የብድር ዘርፎች ለመደገፍ፣ ጠንካራ ዲጂታል መድረኮችን ማዘጋጀት ቅድሚያ መስጠት።
  - ዲጂታል ብድር እና ብድር አስተዳደር አሰራሮች: ስራዎችን ለማቀላጠፍ እና ውጤታማነትን ለማጎልበት፣ ለብድር ነጥብ አሰጣጥ፣ ለብድር አሰጣጥ እና ለብድር አስተዳደር፣ የዘመኑ ዲጂታል ትግበራዎችን መተግበር።
  - የዳታ ሳይንስ አቅሞች: ለትክክለኛ የብድር ግምገማዎች፣ ለአደጋ አስተዳደር/አያያዝ እና ለተሻለ የምርት እድገት፣ ቀጣይነት ያለው የሥልጠና ፕሮግራሞችን መተግበር እና የላቀ የመረጃ ትንታኔዎችን ማሳለጥ ያስፈልጋል።
  - ሀገር በቀል መፍትሄዎች: ተደራሽነትን እና የደንበኞችን ተሳትፎ ለማሻሻል፣ ለተጠቃሚ ምቹ የሆኑ በይነ-ገጾችን እና አገልግሎቶችን በአገር ውስጥ ቋንቋ መፍጠር ተገቢ ነው።

5. **በደንበኛ-ተኮር ፈጠራ ዘላቂ እድገትን መፍጠር።**

- **ግንዛቤ:** ቀጣይነት ያለው ፈጠራ እና የደንበኞችን ባህሪ እና ፍላጎት መረዳት የብድር ውሎችን ለማዘጋጀት እና ተገቢ የብድር ስርዓትን ለማስተዋወቅ ወሳኝ ነው።
- **ትግበራ:** የፋይናንስ ተቋማት ከደንበኛ ባህሪ እና ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ የብድር ምርቶችን በማዘጋጀት ላይ የሚያተኩር አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በተከታታይ ለመፈተሽ እና ለማዋሃድ፣ ራሱን የቻለ የምርምር እና ልማት ቡድን ማቋቋም አለባቸው። ይህ የሚከተሉትን ያካትታል:
- ደንበኛን ያማከለ ምርምርና ልማት: የደንበኞችን ባህሪ እና ፍላጎትን ለመተንተን የምርምር እና ልማት ቡድንን መቅጠር፣ እንዲሁም የብድር መጠንን፣ የወለድ ተመኖችን እና የመክፈያ ውሎችን ማረጋገጥ ከፍ ማለት ያለባቸው ጉዳዮች ናቸው። ይህም የወጣት ተበዳሪዎች ቁጥር ከመጨመር፣ በተለይም ከወጣት ሴቶች የመበደር እድሎች ጋር የሚጣጣም ተገቢ የመበደር ሂደት እና የፋይናንስ አቅሞችን መፍጠር።

* **የቴክኖሎጂ ውህደት ለተሻሻለ አሰራር፡** የተሻሻለ የብድር አገልግሎቶችን እና አገልግሎቶችን የሚያግዙ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማዋሃድ የምርምር እና ልማት ቡድንን መጠቀም እና የደንበኞችን ተሞክሮ ማሳደግ እና የረጅም ጊዜ እድገትን ማስተዋወቅ።
* **ቀጣይነት ያለው መሻሻል፡** በምርምር እና ልማት ቡድን ውስጥ ቀጣይነት ያለው መሻሻል ባህልን ማሳደግ እና እያደገ ከመጣው የደንበኛ ፍላጎት እና ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ።

## 6. የወጣት ሴቶችን የዲጂታል እና ፋይናንስ እውቀትን ማሻሻል

* ተጋላጭ ሴቶች እና ወንዶች በፍላጎት ላይ በተመሰረተ የፋይናንስ እና ዲጂታል እውቀት እና ክህሎት ይደገፋሉ። ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በዲጂታል እውቀት እና ክህሎት ለማብቃት በክፊያ ቴክኖሎጂ አንድ ትምህርት ተዘጋጅቷል። ይህ እውቀት እና ክህሎት ወደ ዘላቂ ስኬት የሚያመጣቸውን በዲጂታል ዓለም ውስጥ በብቃት የመቆየት፣ ገንዘባቸውን በብቃት የማስተዳደር እና በመረጃ የተደገፉ ውሳኔዎችን የመስጠት አቅም ይፈጥርላቸዋል፡፡ ትምህርቱ በአገር ውስጥ ቋንቋዎች ተቃኝቶ የተዘጋጀ ሲሆን የቀረበውም፤
    * በባንክ ቅርንጫፎች
    * በወኪሎች
    * በዲጂታል ዘዴ አማካይነት ነው።

  ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች፣ እንደ ዲጂታል መልክዓ ምድርን መረዳት፣ ዲጂታል መገኘትን መገንባት፣ ፋይናንስን ማስተዳደር፣ የፋይናንስ አማራጮችን ማግኘት፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድ እና የኢንተርኔት ሽያጮችን መጠቀም፣ የንግድ መረጃዎችን መተንተን፣ አደጋዎችን መቀነስ እና የእድገት ስትራቴጂዎችን መንደፍ የመሳሰሉት ቁልፍ ርዕሶችን ፈትሸዋል። ተግባራዊ ምሳሌዎች፣ መስተጋብራዊ ልምምዶች፣ የንጥል ጥናቶች እና ከኢንዱስትሪ ባለሙያዎች የተሰጡ ግንዛቤዎች የመማር ተሞክሮን ያደብራሉ፣ ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ደግሞ የገሃዱን ዓለም የአተገባበር ስርአት ያቀርባሉ። በዚህ ኮርስ መጨረሻ፣ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የዲጂታል አለምን በብቃት ለመጠቀም፣ የፋይናንስ አስተዳደር ልምዶችን ለማዳበር እና ዲጂታል ስልቶችን እና ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም፣ ብሎም የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን እድገት እና ትርፋማነት ለማሳደግ፣ ችሎታ እና ሙያ ይኖራቸዋል።  ትምህርቱ በስምንት ሞጁሎች የተደራጀ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ ሞጁል ምን እንደሚማሩም በግልፅ ተቀምጧል።

## 7. ለጠንካራ የሳይበር ደህንነት እርምጃዎች ቅድሚያ መስጠት፡

* **ግንዛቤ፡** ጠንካራ የሳይበር ደህንነት ሚስጥራዊነት ያለው መረጃን ለመጠበቅ እና በዲጂታል ብድር አውታሮ ላይ እምነት ለመፍጠር አስፈላጊ ነው።
* **ትግበራ፡** መረጃዎችን ለመጠበቅ ጠንካራ የሳይበር ደህንነት እርምጃዎችን መተግበር እና ለዲጂታል ግብይቶች ደህንነቱ የተጠበቀ ሁኔታን መፍጠር።

## 8.2. የልማት አጋሮች - አካታች የብድር ሞዴሎችን መደገፍ

### 1. በስርዓት-አቀፍ ተጽእኖ ላይ ማተኮር

- **ግንዛቤ፡** ዘላቂ እና ተስፋፊ/ታዳጊ ሞዴሎች ስርአት-አቀፍ ተፅእኖን ለማምጣት መፍትሔ አላቸው፡፡
- **ትግበራ፡** ከፕሮግራም የቆይታ ጊዜ በላይ የሚዘልቁ እና አጠቃላይ ዘርፎችን ወይም ስነ-ምህዳሮችን ለማሻገር የስርዓት ለውጥ በሚያሳዩ ሞዴሎች ላይ የሚያተኩሩ ድርጅቶችን መፈለግና መደገፍ፡፡

### 2. የትብብር ሽርክናዎችን ማጠናከር

- **ግንዛቤ፡** በፋይናንስ ተቋማት (ባንኮች፣ጥቃቅን የፋይናንስ ተቋማት፣ የፋይናንስ ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም እንደ ፖሊሲ አውጪዎች፣ ቴሌኮም ወዘተ ባሉት ሰፊ የስነምህዳር አጋሮች) መካከል ያለው ትብብር፣ ሰፋ ያለ ተቀባይነት፣ የጋራ ፈጠራን፣ ሰፋፊ የገበያ ተደራሽነትን፣ ዘላቂ የፋይናንስ መፍትሄዎችን እና የጋራ ስጋት የመቀነስ እድገትን በማምጣት፣ የጋራ ተጠቃሚነትን ያረጋግጣል፡፡
- **ትግበራ፡** መደበኛ የግንኙነት አውታሮችን ማቋቋም፣ የፕሮግራም ተፅእኖ ግንዛቤን ለማሳደግ መድረኮችን መጠቀም እና ለዲጂታል ብድር ጠንካራና ደጋፊ ምህዳር ለመፍጠር፣ በጋራ አላማዎች ላይ መስራት፡፡

### 3. የቁጥጥር ማሻሻያ እና ወጣቶችን ያካተቱ ስልቶችን መደገፍ

- **ግንዛቤ፡** ደጋፊ የፋይናንስ ሴክተር ፖሊሲዎችን ማዳበር አካታች ፖሊሲዎችን ማራመድ እና ወጣት ሥራ ፈጣሪዎችን ጨምሮ በቂ አገልግሎት ለሌላቸው ህዝቦች የብድር አቅርቦት ማስፋት ይችላል፡፡ የቁጥጥር እርምጃዎች በብድር ተደራሽነት ላይ የታወቁ የሥርዓተ-ፆታ ልዩነቶችን በትክክል ይፈታሉ፡፡
- **ትግበራ፡** በፋይናንስ ሴክተር ውስጥ ፈጠራን እና አካታችነትን የሚያበረታቱ ማሻሻያዎችን ለመደገፍ እንደ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ካሉ ተቆጣጣሪ አካላት ጋር መሳተፍ፡፡

### 4. በቴክኖሎጂ ተደራሽነትን ማስፋት፡-

- **ግንዛቤ፡** ቴክኖሎጂን የሚጠቀሙ አዳዲስ መፍትሄዎች ተደራሽነትን የሚያሰፉ እና ዘላቂ ለውጥ የሚያመጡ ናቸው፡፡
- **ትግበራ፡** ቀጣይነት ያለው ተግዳሮቶችን የሚፈቱ እና አዳዲስ እድሎችን ለመፍጠር የሚያስችሉ መሰረታዊ አቀራረቦችን እና ቴክኖሎጂዎችን ማበረታታት እና መደገፍ፡፡

## 8.3. ፖሊሲ አውጪዎችና ተሚጋቾች - የአስቻይ ከባቢ አላባውያን

### 1. የተለያዩ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪዎች እንዲፈጠሩ ማድረግ፡-

- **ግንዛቤ፡** ነባር ደንቦች የብድር አሰራሮችን በባንኮች ብቻ እንዲገደብ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም የፋይናንስ አገልግሎት በሌሎች ተቋማት እንዳይስፋፋ ይከለክላል፡፡
- **ትግበራ፡-** እንደ ኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ናይጄሪያ እና ህንድ ባሉ ገበያዎች ውስጥ እንደታዩት ስኬታማ ሞዴሎች፣ ከባንክ ውጪ ያሉ የፋይናንስ ተቋማት (NBFIs) ዲጂታል የፋይናንስ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ የሚያስችል የቁጥጥር ማዕቀፍ ማዘጋጀት፡፡ ይህ በተለይ

ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ውድድርን ያበረታታል፣ የብድር አቅርቦትንም ያሰፋዋል።

2. **ለፋይናንስ እና ለዲጂታል ትምህርት ማዕቀፎች ቅድሚያ መስጠት፡-**
   - **ግንዛቤ፡-** በፋይናንስ እና ዲጂታል ትምህርት ላይ፣ በተለይ በገጠር አካባቢዎች፣ ክፍተቶች አሉ፤ ይህ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም እንቅፋት ይሆናል።
   - **ትግበራ፡** ግለሰቦች እና የንግድ ተቋማት የዲጂታል ፋይናንስ ስልቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲረዱ እና እንዲጠቀሙ ለማበረታታት፣ አጠቃላይ የፋይናንስ እና ዲጂታል ስልጠና ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ማድረግ። ይህ የህዝብ ግንዛቤ መፍጠርያ ዘመቻዎችን፣ የትምህርት ግብአቶችን እና የስልጠና ውጥኖችን ያጠቃልላል።

3. **ትብብርን ማሳደግ እና የእውቀት ሽግግርን ማበረታታት**
   - **ግንዛቤ፡** በፋይናንስ ሴክተር ውስጥ ፈጠራን ለማስፋፋት፣ በፖሊሲ አውጪዎች የፋይናንስ ተቋማት እና በስነምህዳር አጋሮች መካከል የሚደረጉ ትብብሮች እጅግ አስፈላጊ ናቸው። ስኬቶችን እና ውድቀቶችን በጋራ መድረኮች መጋራት፣ ለመማር እና ለመሻሻል ወሳኝ ነው።
   - **ትግበራ፡** በሥነ-ምህዳር ተዋናዮች መካከል ያለውን አጋርነት ማስተዋወቅ እና ማጠናከር መቀጠል። የእውቀት ሽግግርን ለማመቻቸት ቀጣይነት ያለው መድረኮችን እና አውደ ጥናቶችን ማዘጋጀት፣ በዲጂታል ብድር ውስጥ ምርጥ ተሞክሮዎችን ማስተዋወቅ፣ እና የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶችን ልማት እና ተቀባይነትን መደገፍ።

4. **ግልጽ ፋይናንስ እና የተበዳሪዎች መታወቂያ/ማንነት**
   - በፋይናንስ ተቋማት እና በሶስተኛ ወገን አቅራቢዎች መካከል ደህንነቱ የተጠበቀ የተበዳሪዎች መረጃ መጋራትን ለማረጋገጥ፣ ብሔራዊ ባንኩ ግልጽ የባንክ አሰራርን እና የፋይናንስ መስፈርቶችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ አለበት።
   - በተለያዩ መድረኮች ላይ የተበዳሪዎችን ማንነት የሚያረጋግጡ ጠንካራ እና ሊረጋገጡ የሚችሉ ዲጂታል መታወቂያ አሰራሮችን ለመገንባት፣ የብሔራዊ መታወቂያ ተደራሽነት ለሁሉም ተበዳሪዎች የግዴታ መሆን አለበት።

## 9. ማጠቃለያ

ይህ ንጥል ጥናት እንደሚያሳየው፣ የዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ፕሮግራም፣ በፈጠራዊ ያለዋስትና የዲጂታል ብድር ሞዴሉ በኩል፣ ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ የሆነውን የኢትዮጵያ የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ወሳኝ የፋይናንስ ክፍተት መፍታት እንደቀጠለ ነው። የዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ መርሃ ግብር ባህላዊ ዋስትናን መሰረት ያደረገ ብድርን ወደ ፈጠራዊ ያለዋስትና የብድር ሞዴሎች ለማሸጋገር እየሰራ ነው። ይህ ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር ተደራሽነትን ለማስፋት እና ሁሉን አቀፍ የፋይናንስ ተሳትፎን የሚያደናቅፉ ዘላቂ የፋይናንስ እውቀት ክፍተቶችን ለመፍታት አስችሏል።

ዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ፕሮግራም ዲጂታል ቴክኖሎጂን በማጎልበት እና ስትራቴጂካዊ አጋርነትን በማጠናከር፣ ወሳኝ ካፒታልን ማከፋፈል ብቻ ሳይሆን በፋይናንስ ሴክተሩ ውስጥ የፖሊሲ እና የአሰራር ልምምዶች ሽግግርን አሳልጧል። ቁልፍ የፖሊሲ ለውጦች፣ ለምሳሌ በመረጃ ላይ የተመሰረቱ የብድር ሞዴሎች ተቀባይነት እና የተሻሻሉ የአደጋ አያያዝ ስርዓቶች፣ በተለይ በባንኮች መካከል፣ ቀደም ሲል ላልተካተቱ ህዝቦች የብድር አቅርቦትን በእጅጉ አስፍተዋል። በተጨማሪም የዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ማሳያ ውጤት ተመሳሳይ የዲጂታል ብድር አሰጣጥ ስልቶችን እየተጠቀሙ ካሉት አጋር ያልሆኑ ተቋማት ውስጥ የገበያ ውድድርን እና ፈጠራን አነሳስቷል። ከዚህም ውጭ፣ ዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ወጣት ሥራ ፈጣሪዎችን እንደ ውጤታማ ደንበኞች እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ቁልፍ አንቀሳቃሾች በመፈረጅ፣ በአመለካከታቸው ላይ በጎ ተጽዕኖ አሳድሯል፤ በተጓዳኝም የወጣት ሥራ ፈጣሪዎችን የፋይናንስ ተቋማት ግንዛቤን አሻሽሏል።

ይህ ንጥል ጥናት እንደሚያሳየው፣ የእነዚህ ፕሮግራሞች ስኬታማ የሆነ መባዛትና መስፋፋት፣ ፖሊሲ አውጪዎችን፣ ገንዘብ ለጋሾችን እና የፋይናንስ ተቋማትን ባሳተፈ የጋራ ጥረት ላይ የተመሰረተ ነው። ፖሊሲ አውጪዎች የተለያዩ የፋይናንስ አቅራቢዎችን የሚደግፉ እና ለፋይናንስ እውቀት ቅድሚያ የሚሰጡ አስቻይ የቁጥጥር ማዕቀፎችን እንዲፈጥሩ ይመከራል። ገንዘብ ለጋሾች እና የልማት ድርጅቶች ጠንካራ አጋርነትን በማበረታታት እና የቁጥጥር ማሻሻያ እንዲደረግ በመገመት፣ በቴክኖሎጂ መር ፈጠራ እና ሥርዓታዊ መፍትሄዎች ላይ መዋእለ ነዋያቸውን ማፍሰስ አለባቸው። የፋይናንስ ተቋማት ደግሞ ደንበኛን ያማከለ መፍትሄዎችን በማዳበር እና ጠንካራ የዲጂታል መሠረተ ልማቶችን በመገንባት ዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን እንዲቀበሉ ይበረታታሉ።

በጥቅሉ፣ "የዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ" ሞዴል፣ አካታች የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለማስፋፋት እና ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማበረታታት፣ አግባብነት ያላቸውን ትምህርቶችን እና መተግበሪያዎችን ያቀርባል። በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተዘረዘሩትን ትምህርቶች/ተሞክሮዎችን እና ተግባራትን በመተግበር፣ ባለድርሻ አካላት የዚህን ዘርፍ ሰፊ እምቅ አቅም ማውጣት ይችላሉ፣ ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እድገትን ያመጣሉ፣ በተለያዩ አውዶች/ሁኔታዎች ውስጥ የበለጠ ፍትሃዊ የፋይናንስ ገጽታንም ይፈጥራሉ።

# 10. ማጣቀሻ ጽሑፎች


Ababiya, A. (2018). Financial performance of agricultural enterprises and their determinant factors in Hadiya Zone, Ethiopia. Small, 243(46), 98.

Agwu, M. E. (2021). Can technology bridge the gap between rural development and financial inclusions? Technology Analysis & Strategic Management, 33(2), 123-133.

Ayele, A. W., & Derseh, A. B. (2020). Challenges that hinder the sustainability of small and medium scale enterprises in East Gojjam Zone, Northern Ethiopia. *International Journal of Development Research*, 10(7), 37926-37934.

Baleseng, M. C. (2015). Factors affecting the sustainability of SMEs in the manufacturing sector of Gaborone, Botswana (Doctoral dissertation).

Brixiová, Z., Kangoye, T., & Yogo, T. U. (2020). Access to finance among small and medium-sized enterprises and job creation in Africa. Structural Change and Economic Dynamics, 55, 177-189.

Case Studies Stories from Kifiya users.

Central Statistics Agency. (2021). Final 2021 labour force and migration survey key findings report. https://www.statsethiopia.gov.et/wp-content/uploads/2021/08/Final-2021-LABOUR-FORCE-AND-MIGRATION-SURVEY_Key-finding-Report-.17AUG2021.pdf

Cherkos, T., Zegeye, M., Tilahun, S., & Avvari, M. (2018). Examining significant factors in micro and small enterprises performance: case study in Amhara region, *Ethiopia. Journal of Industrial Engineering International*, 14, 227-239.

Ethiopia's MSED Policy and Strategy. (2016). Federal Democratic Republic of Ethiopia (FDRE), Ministry of Urban Development and Housing: Micro and Small Enterprise Development Policy & Strategy.

IFC. (2024). MSME factsheets. https://www.ifc.org/content/dam/ifc/doc/2024/msme-s-factsheet-ifc-financial-institutions-group.pdf

International Labor Organization. (2022a). Young people in African face pressing challenges in the transition from school to work. https://ilostat.ilo.org/blog/african-youth-face-pressing-challenges-in-the-transition-from-schooltowork/#:~:text=More%20than%2072%20million%20youth%20in%20Africa%20are,8%20on%20decent%20work%20for%20all%20by%202030.

International Labor Organization. (2022b). The global employment trends for youth 2022: Investing in transforming futures for young people. https://www.ilo.org/resource/news/recovery-youth-employment-still-lagging-says-ilo-0

International Monetary Fund. (2021). World economic outlook: Recovery during a pandemic. IMF Publications.

Liu, G., & Wang, Y. (2020). Competition in digital lending: The rise of fintech and its impact on traditional banks. Finance Research Letters, 32, 101018.

Mamo, W. B. (2023). Growth determinants of micro and small enterprises (MSEs): Evidence from entrepreneurs in the Eastern Region of Ethiopia. *Journal of the Knowledge Economy*, 14(1), 138-160.

Mastercard Foundation. (2023). Mastercard Foundation – Access to finance programming review assessment report.

Mastercard Foundation-Young Africa Works. Michu second survey findings. https://Mastercardfdn.org/our-strategy/young-africa-works/

McKinsey & Company. (2020). The future of digital lending: A perspective on contending with emerging threats. https://www.mckinsey.com/

Muiruri, S. (2017). African small and medium enterprises (SMEs) contributions, challenges, and solutions. *European Journal of Research and Reflection in Management Sciences*, 5(1), 36-48.

National Bank of Ethiopia. (2024). Financial stability report. https://nbe.gov.et/wp-content/uploads/2024/11/Financial-Stability-Report_NOV2024.pdf

National Bank of Ethiopia. Directives. https://nbe.gov.et/mandates/directives/

National Bank of Ethiopia. NBE holds consultation forum on regional financial inclusion implementation framework. https://nbe.gov.et/nbe_news/nbe-holds-consultation-forum-on-regional-financial-inclusion-implementation-framework/.

National Financial Inclusion Strategy (2021-2025). (2020). https://nbe.gov.et/files/national-financial-inclusion-strategy-ii-2021-2025/

Negash, G., & Sileshi, T. (2019). Determinants of micro and small enterprises growth in selected towns of West Shoa Zone, Oromia Regional State, Ethiopia. International

Rahel, F. (2018). Factors affecting sustainability of small and medium-scale enterprises: The case of Addis Ababa, Ethiopia. Addis Ababa University.

SAFEE Journey Overview Report. (2024).

SAFEE Quarter III Narrative Report.

Smith, J. A., & Johnson, L. M. (2020). The impact of uncollateralized lending on borrower default rates. *Journal of Financial Economics*, 45(3), 245-267.

SME Finance Forum. (2017). MSME finance gap. https://www.smefinanceforum.org/data-sites/msme-finance-gap

Sustainable Access to Finance to Enable Entrepreneurship Scaling Up Uncollateralized Digital Lending in Ethiopia Program Documents.

United Nations. (2024). 2024 theme: MSMEs and the SDGs. https://www.un.org/en/observances/micro-small-medium-businesses-day#:~:text=MSMEs%20account%20for%2090%25%20of%20businesses%2C%2060%20to,poor%2C%20women%2C%20youth%2C%20and%20groups%20in%20vulnerable%20situations.

United Nation Development Program. (2024). https://www.undp.org/ethiopia/blog/digital-lending-platforms

World Bank. (2015). SMEs finance in Ethiopia: addressing the missing middle challenge. Retrieved from https://documents.worldbank.org/en/publication/documentsreports/documentdetail/805371468247458154/sme-finance-in-ethiopia-addressing-the-missing-middle-challenge?

World Bank. (2019). Ease of doing business report. https://archive.doingbusiness.org/en/scores

World Economic Forum. (2022). The future of financial services: How technology is reshaping the financial services industry. WEF report. Retrieved from https://www.weforum.org/

Zhang, Z., & Zhan, F. X. (2021). Alternative credit scoring: The impact of digital lending on interest rates. Journal of Financial Technology, 19(4), 245-26.

**አባሪ ሀ. የዘገባው መረጃ**

**የመረጃ ምንጮች እና የአሰባሰብ ሂደት**

| | | |
|---|---|---|
| 1 | **ቁልፍ መረጃ ሰጪ ቃለመጠይቅ** | |
| | **ተሳታፊዎች** | **የናሙና ብዛት** |
| | ብሔራዊ ባንክ | 2 |
| | የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር | 1 |
| | የሳይንስና እኖቬሽን ሚኒስቴር | 1 |
| | MCF | 2 |
| | ባንኮች | 15 |
| | ጥቃቅን የፋይናንስ ተቋማት | 4 |
| | ክፍያ ቴክኖሎጂ | 2 |
| | ፊርስት ኮንሰልት | 1 |
| | የኢትዮጵያ ስራ ፈጣሪ ወጣቶች ማህበር | 1 |
| | **ድምር** | 29 (27 **ንቁ ተሳታፊ**) |
| 2 | **የትኩረት ቡድን ውይይቶች (ትቡው)** | |
| | **ተሳታፊዎች** | **የናሙና ብዛት** |
| | ትቡው 1 | 5 |
| | ትቡው 2 | 6 |
| | ትቡው 3 | 4 |
| | ሁለተኛ (ቀጥተኛ ያልሆነ) መረጃ | |
| 1.ተዛማጅ ፅሑፍ ክለሳ፣ የብጤ ክለሳ፣ ኢ-መደበኛ የንግድ መረጃ ምንጮች | | 2. የሰነድ ዳሰሳ፣ ፖሊሲዎችና የፕሮግራም ሪፖርቶች |

ይህ ንጥል ጥናት እያደገ የመጣውን የኢትዮጵያን የፋይናንስ ሴክተር ስነ-ምህዳር እና አዳዲስ የብድር ስርዓት አቀራረቦችን ያመጣውን የፖሊሲና የአሰራር ለውጦችን በጥልቀት ለመተንተን የቅይጥ ዘዴዎችን አቀራረብ ተጠቅሟል። በዋነኛነት፣ ዓይነታዊ መረጃ የተሰበሰበው ቁልፍ የቁጥጥር ተዋናዮችን እና የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ፣ እይታ እና አረዳድን ለመረዳት ሲሆን፣ ይህም የፖሊሲ ለውጦችን፣ የብድር ተሞክሮዎችን እና የስነ-ምህዳሩን ሁኔታን ለመገንዘብ አስችሏል። ይህንን የሚደግፍ፣ የአዝማሚያዎችን እና ሊለኩ የሚችሉ ውጤቶችን ተጨባጭ ትንታኔ ለመስጠት፣ ቁጥራዊ መረጃ ተሰብስቧል።

የመረጃ ምንጮች ከቁልፍ የመረጃ ሰጭ ቃለመጠይቆች እና ከትኩረት ቡድን ውይይቶች ከተገኙ የመጀመሪያ ጥናቶችን እና ተቋማዊ መረጃን፣ የፕሮግራም ሰነዶችን እና ተዛማጅ ጽሑፎችን ከዳሰሱ ሁለተኛ ደረጃ ጥናቶችን ያካተቱ ናቸው። ይህ የተቀናጀ አቀራረብ ምናባዊ (subjective) አመለካከቶችን ከተጨባጭ ማስረጃዎች ጋር በማጣመር የተሟላ ግምገማ እንዲኖር አስችሏል።

**ቁልፍ የመረጃ ሰጭ ቃለ-መጠይቆች:** ተቆጣጣሪዎችን፣ የመንግስት ተቋማትን፣ ባንኮችን፣ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማትን እና የፕሮግራም አጋሮችን ኢላማ ያደረገ፣ በድምሩ 29 ቃለ

መጠይቆች ታቅዶ ነበር። ውይይቶቹ በደንብ የተዋቀረ የቁልፍ መረጃ ሰጭ ቃለ-መጠይቅ መመሪያን በመጠቀም፣ ስለ ጉዳዩ ባላቸው ጥልቅ እውቀት ላይ ተመስርተው በጥቆማ ከተመረጡ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ጋር የተደረጉ ነበሩ። የመጀመርያው ኢላማ 29 ቃለ መጠይቆችን ማካሄድ ሲሆን፣ 27ቱ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቀዋል (አባሪ ሀን ይመልከቱ)። የአማራ ባንክ የፕሮግራም ትግበራ ገና በጀመረበት ወቅት በመመሆኑ ከመጠይቁ ውጪ የተደረገ ሲሆን፣ ከብሔራዊ ባንክና ከኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ ተወካዮች ጋር ሊደረግ የታቀደው ሁለት ቃለ ምልልሶች ሳይሳኩ ቀርተዋል።

**የትኩረት ቡድን ውይይቶች፡-** ያለዋስትና የዲጂታል ብድር አሰጣጥ አስመልክቶ፣ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ስላላቸው ልምድ መረጃ ለመሰብሰብ፣ በድምሩ 16 ተሳታፊዎችን ያሳተፈ ሶስት የትኩረት ቡድን ውይይቶች ተካሂደዋል። አላማው የስኬት ታሪኮችን መሰብሰብና መሰነድ፣ ተግዳሮቶችን መለየት እና በፋይናንስ ተቋማቱ ፖሊሲዎች እና አሰራሮች ላይ የተደረጉ ለውጦች እንዴት በስራ ፈጠራ አመለካከታቸው ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደሩ መረዳት ነበር።

ተሳታፊዎቹ፣ የየኢንተርፕራይዞቹን መጠን እንዲሁም የቁልፍ ዘርፎችን ማለትም፣ ማኑፋክቸሪንግን፣ አግሮ ፕሮሰሲንግን እና ዲጂታል ኢኮኖሚን ውክልና ለማረጋገጥ፣ በከፋፍሎ የናሙና መረጣ ዘዴ የተመረጡ ናቸው[26]። ከ95% በላይ የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ወጣት ሴቶች በመሆናቸው፣ ሁሉም የትኩረት ቡድን ውይይቶች የተካሄዱት በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ ሴት ስራ ፈጣሪዎች ጋር ሲሆን እያንዳንዱ ቡድን ከተመረጡት ዘርፎች እና የኢንተርፕራይዝ መጠኖች ከ4-6 ተሳታፊዎችን ያቀፈ ነበር።

የመጀመሪያ ደረጃ መረጃን ለማዳበር እንዲረዳ፣ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ መረጃን የማሰባሰብ ሂደት ተካሂዷል። የስነ-ጽሁፍ ዳሰሳው የተካሄደው፣ በአቅርቦት በኩል የፋይናንስ ተደራሽነትን፣ በታዳጊ ኢኮኖሚዎች የሚታየውን ዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን እና ተዛማጅ ርዕሶች ላይ የተደረጉ ምርምሮችን በፍጥነት ለማቀናጀት ሲሆን፣ ይህም የኢትዮጵያን ጉዳይ አውድ ለመረዳት መልካም አጋጣሚ ነበር። በተጨማሪም የብሔራዊ ባንክ ፖሊሲዎችን፣ ያለዋስትና የብድር ፕሮግራም ሰነዶችን (ውጥኖችን፣ ቻርተሮችን እና የግምገማ ሪፖርቶችን ጨምሮ)፣ የቴክኒክ ድጋፍ ማቴሪያሎችን እንዲሁም፣ ከኮቪድ-19 መቋቋሚያ እና ማገገሚያ ፕሮግራም፣ ከ Bridges፣ ከጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ማቋቋሚያ እና ከዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ የተውጣጡ የፕሮግራም ሰነዶችን በመተንተን የተሟላ የሰነድ ግምገማ ተካሂዷል። ይህ ሁለገብ የሁለተኛ ደረጃ መረጃ አሰባሰብ ስልት፣ የጥናቱን ዋና ዋና ጭብጦች በሚገባ ለመረዳት አስችሏል።

---

[26] *በሎጂስቲክ እጥረት ምክንያት ከአዲስ አበባ ውጭ ካሉት ተጠቃሚዎች ጋር ውይይት ማዘጋጀት ስላልተቻለ፣ የግብርና ዘርፍ በመረጃ ውስጥ አለመካተቱን ለማስታወስ እንወዳለን።*

**የቃለ መጠይቅ ዝርዝር፤**

| | ድርጅት | ስም | ሚና |
|---|---|---|---|
| 1 | አዋሽ ባንክ | ሙሉጌታ ከፍያለው | ዳስፖራና ፐርሰኔል ማናጀር |
| 2 | አቢሲኒያ ባንክ | ቴዎድሮስ ሀይሌ | የብድር ፖርትፎሊዮ አስተዳደር ማናጀር |
| 3 | ብርሃን ባንክ | አለምስላሴ ሙላት | የ MIS እና ስትራቴጂ ክትትል ም/ማናጀር |
| 4 | ቡና ባንክ | ሮቤል አለማየሁ | የፕሮግራም አስተዳደርና ፈጠራ ዳይሬክተር |
| 5 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ፍሰሃ ተስፋዬ | ደንበኛ አገልግሎት |
| 6 | የኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ | አብዲ ፈቀደ | የኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ |
| 7 | ዳሽን ባንክ | ብራቱ ሞስሳ | ጥቃቅን እና አነስተኛ ንግድ ባለሙያ |
| 8 | እናት ባንክ | ጋሻው ደበለ | የብድር አስተዳደር ዳይሬክተር |
| 9 | የኢትዮጵያ ስራ ፈጣሪ ወጣቶች ማህበር | ሰሚያ አብዱልቃድር | የኢትዮጵያ ስራ ፈጣሪ ወጣቶች ማህበር ፕሬዚደንት |
| 10 | ፈርስት ኮንሰልት | ኬና ኢታና | ጥቃቅን፣ አነተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ማቋቃሚያ ፕሮግራም መሪ |
| 11 | ህብረት ባንክ | አለምፀሀይ ብርሃኑ | ጥቃቅን፣ አነተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና የግብርና ብድር ዳይሬክተር |
| 12 | ክፍያ ቴክኖሎጂ | 1. ሙኒር ዱሪ | የክፍያ ቴክኖሎጂ ስራ አስፈፃሚ |
| 13 | ክፍያ ቴክኖሎጂ | 2. ሀያት አብዱልማሊክ | ዋና የእምፓክት ቢሮ እና ፕሮግራም ዳይሬክተር |
| 14 | ክፍያ ቴክኖሎጂ | 3. ሀናን አንዳርጋቸው | ፕሮግራም ማናጀር |
| 15 | መክሊት ማይ/ፋይናንስ | አቶ አዲስ አድማስ | MIS ማናጀር |
| 16 | መተማመን ማይክሮ ፋይናንስ | አቶ አይተነው ወንድማገኝ | የብድር እና ፖርትፎሊዮ አስተዳደር ማናጀር |
| 17 | የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር | ደ/ር አብዮት ባዩ | በሳይንስና እኖቬሽን ሚኒስተር፣ የሚኒስተሩ ዋና አማካሪ |
| 18 | የስራ እና ክህሎት ሚኒስቴር | ተፈሪ አዳሙ | የኢትዮጵያን ማስቻል ፕሮግራም ማናጀር |
| 19 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ | ሙህዲን ሽፋ | የደንበኞች ጥበቃና ፋይናንስ ትምህርት ዳይሬክተር |
| 20 | ንብ ባንክ | ገበየሁ ሮባ | የቢዝነስ ፕሮግራም ዳይሬክተር |
| 21 | ንስር ማይክሮ ፋይናንስ | ዳኛቸው አዳራው | የብድር አስተዳደር ዳይሬክተር |
| 22 | ኦሮሚያ ባንክ | መልካሙ አሰበ | የአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ብድር ማናጀር |
| 23 | ቪዥን ፈንድ ማይ/ፋይናንስ | ሀይሉ ለታ | የቪዥን ፈንድ ማይ/ፋይናንስ ምክትል ስራ አስፈፃሚ |
| 24 | ወጋገን ባንክ | ሱራፌል ያዛቸው | ዲጂታል ብድር ማናጀር |
| 25 | ዘመን ባንክ | ኦስማን ሞሃመድ | የፕሮጀቶች አስተዳደር ቢሮ ሓላፊ፣ ዘመን ባንክ |
| 26 | ማስተርካርድ ፋዎንዴሽን | ሳሙኤል ያለው | ማስተርካርድ ፋዎንዴሽን ካንትሪ ዳይሬክተር |
| 27 | ማስተርካርድ ፋዎንዴሽን | አብድላሂ ፋራህ | የፋይናንስ አካታችነትት እና እንቨስትመንት ፕሮግራም መሪ |

## አባሪ ለ፡ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የፋይናንስ አካታችነት ፕሮግራሞች በኢትዮጵያ

የ2030 ግቦቹን ለማሳካት ማስተርካርድ ፋውንዴሽን በኢትዮጵያ ውጤታማ ፕሮግራሞችን ጀምሯል:: ከፈርስት ኮንሰልት ጋር በመተባበር ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ሶስት ቁልፍ ፕሮግራሞችን ጀምሯል:: BRIDGES (ጥቅምት 2019 - ነሀሴ 2024) (እኤአ) ለወጣቶች የክህሎት ስልጠና፣ የንግድ ልማት ድጋፍ፣ የገበያ ትስስር እና የፋይናንስ አቅርቦት ላይ ያተኩራል:: ኮቪድ-19 መቋቋሚያ እና ማገገሚያ ፕሮግራም (ሰኔ 2020 - ሰኔ 2023) (እኤአ) የገንዘብ ልገሳ በማድረግ እና ለክፍያ የሚቀል ብድር (soft loan) በመስጠት፣ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት ያጋጠማቸውን የገንዘብ እጦት ተግዳሮቶችን ቀርፎላቸዋል:: በየኮቪድ-19 መቋቋሚያ እና ማገገሚያ ፕሮግራም ስኬት ላይ በመገንባት ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ማቋቋሚያ (2022-2027) የማገገም አቅማቸውን ለማሳደግ እና ለወጣቶች የስራ እድል ለመፍጠር፣ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በገንዘብ ድጋፍ፣ በንግድ ስራ ልማት እና በስነ-ልቦና ድጋፍ እገዛ ያደርግላቸዋል::

### ወጣት አፍሪካዊያን ይሰራሉ የፋይናንስ ተደራሽነት ፕሮግራም

| | ብሪጅስ (ጥቅምት 2019-ጥቅምት 2024) | ኮመማፕ (ሰኔ 2020-ሰኔ 2023) | ጥአመኢመ (2022-2027) | ዘፋአስፈ (ታህሳስ 2023-ህዳር 2028) |
|---|---|---|---|---|
| ዓላማ | በኢንተርፕራይዝ ፈጠራ፣ በስራ ትስስር፣ በፋይናንስ አቅርቦት፣ እና በኢንተርፕራይዝ ተወዳዳሪነት ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን መደገፍ | በገንዘብና ለክፍያ የሚቀል ብድር መልክ በኮቪድ-19 የተጠቁ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በፋይናንስ አቅርቦት ድጋፍ ማድረግ | የንግድ ድርጅቶች በፋይናንስ ተደራሽነት (የገንዘብ ድጋፍና ለክፍያ የሚቀል ብድር)፣ በBDS እና ስነልቦና አገልግሎት ከክሳራ አገግሞ አቅማቸውን እንዲገነቡ ማድረግ | በመረጃ የተደገፈ ፈጠራዊ የብድር አሰጣጥ ቴክኖሎጂን በማሳደግ፣ የፋይንስ አካታችነትን ለማምጣት እና ስራ ለመፍጣር ብሎም ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ያለዋስትና የብድር ተጠቃሚ ለማድረግ |
| አጋሮች | ፈርስት ኮንሰልት ሰማጉሚ፣ የፌደራል ቴሙትስ ኤጀነሲ፣ ጥቃቂን የፋይናንስ ተቋማት፣ ባንኮች | ፈርስት ኮንሰልት፣ ሰማጉሚ፣ ባንኮች | ፈርስት ኮንሰልት፣ ሰማጉሚ እና ፋይናንስ ተቋማት (ባንኮች፣ ጥቃቂን የፋይናንስ ተቋማት፣ የጊጂታል ፋይናንስ አቅራቢ.ዎች)፣ BDS አቅራቢ.ዎች፣ የስነ ልቦና ድጋፍ ሰጪ.ዎች | ክፍያ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ እና 6 አጋር ባንኮች (አማራ ባንክ፣ ቡና ባንክ፣ ኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ፣ እናት ባንክ፣ ዎጋገን ባንክ እና ዘመን ባንክ) |
| የፕሮግራሙ ተሳታፊ | በ7 ክልሎች እና በ2 ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ ከ18-35 ዓመት ዕድሜ ያሉ ወጣቶችና 70% ሴቶች | በአዲስ አበባ የሚገኙ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና የግጪት ተጠቂ የሆኑ አካባቢ.ዎች (አፋር፣ አማራ፣ እና ትግራይ ክልሎች) 70% ሴቶች | አገር አቀፍ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች፣ የግጭት ተጠቂ አካባቢ.ዎች፣ 70% ሴቶች | ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች፣ አነስተኛ አርሶ አደሮች እና መካከከለኛ ገቢ ተጠቃሚ.ዎች፣ 80% ወጣት ሴቶች፣ 10% አካል ጉዳተኞች፣ 10% ስደተኞች፣ ተፈናቃዮች |

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ ዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ፕሮግራም (2023-2028) ከክፊያ ፋይናንስ ቴክኖሎጂ ጋር በመተባበር፣ 2.18 ሚሊዮን ወጣቶች የዲጂታል ችሎታዎችን፣ የፋይናንስ እውቀታቸውን እና የብድር ተደራሽነትን በማጎልበት፣ ያለዋስትና የዲጂታል ብድር ስርዓትን ተጠቅመው ሥራ እንዲያገኙ ለማስቻል ዓላማ አድርጎ እየሰራ ነው። እነዚህ ውጥኖች የተነደፉት፣ ስልታዊ ለውጥን ለማምጣት፣ የፋይናንስ ተደራሽነትን፣ ስልጠናን እና ገበያን ለማሻሻል እና ለወጣቶች ትርጉም ያለው የስራ እድል ለመፍጠር ነው።

ከጥቅምት 2011 እስከ ጥቅምት 2024 (እኤአ) ድረስ በሰባት ክልሎች እና በሁለት የአስተዳደር ከተሞች በፈርስት ኮንሰልት የተተገበረው የBRIDGES መርሃ ግብር የስራ እድል ፈጠራን እና ስራን ለማነቃቃት ያለመ ነው። አራቱ ቁልፍ የትግበራ ዘርፎች፣ ኢንተርፕራይዝ ማቋቋም (BDS እና ሥራ የማግኘት ችሎታ/ሙያ)፣ የስራ ትስስር (ሰራተኞችን ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ጋር ማገናኘት)፣ የኢንተርፕራይዝ ተወዳዳሪነት እና የፋይናንስ ተደራሽነትን ያካትታሉ። በፋይናንስ ተደራሽነቱ ዘርፍ፣ BRIDGES በፍላጎትም በአቅርቦትም በኩል የፋይናንስ ክፍተቶችን ቀርፏል። በፍላጎት በኩል፣ ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ለወጣት ስራ ፈጣሪዎች የፋይናንስ ትምህርት ግብዓቶችን አዘጋጅቶ ለኢትየዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አቅርቧል። በአቅርቦት በኩል፣ የጅምላ ሽያጭ ብድር አሰጣጥን አመቻችቷል፣ የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር መስፈርቶች አዘገጃጀትን አስመልክቶ፣ ለባንኮች እገዛ አድርጓል፤ እንዲሁም፣ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የብድር ውሎች እንዲኖሩ ድርድር አድርጓል።

ከሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከአዋሽ ባንክ እና ከዳሽን ባንክ ጋር በመተባበር፣ ከሰኔ 2020 እስከ ሰኔ 2023 (እኤአ) በፈርስት ኮንሰልት የተተገበረው የኮቪድ-19 መቋቋሚያ እና ማገገሚያ ፕሮግራም፣ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በአዲስ አበባ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ላይ የሚያደርሰውን ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ ለመቀነስ ያለመ ነበር። ፕሮግራሙ ለኢ-መደበኛ ኢንተርፕራይዞች ቀጥተኛ የገንዘብ ዕርዳታ፣ ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለክፍያ የሚቀል ብድር እና ለመደበኛ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ደግሞ ሁለቱንም ዓይነት ድጋፍ አድርጓል። የገንዘብ እጦት ተግዳሮቶችን ለመፍታት ማስተርካርድ ፋውንዴሽን የ50% የብድር ዋስትና የሰጠ ሲሆን፣ ተበዳሪዎች ቀሪውን 50% በደመወዝ ወይም በግል ዋስትና ያገኙታል። እነዚህ ብድሮች ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የኪራይ እና የደመወዝ ወጪዎችን እንዲሸፍኑ ረድተዋቸዋል፣ ይህም የንግድ ሥራቸው እንዳይዘጋ አግዟቸዋል።

በኮቪድ-19 መቋቋሚያ እና ማገገሚያ ፕሮግራም ስኬት ላይ በመገንባት፣ በመካሄድ ላይ ያለው የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ማቋቋሚያ ፕሮግራም (2022-2027) የንግድ ሥራ መንሰራራትን ለማጎልበት፣ የኮቪድ-19 ማገገሚያ ስራን ለማፋጠን እና በአገር አቀፍ ደረጃ የስራ ዕድሎችን ለመፍጠር ያለመ ነው። ፕሮግራሙ፣ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን ባቀፈ የመንግስት አጋርነት እና የአዋሽ ባንክ፣ የአቢሲኒያ ባንክ፣ ህብረት ባንክ እና ዳሽን ባንክን ባቀፈ የገንዘብ ተቋማት አጋርነት ጋር በመሆን፣ በፈርስት ኮንሰልት የተተገበረው ይህ ፕሮግራም፣ በአገር አቀፍ ደረጃ የፋይናንስ፣ የንግድ ልማት እና የስነ-ልቦና አገልግሎቶችን ተደራሽ የሚያደርግ ነው። እነዚህ ውጥኖች፣ በተለይ ለወጣት ሴት ሥራ ፈጣሪዎች፣ የሥራ ስምሪት እና የገንዘብ ተሳትፎን በማበረታታት ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ፍላጎት ምላሽ ይሰጣል።

ሰኔ 2023 (እኤአ) የጀመረው ማስተርካርድ ፋውንዴሽን፣ ከክፊያ ፋይናንስ ቴክኖሎጂ ጋር በመተባበር፣ ዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ፕሮግራም፣ ሰማኒያ ከመቶ ትኩረቱን

በሴቶች ላይ በማድረግ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን፣ አነስተኛ አርሶ አደሮችን እና መካከለኛ ገቢ ያላቸውን ሸማቾች እላማ ያደረገ ያለመያዣ የብድር ሞዴልን እስተዋውቋል/እፋ አድርጓል። ይህ ቀጣይነት ያለው መርሃ ግብር ያለመያዣ የዲጂታል አገልግሎቶችን በመስጠት፣ ዲጂታል ክህሎቶችን፣ የፋይናንስ እውቀትን እና የብድር አቅርቦትን በማሳደግ የስራ እድል ፈጠራን ያመቻቻል። ዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ፣ በ75 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የእዳ ክፍያ ድጋፍ እና በ25 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የቴክኒክ የገንዘብ ድጋፍ በመታገዝ፣ ሁሉንም የፋይናንስ ተደራሽነት ለማስፋት የተነደፈ ፕሮግራም ነው። ፕሮግራሙ፣ ከስድስት አጋር ባንኮች ጋር በመተባበር፣ ከ300 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ በሆነ ገንዘብ ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ያለዋስትና የዲጂታል ብድር አሰራር ለማስተዋወቅ ያለመ ነው።

ሁሉም ብሪጅስ፣ የኮቪድ-19 መቋቋሚያ እና ማገገሚያ ፕሮግራም፣ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ማቋቋሚያ እና ዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ፕሮግራም፣ በገንዘብ ማስገኛ ዘዴ ላይ በማተኮር፣ ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን የፋይናንስ ተደራሽት እና ፍላጎት እንቅፋቶችን በማቃለል ላይ ያነጣጠሩ ናቸው። የኮቪድ-19 መቋቋሚያ እና ማገገሚያ ፕሮግራም እና ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ማቋቋሚያ ፕሮግራም ለክፍያ የሚቀል ብድር እና የገንዘብ እርዳታ የሚያቀርቡ ሲሆን፣ ተበዳሪዎቹ በደመወዝ ወይም በግል ዋስትና እንዲሰጡ ይጠይቃሉ። በአንጻሩ፣ ዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ፕሮግራም ፈጠራዊ ያለዋስትና የብድር ሞዴልን አስተዋውቋል። ዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ ፕሮግራም፣ በሰው ሰራሽ አስተውሎት የሚመራውን ተሺጋሪ የገንዘብ ማስገኛ ማዕቀፍን በመጠቀም፣ የተበዳሪዎችን የዋስትና አስፈላጊነት ያስወግዳል። ይህ ደግሞ ትልቅ የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ ስርዓት ለውጥ አምጥቷል።

**ምስል 7፡ በወጣት አፍሪካዊያን ይሰራሉ የፋይናንስ ተደራሽነት ፕሮግራም መፍትሔ የተሰጣቸው ተግዳሮቶች**

| በፍላጎት በኩል | | በአቅርቦት በኩል | |
|---|---|---|---|
| **ተግዳሮት** | **የፈታው አካል** | **ተግዳሮት** | **የፈታው አካል** |
| የዋስትና እጦት፣ በስም የተቀመጠ የቋሚ ንብረት ውስንነት | ዘፋአስፈ | በቂ ያልሆነ የአደጋ ግምገማ ስልቶች፣ አደጋን ለመቆጣጠር በዋስትና ላይ መደገፍ | ዘፋአስፈ |
| የንግድ ስራዎች ኢ-መደበኛነት፣ ደካማ የብድር ታሪክ፣ የፋይናንስ ምዝገባ አለመኖር | ዘፋአስፈ | ተገቢና ጠቃሚ የፋይናንስ አገልግሎቶች አለመኖር | ዘፋአስፈ |
| ዝቅተኛ የፋይናንስ ዕውቀትና ግንዛቤ | ብሪጅስ | ተደጋጋሚና አነስተኛ መጠን ያለውን ብድር ለማግኘት፣ ለማስተዳደር እና ለመስጠት የሚወጣው ከፍተኛ ወጭ | ዘፋአስፈ፣ ብሪጅስ |
| የመረጃ ወጥነት አለመኖር፣ ለምሳሌ የመታወቂያ አለመኖር፣ ለአበዳሪ ተገቢ መረጃ መስጠት አለመቻል | ዘፋአስፈ | ለጥአመኢዎች ማበደር ከፍተኛ አደጋ እንዳለው አድርጎ ማሳብ | ዘፋአስፈ፣ ኮመማፕ፣ ጥአመኢማ |
| የትግበራ ሂደት መንዛዛት | ዘፋአስፈ | የገንዘብ እጦት ተግዳሮቶች | ዘፋአስፈ፣ ብሪጅስ፣ ኮመማፕ፣ ጥአመኢማ |
| | | የዲጂታል መሰረተ ልማት አለመኖር፣ በገጠር አካባቢዎች የኔተዎርክ ቅርንጫፎች ውስንነት | ዘ.ፋ.አ.ስ.ፈ |

## አባሪ ሐ፡ የዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ የለውጥ ፅንሰ ሀሳብ

| ዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለስራ ፈጠራ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ችግር/ቁልፍ ተግዳሮት | የቅድሚያ ቅድሚያ ምክንያቶች/ዋና መንስኤዎች | ለውጥ የሚፈልግ (ስትራቴጂክ እርምጃዎች) | መካከለኛ ውጤት | ስትራቴጂክ ውጤት | ተፅዕኖ |
| ወጣት ተጋላጭ ሴቶችና ወንዶች ዋስትና አያገኙም፣ እንዲሁም ተገቢና ጠቃሚ የፋይናንስ አገልግሎቶች አይደርሳቸውም | ወጣት ሴቶችና ወንዶች ለፋይናንስ ተደራሽነት ችግር ይጋለጣሉ፤ | የወጣቱን የዲጂታልና የፋይናንስ እውቀት እና ሙያን ማሻሻል፤ | ወጣት ተጋላጭ ሴቶችና ወንዶች የፋይናንስ ግንዛቤና ሙያ አግኝተዋል፤ | የተሸለ ፍትሃዊ የፋይናንስ አገልግሎቶች ተደራሽነት፤ | ወጣት ተጋላጭ ሴቶችና ወንዶች ጥንካሬን ያዳብራሉ፣ የተሸለ ኑሮ ያጋጥማቸዋል፤ |
| | ተጋላጭ ወጣት ሴቶችና ወንዶች ዝቅተኛ የፋይናንስ እንዲሁም የዲጂታል እውቀት፣ ሙያና አቅርቦት ይገጥማቸዋል፤ | ወጣት ሴቶችና ወንዶች፣ በተለይም ተጋላጭና በቂ የሆነ አገልግሎት የማያገኙ ወጣቶችን ወደ ብድር ተጠቃሚነት የሚመራውን የዳታ ቋት ለመገንባት የዳታ ትግበራን ማበረታታት፤ | ወጣት ተጋላጭ ሴቶችና ወንዶች ያለዋስትና የብድር አጠቃቀማቸው ጥራት ተገምግሟል፤ | 5.83 ሚሊየን ወጣት ሴቶችና ወንዶች (80% ሴቶችና 10% ተጋላጭ ግለሰቦች) የደመወዝና የግል ስራ ተጠቃሚ ሆነዋል። ከዚህ ውስጥ 2.18 ሚሊየኑ በቀጥታ በዚህ ፕሮግራም የታገዙ ሲሆን፣ ቀሪው 3.65 ሚሊየኑ ደግሞ በሌሎች ማስተርካርድ ፋዎንዴሽን አጋር ፕሮግራሞች የታገዙ ናቸው፤ | |
| | በቂ ያልሆነ ዳታ እና የዳታ መሰረተ ልማት ወጣት ተጋላጭ ወንዶችንና ሴቶችን ያለዋስትና የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ከሚያደርጋቸው የብድር አሰጣጥ ስርዓት ያገላቸዋል፤ | አካታች የብድር ነጥብ አሰጣጥን፣ ዲጂታል የብድር አውታር ለባንኮች፣ ለጥቃቂን ፋይናንስ ተቋማትና የፋይናንስ ቴክኖሎጂ ተገቢ አገልግሎቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ቴክኖሎጂን መፍጠርና ማጠናከር፤ | ለወጣቶች ተስማሚ የሆኑና ጠቃሚ የፋይናንስ አገልግሎቶች መኖራቸው | ንተርፕራይዞች ተፈጥረዋል፣ ቀጣይነትን አሳይቷል፣ ተስፋፍቷልም፤ | |
| | ለወጣት ተጋላጭ ሴቶችና ወንዶች ሊሰጥ የሚችል ብድር ውስንነት፤ | የወጣት ተጋላጭ ሴቶችንና ወንዶችን ፍላጎት ለማሟላት ለባንኮች፣ ጥቃቂን ፋይናንስ ተቋማትና የፋይናንስ ቴክኖሎጂ የቴክኒክ ድጋፍ ማቅረብና አቅማቸውን መገንባት፤ | በአሰራር ደረጃ ለውጥ ተገኝቷል፤ | | |
| | በአማራጭ የብድር ጥራት ምዘና እና ከፍተኛ የብድር አስተዳደር ወጭ ምክንያት ባንኮች በዋስትና ላይ የተመሰረተና ትልልቅ ብድሮችን ያቀርባሉ፤ | ተሸጋሪ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችንና ጊዜያዊ የብድር ዋስትና እቅድን መንደፍና መተግበር፤ | ለወጣት ተጋላጭ ሴቶችና ወንዶች የፋይናንስ ምንጮች በግልጽ መገኘት ችሏል፤ | | |
| | ያለው ገንዘብ የሚመደበው ለጥቂት የኮርፖሬት ተበዳሪዎች ነው፤ | ያለዋስትና የዲጂታል ብድር መልካም ተሞክሮዎችን በማቅረብ፣ የቁጥጥር ሁኔታን ማገዝ፤ | | | |

| አስቻይ ሁኔታ | ቁልፍ አስተሳሰቦች | | | |
|---|---|---|---|---|
| ለዲጂታል ብድር አሰራር የተሻሻለ የገበያ ግንዛቤና የቁጥጥር ሁኔታ | ወጣቶች ስልጠናንና ስልጠናን እውን የሚያደርጉ ኔታዎችን ለመከታተል ፍላጎቱም፣ ፈቃደኝነቱም አላቸው | መረጃዎች መያዝ አለባቸው፣ የብድር አሰጣት ነጥቦች መኖር አለባቸው | ባንኮች ጠቃሚ አገልግሎቶችን ለማዳበር፣ የፋይናንስ ቴክኖሎጂን ለመጠቀምና በቂ የገንዘብ ምንጭን ለመፍጠር ፈቃደኞች ይሆናሉ። | እንዱስትሪውና ተቆጣጣሪው አካል ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ትኩራት ይሰጣል። |

## አባሪ መ፡ የስኬት ታሪኮች ከፕሮግራም ተጠቃሚዎች

## የስኬት ታሪክ የወጋገን ባንክ ከሆነው እፎይታ ያለዋስትና የብድር ስርዓት ፕሮጀክት ተጠቃሚዎች

ምስራቅ አበባው መጋቢው በ27 ዓመቷ፣ በአዲስ አበባ አያት አደባባይ አካባቢ በሚገኘው፣ በሚያማምሩ የህፃናት ልብሶች የተከበበ የህፃናት ልብሶች በሚሸጥበትን ማይክሮ-ቢዝነስ ሥራ ላይ ተሰማርታለች፡፡ እያንዳንዱ ልብስ በአስቸጋሪ ኢኮኖሚ ውስጥ ኑሮን ለማሸነፍ ወስና ወጣት ሥራ ፈጣሪ ለመሆን ያለፈችበትን ታሪክ ይናገራል፡፡ ከሶስት ዓመት የንግድ ሥራ በኋላ፣ በ24 ዓመቷ፣ የዕቃዎቿ ዝርዝር መደርደሪያ ላይ ሞልቶ የነበረበትን የጅማሮዋን ጊዜ ታስታውሳለች፡፡

ፈገግ ብላ "እነዚያን ቀደምት ጊዜያት አስታውሳለሁ" አለች፡፡ "የእኔ ሱቅ ባዶ ሆኖ ተሰማኝ፣ በራስ የመተማመን ስሜቴም እንዲሁ፡፡ ለደንበኞቼ ተጨማሪ ምርጫዎችን ማቅረብ ፈልጌ ነበር፣ ነገር ግን ያለ ገንዘብ የማይቻል ነበር."

የቢዝነስ ልማት ሥራ አስፈፃሚ ሰፈሯን ሲጎበኝ ስለ ወጋገን ባንክ እፎይታ አውታሮች ግንዛቤ ማግኘቷን በደንብ ታስታውሳለች፡፡ ጓጉታ ስለነበር፣ መረጃውን በደንብ ተከታተለችና በንግዷ እንደምትስፈነጠር በእምነት ወሰነች፡፡

"ተጨንቄ ነበር" ስትል ተናገረች፡፡

"ገንዘብ መበደር ትልቅ አደጋ መስሎ ተሰምቶኝ ነበር፡፡ ነገር ግን BDE ሁሉንም ነገር፣ ማለትም ሂደቱ እንዴት እንደሚሰራ፣ የመክፈያ ውሎች እና ብድሩን እንዴት ንግዴን ለማሳደግ እንደምጠቀም በግልፅ አብራርቶልኛል፡፡ ይህ ለማመልከት ድፍረት ሰጠኝ፡፡"

የምስራቅ የመጀመሪያ ብድር 30,000 ብር በፍጥነት ጸደቀና ታዋቂ የሆኑ ልብሶችን በማከማቸት ላይ ኢንቨስት አደረገች፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የእርሷ መደርደሪያዎቿ ሞላችና፣ ደንበኞች ትኩረት መስጠት ጀመሩ፡፡ በመጀመሪያው ስኬትዋ ተበረታታ፣ ምስራቅ ንግዷን ከፍ ለማድረግ የበለጠ በራስ የመተማመን ስሜት ተሰማት፡፡ በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ውስጥ ተጨማሪ ሁለት ብድር በማመልከት አጠቃላይ ብድርዋን ወደ 90,000 ብር አሳድጋለች፡፡ እያንዳንዱ ብድር የእርሷን ዕቃ ክምችት ለማስፋት እና እንደ ጃኬቶች እና የትምህርት ቤት ደንብ ልብሶች ያሉ አዳዲስ ምርቶችን ለመጨመር ረድቷታል፡፡

"እያንዳንዱ ብድር እንደ አንድ እርምጃ ተሰማኝ" ትላለች፡፡

“መልካም ስም እየገነባሁ ነበር፡፡ ደንበኞች የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንዳገኝ ማመን ጀመሩ፣ እናም መታመን በጣም የምኮራበት ነገር ነው፡፡

የምስራቅ ንግድ እድገት ሰፋ ያለ ተጽእኖ ነበረበት፡፡ ገቢዋ እያደገ ሲሄድ፣ ሌሎች ከአገር ውስጥ አቅራቢዎች የተለያዩ ጨርቆችን መግዛት ጀመረች፤ በዚህም አነስተኛ ንግዶችን መደገፍ ቻለች፡፡ ምስራቅ በማህበረሰቧ ውስጥ ያሉ ጥቂት ሴቶችን መምከር እና በእፎይታ በኩል ተመሳሳይ እድሎችን እንዲያፈላልጉ ማበረታታት ጀመረች፡፡

"ይህ ብድር ከገንዘብ በላይ ነው" ትላለች፡፡ "የማብቃት ጉዳይ ነው፡፡ ሌሎች ሴቶች የሚቻል መሆኑን እንዲገነዘቡ እና በችሎታቸው እንዲያምኑ እፈልጋለሁ፡፡ "

የምስራቅ በራስ የመተማመን ስሜት ከንግድዋ ጋር አድጓል። ጠቃሚ የፋይናንስ ሙያዎችን ቀስማለች እናም አሁን የደንበኞቿን ፍላጎት በተሻለ ሁኔታ ተረድታለች።

"እቅድ አውጪ፣ ተደራዳሪ እና ነገሮችን ማድረግ የሚችል ሰው ሆኛለሁ" ስትል በኩራት ትናገራለች። ዛሬ ምስራቅ ሱቅዋን ለማስፋት እና በቁጥር እያደገ የመጣውን ደንበኞቿን ለማስተናገድ ረዳት ለመቅጠር አቅዳ አራተኛ ብድርዋን እየጠየቀች ትገኛለች። ከረዥም ጊዜ ግቦቿ ውስጥ፣ ሁለተኛ ሱቅ ሌላ ቦታ መክፈት እና ደንበኞች በልካቸው የተሰሩ ልብሶችን የሚያገኙበት የልብስ ስፌት ቦታ መፍጠር የሚሉት ይገኙበታል። ምስራቅ ጉዞዋን መለስ ብላ ስታስብ ታመሰግናለች፤ "ይህ ፕሮግራም ለእኔ ብቻ ሳይሆን፣ በቢዝነስ ስራ አቅማቸውን ለመፈተሽ ለሚፈለልጉ ብዙ ሴቶች በረከት ነው።"

## የስኬት ታሪክ ከኦሮምያ ኅብረት ሥራ ባንክ፣ 'ሚቼ' ያለዋስትና ዲጂታል ብድር ስርዓት

በአዲስ አበባ ቦሌ ለሚ ኩራ የማይክሮ ቢዝነስ ባለቤት የሆነችው የ33 አመቷ ወይንሸት ንጉሴ መኮንን ከሁለት ሰራተኞች ጋር ለ5 አመታት እየሰራች ነው። በ33 ዓመቷ ወይንሸት ንጉሴ መኮንን ከአዲስ አበባ ወጣ ብሎ በሚገኘው ቦሌ ለሚ ኩራ የሚገኘውን ለ5 አመት የሰራችውን የለሊት ልብስ ቡቲኳን ወደ ጥሩ ንግድ ቀይራለች። መነሻዋ ማጀቴ ከተባለች ትንሽ የሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ ከተማ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ባሏን ካገባች በኋላ በ20 ዓመቷ ወደ ዋና ከተማ መጣች። ወይንሸት በአዲሱ ከተማ ውስጥ የሚያጋጥሟትን ፈተናዎች በመጋፈጥ፣ እንጀራና ባህላዊ ቡና ለጎረቤቶች በመሸጥ ለስራ ፈጠራ ጉዞዋ መሰረት ጣለች። በኋላም ዘመናዊ እና ምቹ የለሊት አልባሳትን በማቅረብ ስኬቷን ቀጠለች።

"ከየት ተነስቼ እንዴት እዚህ እንደደረስኩ ሳስብ ኩራት ይሰማኛል፣ እናም ጉዞዬ ጥሩ እንደ ነበር አውቃለሁ፤" ትላለች። ለዓመታት ያሳለፈችው ትጋትና ለቁጠባ የሰጠችው ትኩረት፣ ቡቲክ ለመሥረት ለነበራት ሀሳብ አስታዋጽኦ አድርጎላታል።

"ልዩ የሆነ ነገር መፍጠር ፈልጌ ነበር" በማለት ታስታውሳለች። "በገበያው ላይ ጥራት ያለውና ተመጣጣኝ የሆነ የመኝታ ልብስ ለማግኘት ክፍተት አየሁ፣ እና ይህን ክፍተት መሙላት እንደምችል ተረዳሁ።"

በዚህ ራዕይዋ ነበር ወይንሸት፣ በአዲስ አበባ የጅምላ ገበያ ዋና መነሃሪያ ከሆነው ከመርካቶ ጥራት ያላቸውን የለሊት ልብሶች በማምጣት ከ5 ዓመት በፊት ሱቋን የከፈተችው። ቡቲክዋ ተስፋ ቢያሳይም፣ ወይንሸት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የደንበኞችን ፍላጎት ለማሟላት፣ ተጨማሪ የስራ ካፒታል እንደሚያስፈልጋት ተረዳች። ከዋስትና ነፃ የሆኑ ብድሮች እውነት እና በጣም ጥሩ መሆኑን የተገነዘበችበትን የኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ ሚቼ ዲጂታል የብድር መዋቅር አፈላልጋ አገኘች። በባንኩ ተወካዮች በመበረታታት እድሉን ተጠቀመች፤ እናም የመጀመሪያው 5,000 ብር ብድር በአንድ ቀን ውስጥ ጸደቀላት።

"መጀመሪያ ላይ አላመንኩም ነበር" አለች እየሳቀች። "ነገር ግን እውነት ነበር፣ እናም እኔ በሚያስፈልገኝ ጊዜ ተገኘ፣" አለች።

ወይንሸትን ብድርዋ ተጨማሪ ዕቃ እንድታከማች እና መደርደሪያዋን እንድትሞላ አስችሏታል። በሚቼ በኩል 30 ጊዜ ብድር አግኝታለች፣ የብድር ገደቧን ጣራ ወደ 80,000 ብር አደረሰች።

የግል እድገቷ አስደናቂ ነው፣ ብድርን በማስተዳደር የፋይናንስ ችሎታዎችን በማዳበር፣ ለወደፊት እድሎች አዘጋጅቷታል.

"በዚህ ጉዞ ብዙ ተምሬአለሁ" ስትል ሀሳቧን አንጸባርቃለች። "የበለጠ በራስ የመተማመን መንፈስ እና አቅም እንዲኖረኝ አድርጎኛል።"

ሱቅዋን ለማስፋት፣ ተጨማሪ ምርቶችን ለማቅረብ እና ቡቲክዋ የቤተሰብ ስም ሆኖ ለማየት ትመኛለች።